# የእግዚአብሔር ሕግ

## መግቢያ

አምላካችን እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረው ጊዜ የሚመዝንና የሚያስተውል አእምሮ ሰጥቶት በነፃነት የፈጠረው መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉ:: ስለዚህም በተሰጠው ነፃ አእምሮ ክፋውን ከመልካሙ በመለየት በእግዚአብሔር ፊት በጽድቅ መኖር ለሰው ልጅት ከፍጥረት መጀመሪያ አንሥቶ የተሰጠው ጸጋ ነው:: ይህንንም የጻድቃን አባቶችን ታሪክ በግልጥ የሚያስረዳ መሆኑን በመጽሐፍ ተጽፏል:: በዚህ ተቃራኒ ደግሞ አእምሮአቸውን በሕገ ልቡና ከኃጢአት ለይተው መኖር የተሳናቸው ሰዎች ሞት እንደተፈረደባቸወ በሰብአ ትካት (በኖኅ ዘመን የጠፉ ሰዎች) እና በሰዶምና በገሞራ ሰዎች ታሪክ የታወቀ ነው::

አምላክ ለሰው ልጆች ላዘጋጀው ክብር እንደብቁ መመሪያ የሚሆኑ የእምነትና የምግባር ሕግጋትን በሕገ ልቡና ብቻ ሳይሆን በዓይን የሚታይና በእጅ በሚዳሰስ ሁኔታ በጣቶቹ በመጻፍ በነቢዩ በሙሴ አማካይነት ለእስራኤል ሰጥቷል:: ዘጸ. 20-1:17 ዘዳግ. 5:: እነዚህ ሕግጋት አሥራ በመሆናቸው «አሠርቱ ትእዛዛት በመባል ይታወቃሉ:: በሌላ አነጋገርም «ትእዛዛተ ኦሪት» ይባላሉ:: በዚህ ጽሑፍም በተከታታይ ስለእነዚሁ «አሠርቱ ትእዛዛት» ለመግለጽ ያቀድን በመሆኑ ለዛሬ መግቢያውን እነሆ::

አሠርቱን ትእዛዛት በጠቅላላው ስንመለከታቸው የሚከተሉትን ዐበይት ነጥቦች እንድናስተውል ያደርጉናል::

### ሀ. <u>አሠርቱ ትእዛዛት</u>

በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የተደረጉ ኪዳናት ናቸው::

አሠርቱ ትእዛዛት የተሰጡት ለአለፉት በቀደምት ዘመናት ለነበሩት ሰዎች ብቻ ሳይሆን እኛም የዚህ ዘመን ሰዎች ክርስቶስና ደቀ መዛሙርቱ በኃላም ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ካስተማሩት ርቱዕና ምሉዕ የክርስትና ሕግና ትምህርት ጋር በማዋሐድ እንድንመራባቸው ነው:: ስለዚህ ከሁሉ አስቀድሞ እነዚህ አሠርቱ ትእዛዛት በእግዚአብሔርና በሰው ልጆች መካከል የተደረጉ ኪዳናት መሆናቸውን መረዳት ይገባል:: ነቢየ እዚአብሔር ሙሴም ይህንኑ ለማስረዳት « አምላካችን እግዚአብሔር በኮሬብ ከእኛ ጋር ቃለ ኪዳን አደረገ:: እግዚአብሔር ዛሬ በዚህ በሕይወት ካለነው ከእኛ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ እግዚአብሔር ዛሬ በዚህ በሕይወት ካለነው ከእኛ ከሁላችን ጋር እንጂ ከአባቶቻችን ጋር ብቻ ይህችን ቃል ኪዳን አላደረገም::» በማለት አስገንዝቧል:: ዘዳ. 5-2:3:: ከዚህ በመነሣት ነው አሠርቱ ትእዛዛት የተጻፉባቸውን ጽላት «የቃል ኪዳኑ ጽላት» ብለን የምንጠራው:: ዘዳ. 9-11:: እነዚህ አሠርቱ ትእዛዛት የተጻፉበት መጽሐፍ» ተብሏል:: ዘዳ. 24-7::

እንግዲህ እነዚህ ትእዛዛት እኛ እግዚአብሔርን ባመለክንበት ወይም እርሱም ባመነበት ጊዜ በእኛና በእርሱ መካከል የተመሠረቱ ኪዳናት ናቸው:: ልዑል እግዚአብሔርም እነዚህን ኪዳንና ከሰዎች ልጆች ጋር ባደረገ ጊዜ በሚያስፈራና በሚያስደነግጥ ሁኔታ እንደነበር ቅድስ መጽሐፍ ያስረዳናል:: በዚያን ጊዜ ተራራው ይናወጥ ነበር:: የሲና ተራራ ሁሉ ይጤስ ነበር:: ከእርሱም እንደ እቶን ያለ ጢስ ይወጣ ነበር:: ዘዳ. 19-16:-19:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ይህንኑ ሁኔታ ሲገለጥ «ሙሴ እጅግ እፈራለሁ እንቀጠቀጣለሁ እስኪል ድረስ የሚታየው እጅግ የሚያስፈራ ነበረ» ብሏል:: ዕብ. 12-21::

### ለ. <u>የትእዛዛቱ አስፈላጊነት</u>

እነዚህ አሠርቱ ትእዛዛት በፈጣሪአችን በእግዚአብሔር አንደበት የተነገሩ በጣቶቹም የተጻፉና ከእርሱ የተሰጠ መሆናቸው አስፈላጊነታቸውን የጎላ ያደርገዋል:: ዘጸ. 20-1:: ዘዳ. 9-10:: ነቢዩ ሙሴም አሠርቱን ትእዛዛት ተቀብሎ ሲወርድ

ከተራራው በታች የሚቃጠል መሥዋዕት የደኅንነትም መሥዋዕት ከአቀረበ በኋላ ደሙን ወስዶ በሕዝቡ ላይ ረጨው:: በመቀጠልም «በዚህ ቃል ሁሉ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ያደረገው የቃል ኪዳኑ ደም እነሆ» በማለት በናግሯል:: ክዳ. 24-4:8::

አሠርቱ ትእዛዛት አስፈላጊ ከመሆናቸው የተነሣ በእግዚአብሔር ጣቶች ከአንድ ጊዜ በላይ ተጽፈዋል:: ዘዳ. 20-2:17:: ዘዳ. 5-6:21:: እግዚአብሔርም ሁለት ጊዜ ጽፏቸዋል:: መጀመሪያ ሙሴ በተቀበላቸውና ከእጁ በወደቀው በተሠበሩ ሁለቱ ጽላት ላይ ለሁለተኛ ጊዜ ደግሞ ሙሴ በመጀመሪያዎቹ ዓይነት በቀረጻቸው ጽላት ላይ ነው:: ዘዳ. 10-41:: ዘዳ. 34-1::

ሐ. <u>ቁጥራቸው ለምን አሥር ሆነ ?</u>

በዕብራውያን አሥር ቁጥር የምሉዕነት ምሳሌ ነው:: አሠርቱ ትእዛዛትም የሕግጋት ሁሉ ማለትም የትእዛዛት ሁሉ ምሳሌዎች ናቸው:: በቁጥር አሥር መሆናቸው የምሉዕነት ምሳሌ መሆኑን በተወሰኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ለማስረዳት እንሞክራለን::

አሥሩ ደናግል ማቴ. 25-1:12:: በዚህ ምሳሌ አሥር ቁጥር መላውን ዓለም የሚያመለክት ነው:: ጻድቃንንም ኃጥአንንም ጨምሮ ሁሉንም የመለከታል:: ተዘጋጅተው የቆዩት አምስቱ የጻድቃን የቀሩት አምስቱ ደግሞ የኃጥአን ምሳሌ ናቸው::

ጌታቸው እስኪመጣ ድረስ ነግደውና አትርፈው እንዲጠብቁት አሥር ምናን የሰጣቸውን ባሪያዎችም ያመለክታል:: ሉቃ. 19-13:: እነዚህ ባሪያዎች የሰው ሁሉ ምሳሌዎች ናቸው የጻድቃንም የኃጥአንም:: ከእነዚህ ባሪያዎች መካከል የፊተኛውና በሚገባ ነግዶ ያተረፈው «ጌታ ሆይ ምናንህ አሥር ምናን አተረፈ» ብሎ ለጌታው መለሰ:: ሉቃ. 19-17:: ስለዚህም በተሰጠው ችሎታና ዕውቀት ሁሉ ተጠቅሞ በመሥራት የሚጠበቅበትን አደራና የተጣለበትን ኃላፊነት በሚገባ የተወጣ የፍጹም ሰው ምሳለ ሆኖ እንመለከታለን:: ይህ ባሪያ የተጠበቀበትን በሚገባ ፈጽሞ በመገኘቱ ከጌታው የተቀበለው ዋጋም ሙሉ ነው:: «አንተ በጎ ባሪያ በጥቂት የታመንክ ስለሆንክ በአሥር ከተማዎች ላይ ሥልጣን ይሁልልህ::» ሲል ጌታው አመስግኖታል:: ሉቃ. 19-17::

የጠፋው ድሪም ታሪክም አሥር ቁጥር የምሉዕነት ምሳሌ መሆኑን ያስረዳል:: በመጽሐፍ የተጠቀሰችው ሴት አሥር ድሪም ነበራት:: አንዱ ጠፋ:: በዚህ ታሪክ አሥሩ ድሪም የሴቲቱ ጠቅላላ ንብረት ምሳለ ነው:: ሉቃ. 15-8::

ስለ አሥራት የተሰጠው ትእዛዝም የሰውን መላ ንብረት በአሥር እጅ እንደመዘነው እንመለከታለን:: ካሰውም አንዱን እጅ ለእግዚአብሔር እንዲሰጥ ታዝዟል::

ነቢዩ ዳንኤልም «እኛን ባሪያዎችን  አሥር ቀን ያህል ትፈትነን ዘንድ እለምንኻለሁ» ሲል የመጨረሻና ከፍተኛውን የፈተና ጊዜ ለእርሱ አቅምም ፍጹም የሆነውን ማለቱ ነው:: ዳን. 1-12::

ስለ አሥር ቁጥር የተነገረው ሁሉ በመቶና በሺዎች ለሚነገሩ አሥሮችም ሊተረጐም ይችላል:: ለምሳሌ የጠፋውን በግ ተከትሎ ስለሄደው መልካም እረኛ የተነገረው ይህን ሊያስረዳ ይችላል:: በዚህ ታሪክ ውስጥ «መቶ በጎች» የሚያመለክቱት በእግዚአብሐር የሚያምኑትን ሰዎች ሁሉ ነው:: እንግዲህ አሥር ቁጥር ከፍብለን እንደጠቀስነው የምሉዕነት ምሳሌ ነው:: ቅዱስ አውግስጢኖስ የዩሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 21-11ን በተረጐመበት ድርሳኑ «አሥር ቁጥር በአሠርቱ ትእዛዛት የተገለጡት የሕግጋት ሁሉ ምሳለ ነው» ያለውም ለዚህ ነው:: በእርግጥም አሠርቱን ትእዛዛት በጥሞና ብንመረምራቸው በእያንዳንዱ ውስጥ ያለው ምሥጢራዊ ትርጉም የተቀሩትን ሕግጋት ሁሉ የሚያጠቃልል ሆኖ እናገኘዋለን:: ይሁን እንጂ ሁሉም ደግሞ ተጠቃለው በአንድ ትዕዛዝ ይካተታሉ:: ይህም ቆየት ብለን በሰፊው የምንመለከተው ፍቅር ነው::

መ. <u>ሁለቱ ጽላት</u>

አሠርቱ ትእዛዛት ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች የያዘ ነው:: የመጀመሪያው ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረውን አምልኮታዊ ግንኙነት የሚመለከቱ ሶስት ትዕዛዛትን የቀፈ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሰዎች እርስ በርሳቸው ስለሚኖራቸው ግንኙነት የሚያወሱትን ስድስት ትእዛዛት የያዘ ነው::

ጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አንድ ሕግ ዐዋቂ ሊፈትነው ሽቶ «መምህር ሆይ ከሕግ ማንኛይቱ ትእዛዝ ታላቅናት» ብሎ በጠየቀው ጊዜ መድኃኒታችንም መልሶ «ጌታ አምላክህን በፍጹመ ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ:: ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህችን ትመስላለች እርሷም «ባልንጀራህን እንደነፍስህ ውደድ» የምትለው ናት ኦሪት እና ነቢያትም በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ጸንተዋል::» ማለቱ ለዚህ ነው:: ማቴ. 22-35:40::

በእነዚህ ጽላት ላይ በመጀመሪያው ነገረ አምላክን የሚያወሱት ትእዛዛት የተጻፍ ሲሆን በሁለተኛው የተጻፉት ደግሞ ፍቅረ ቢጽን የሚያስተምሩት ተጽፈዋል:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛመሙርቱ ባስተማረው ጸሎትም በመጀመሪያ የተቀመጠው ነገረ ሃይማኖትን የሚያወሳው ነው:: «አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር ስምህ ይቀደስ መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በምድር ይሁን...» ካለ በኃላ ነው ስለ ፍቅረቢጽ የሚያወሱት ቃላት የተከተሉት:: ማቴ. 6-9

<u>ሕገ ልቡናን ያስታውሱናል::</u>

እነዚህ አሠርቱ ትእዛዛት በእግዚአብሔር ጣቶች የተጻፋና በጽላት ላይ የተቀረጹ ቢሆኑም በሰው ዘንድ ያልነበሩና የማይታወቁ አዲሶች አይደሉም:: ከሙሴ እና ከጽላቱም መቀረጽ በፊት የነበሩ ናቸው:: በመሆኑም ሳይጻፋ በሕገ ልቡና አበው ሲመሩባቸው የነበሩትን ቀደምት ሕግጋት ያስተውሱናል:: ለዚህም የሚከተሉትን ማረጋገጫዎች እንመልከት::

1. *<u>አትግደል:-</u>* መግደል ቀድሞም ቢሆን በሰው ልጆች ዘንድ ኃጢያት ነበር:: ቃየል አቤልን በገደለው ጊዜ እግዚአብሔር ቃየልን በከባድ ቅጣት እንደቀጣው ተጽፏል:: ዘፍ. 4-13:: ስለዚህ ይህ ትእዛዝ በጽላት ተቀርጾ ለሙሴ ከመሰጠቱ በፊት በሕገ ልቡና ዘመን በሰዎች አእምሮ የሚታወቅ ነበር::
2. *<u>አታመንዝር:-</u>* ሰዎች ዝሙት ኃጢአት መሆኑን ያወቁት ከሙሴ ዘመን በፊትም ነበር:: ከሙሴ በመቶ በሚቆጠሩ ዓመታት ቀድሞ የነበረው ጻድቁ ዩሴፍ የጲጥፋራ ሚስት በኃጢአት ወጥመድ ለመያዝ በፈተነችው ጊዜ «እንዴት ይህን ክፉ ነገር አደርጋለሁ? በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ?» በማለት እምቢ ማለቱ ዝሙት ከሙሴ በፊትመ በሕገ ልቡና በኃጢአትነቱ የሚታወቅ ለመሆኑ ማስረጃ ነው:: ዘፍ. 39-9:: እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሔር በጥፋት ውኃ ዓለምን ያጠፋው የሰው ልጅ ለክፍ ሥራ የተገዛና ኃጢአት የሠለጠነበት በመሆኑ ነው:: ዘፍ. 6-5:8:: ዘፍ.7-19:: እነዚህ የምኞትና የፍትወት ሥራዎች ሁሉ ኃጢአት መሆናቸወ ከሙሴ በፊት በሕገ ልቡና ዘመንም የሚታወቁ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ::
3. *<u>አትስረቅ:-</u>* መስረቅ ክፉ ሥራ (ኃጢአት) እንደሆነ ቀደመ ብሎ የሚታወቅ ለመሆኑ ያዕቆብ ከላባ ጋር ሲከራከርባቸው የነበሩት የተሰረቁ የላባ አማልክት ታሪክ ምስክር ነው:: ዘፍ. 31-30:39::
4. *<u>አትመኝ:-</u>* መመኘትም ኃጢአት መሆኑ ቀደም ብሎ ከሙሴ በፊትም መታወቁ ኢዮብ «ከዓይኔ ጋር ቃል ኪዳን ገባሁ እንግደህስ ቆንጆይቱን እንዴት እመለከታለሁ?» ሲል ከተናገረው ቃል ግልጥ ሆኖ ይገኛል:: ኢዮ. 31-1::
5. *<u>ሰንበትን አክብር:-</u>* ይህም አሠርቱ ትእዛዛት ለሙሴ ከመስጠታቸው በፊት የሚታወቅ ነው:: እሥራኤል መናን እንዲለቅሙ በተነገራቸው ጊዜ ሰንበትን ደግሞ እንደያከብሩ ታዝዘው ነበር::

«እግዚአብሔርም የተናገረው ይህ ነው:: ነገ እረፍት ለእግዚአብሔርም የተቀደሰ ሰንበት ነው::» ዘዳ. 16-23:29:: በተለይም እጅግ ቀደም ብሎ እግዚአብሔር ፍጥረቱን ከፈጠረ በኃላ በሰባተኛው ቀን ማረፋ ሰንበትን ማክበር ከሙሴ በፊትም የሚታወቅ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው:: ዘፍ. 2-2:3::

ከዚህ በላይ የጠቀስናቸው ማስረጃዎች አሠርቱ ትእዛዛት በእግዚአብሔር ጣቶች ተጽፈውና በጽላቱ ተቀርጸው ለሙሴ ከመሰጠታቸው በፊት በሕገ ልቡና በሰው ልጆች አእምሮም የነበሩ በመሆኑ እነዚህን ቀደምት ሕግጋት ልቡና የሚያስታውሱን ናቸው ለማለት ይቻላል::

በአጠቃላይ ደግሞ እነዚህን ትእዛዛተ እግዚአብሔር ከእርሱ የተሰጡና በእርሱና በሰው ልጆች መካከል የተደረጉ ኪዳናት መሆናቸውን እያሰቡ የፈጸሟቸውና የተመሩባቸው በረከትን ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚያገኙ ሲሆን የናቁአቸውን የተውአቸው ደግሞ መርገምን ይቀበላሉ:: እነዚህን ትእዛዛተ እግዚአብሔርን ለመፈጸምና የእግዚአብሔርን የጸጋ ስጦታም ለመቀበል ደግሞ እያንዳንዳቸውን በጥልቀት መመልከትና ማጥናት ተገቢ ነው:: በሚቀጥለው እትም የመጀመሪያውን ትእዛዝ ይዘን እንቀርባለን::

የእግዚአብሔርን ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን::

## አንደኛው ትእዛዝ

## «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ»

ሰዎች ይህን ትእዛዝ በሚያነቡበት ወይም በሚሰሙበት ጊዜ «ይህ ከእኔ ጋር ምን ግንኙነት አለው? ይህ ሊነገር የሚገባው ለከሐድያንና ለመናፍቃን ወይም ከሥጋዊ ዕውቀታቸው የተነሣ አሊያም ከፍልስፍና በመነጨ ሁኔታ ከሃይማኖት ያፈነገጡትን ነው። እኔ ግን በሳምንት ይኸን ያህል ቀን እጸማለሁ አሥራት አወጣለሁ በየሰዓቱ እጸልያለሁ ከልቤ እዘምራለሁ የቤተ ክርስቲያን መርሐ ግብሮችን ያለማቋረጥ እከታተላለሁ ስለሆነም ይህ ትእዛዝ አይመለከተኝም» ይሉ ይሆናል።

ነገር ግን ይህ ትእዛዝ ማንንም ሳይለይ ሁሉንም ሰው የሚመለከት ነው። «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ» ሲልም በሰው እጅ የተጠረቡትንና ሰወ ያሰማቸውን በፀሐይ በባሕር ወይም በእሳት ወዘተ የተሰየሙትን ጣዖታት ብቻ አይደለም። ከእነዚህ ሌላ በሰዎች የሚመለኩ እጅግ ብዙ ጣዖታት አሉ። አንዳንድ ሰዎች ኃይላቸውን ያመልካሉ። ሌሎችም ሥልጣናቸውን የተቀሩት ደግሞ ክብራቸውን ገንዘባቸውን ውበታቸውን ወዘተ. ያመልካሉ በየፊናቸው የየራሳቸው ጣዖታትና አማልክት አሏቸው ማለት ነው። ነገር ግን ሁሉም ሰዎች «በእውነት አንዱን እግዚአብሔርን እናመልካለን። በእርሱም እናምናለን» ሲሉ ይሰማሉ።

በቀደምት ዘመናት የነበሩ ሰዎች ከፍርሃት ወይም ከመጠን በላይ በሆነ ፍቅር አሊያም ለጥቅም ሲሉ እንግዳ አማልክትን ያመልኩ እንደነበረ ታሪክ ያስረዳል። በእነርሱ አመለካከት ጥሩና መጥፎ የሚሏቸው አማልክትም ነበሯቸው። ጥሩ ከሚሏቸው ጥቅምን ፍለጋ መጥፎ የሚሏቸውን ደግሞ በመፍራት ያመልኳቸው ነበር ። ለምሳሌ ታላላቅ ነገሥታትን ለጥቅም ሲሉ መናፍስትን ታላላቅ ወንዞችንና ፏፏቴዎችን እሳትን ወዘተ. ደግሞ በመፍራት ያመልካሉ። መሳ. 3-8:14። ቀጥሎ የአምልኮ ዓይነቶችን በዝርዝር እንመልከት።

1. ገንዘብን ማምለክ

ገንዘብ ብዙ ሰዎች የሚያመልኩትና የእግዚአብሔርን አምላክነት የሚቀናቀን ጣዖት ነው። ስለዚህም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራው ስብከቱ ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም ወይም አንዱን ይጠላል ሁለተኛውን ይወዳል ወይም አንዱ ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል። ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም» በማለት ነገሮናል። ማቴ. 6-24

ማንም እግዚአብሔርን አመልካለሁ እያለ ገንዘብን ከመጠን በላይ የሚያፈቅር ከሆነ ራሱን ያሞኛል። ይህም የገንዘብን መገልገያነት መቃወም አይደለም። የገንዘብ አገልግሎትም ቢሆን ደግሞ ለአምልኮ ጣዖትና ለገቢረ ኃጢአት ከዋለ ገንዘብ አምላክ ሆኖ እየተመለከተ ነው ማለት ነው።

በይበልጥ ደግሞ በአንዳች አገልግሎት ላይ ሳያውሉ ገንዘብን በማከማቸት የሚረኩ ሰዎች ለገንዘብ የተገዙና ገንዘብና አምላካቸው ያደረጉ ናቸው። እንደዚህ ዓይነት ሰዎች የሳንቲም ሽራፊ እንድትወድቅባቸው የማይሹና በፈቃዳቸውም ገንዘብን የማይሰጡ (የማይመፀወቱ) ናቸው። እንደህ የሚያደርጋቸው ፍቅረንዋይ ነው። ገንዘብን ከማንም በላይ ስለሚወዱ እንደጣዖት ያመልኩታል። ጌታችን «ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ» ሲል የተናገረው ለዚህ ነው። ማቴ. 6-19

የሰው ልጆች የሆንን እኛም የገንዘብ ፍቅር ወደልቡናችን እንዲገባና እንዲሠለጥን ከፈጣሪአችንም ጋር እንዳያጣላን መንገድ ከመክፈት በጽኑ ልንጠነቀቅ ይገባል። አንድ አባት መንፈሳዊ ልጃቸውን ሲመክሩ «ገንዘብ ካለህ በሥራ ላይ አውለው። ገንዘብ ከሌለህ ግን ምንም አትሰብስብ» ማለታቸው አደገኛነቱን የሚያስረዳ ነው።

2. መልካም ያደረጉልንን ማምለክ

ብዙ ሰዎች ውለታ የዋለላቸውን ሰው የመልካሉ። ወይም ፈጽመው ይገዙለታል። ይህ ሰው ከሚከፋ እግዚአብሔር ቢያዝን መልካም እንደሆነ ይቆጠራሉ። አንድ ደራሲና ገጣሚና «ለሰዎች መልካምን አድርግ ልቡናቸውን የአንተ ታደርጋለህ» ሲል የተናገረው በመልንም ሥራቸው በለሎች ዘንድ የሚመለኩትን ለመጥቀስ ነው። መልንም የምንሠራው ግን በሌሎች ዘንድ የሚመለኩትን ለመጥቀስ ነው። መልካም የምንሠራው ግን የሌሎች ገዦች ለመሆን ብለን መሆን የለበትም።

መልካም ላደረገልን መልካም ውለታ መዋል ከሰአዊነታችንና ከክርስትናችን ሕግ የተነሣ የማጠበቅብን ከመሆኑ በቀር መልካም የሠሩልንን ሰዎች እንደፍጹማን አማልክት ቆጥረን በደባልነት ልናመልካቸው ደግሞ የማይገባ መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል:: ለመልካም ሥራቸው ሰማየዊ ዋጋ ከእግዚአብሔር ማግኘት ሲገባቸው በውዳሴ ከንቱ ተይዘው ድካማቸውን እንዳያስቡ እንቅፋት በመሆን በምድራዊ ዋጋ ሰማያዊውን በረከት እንዲያጡ እኛ ምክንያት ከመሆን መጠበቅ አለብን::

3. ዝናን ማምለክ

አንዳንድ ሰዎች በሚገባ ወይም በማይገባ ነገር ለዝናቸው ወይም ለሚያውቁት ሰው ዝና ሲሟገቱ ይታያሉ:: የራሳቸውን ወይም የሚሟገቱለትን ሰው ስህተት በመሸፈን ጥፋቱን ከቤተ ክርስቲያን ከሕዝብ ወይም ከመንግሥት በላይ አድርገው ዝናውን ለመጠበቅ ይጥራሉ:: መሳሳታቸውን ወይም የሚሟገቱለት ሰወ ስህተት መፈጸሙን ቢያውቁም ስለምድራዊ ዝና ሲሉ እውነትን ይደብቋታል:: ይህ ደግሞ ለዝና መዛትና ዝናን ማምለክ ነው:: ጸሐፊው ስለዝና የሚሟገቱትን አስመልክቶ «የባልንጀራ ዓይን ለስህተት የተደፈነች ናት:: የጠላት ዓይን ግን እያንዳንዱን ጥፋት ትገልጣለች» ብሎአል:: የዚህ ዓይነቱ ባልንጀራ ጠቃሚ አይደለም:: ጥፋቴን ዓይቶ ካልነገረኝ እንድስተካከልም ካልመከረኝ ለባዶነቴ ቢሟገትልኝ በመጨረሻ ከውድቀቴ ሊያነሣኝ አይችልምና አይረባኝም:: «እውነተኛ ባልንጀራ መስተዋት ነው» ይባል የለ::

ለሰው ዝና ተብሎ «እውነት» መሥዋዕት መሆን የለባትም:: ለጥቅም ተብሎም የሰው ዝና መጠበቅና የሐሰት ተሟጋች መሆን አይገባም:: ስለዚህ ነገርም መጽሐፍ «ኃጥኡን የሚያጸድቅና በጻድቁ ላይ የሚፈርድ ሁለቱ በእግዚአብሔር ዘንድ አስጠያፊዎች ናቸው» ብሏል:: ምሳ. 17-15:: እውነትን ስለዝና መለወጥ የእውነት አምላክና እውነት የሆነውን እግዚአብሔርን ክዶ ባለዝና የሆነውን ሰው ማምለክ ነው:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «እኔ መንገድም እውነት ሕይወትም ነኝ» ብሏልና እውነትን ለዝና መለወጥን ጣዖትን ከእግዚአብሔር መጣላት ነው:: ዮሐ. 14-6::

ለእግዚአብሔር የሚገባውን ክብር ለሰው የሚሰጥ ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰውን ያመልካል:: እግዚአብሔርን ከቋስደሰት ይልቅ ሰውን በማይገባ ነገር የሚያስደስት የሚያስደስተውን ያመልካል:: ለእግዚአብሔርም ከመታዘዝ ይልቅ ለሰው የሚታዘዝ ሰው የታዘዘለትን ያመልካል:: ቅዱስ ጳውሎስም «ሰውን ወይስ እግዚአብሔርን አሁን እሺ አሰኛለሁን? ወይም ሰውን ደስ ላሰኝ እፈልጋለሁን? አሁን ሰውን ደስ ባሰኝ የክርስቶስ ባሪያ ባልሆንኩም::» በማለት መናረሩ ለዚሁ ነው:: ገላ. 1-10::

ማንም ሰው ቢሆን የሚያደርገውን ነገር ሁሉ በንጹሕ አእምሮ እግዚአብሔርን ብቻ ለማስደሰት ማድረግ አለበት:: ለእግዚአብሔር የሚገባውን ፍቅር አክብሮትና አምልኮት ለማንም ሳይለውጥና ማንንም ሳያወድስ ኅሊናውን ክዶ ለሌሎች ዝና ሳያኅበድድ በተገቢው መንገድ መኖር አለበት:: አለበለዚያ «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ» ያለውን የእግዚአብሔር ትእዛዝ እንዴት ማክብር ይቻላል?

4. መሪዎችን ወይም ታላላቆችን ማምለክ

መጽሐፍ ቅዱስ «ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ:: እነርሱ ስለነፍሳችሁ ይተጋሉ» ይላል:: ዕብ. 13-17:: ይህ የሐዋርያው አባባል ታዘዙአቸው አታምፁባቸው እንጂ በእግዚአብሔር ፈንታ አምልኳቸው የሚል አይደለም:: መሪዎችንም ሆነ መንፈሳዊ አባቶችን ለመሪነታቸውና ለአባትነታቸው በሚገባው መጠንና ወሰን በመታዘዝ ልንገዛላቸው ከሚገባ በቀር ከእግዚአብሔር ጋር አወዳድረን ልናመልካቸውና ከፈጣሪአችን የሚያጣላን ትእዛዝ በሚያዝዙን ጊዜም በጅብለን ልንቀበላቸው አይፉባም::

መሪ ወይም አባት ከሚገባው መንገድ የወጣ እንደሆነ ከበታቹ ያለውም የግድ ተከትሎት እንዲሄድ ሕግ አልተሠራም:: መንፈሳውያን መሪዎችና አባቶች የነበሩት እነ አርዩስ መቅዶንዩስ ንስጥሮስ አውጣኪ የመሳሰሉት ከእውነት ባፈነገጡ ጊዜ መንፈሳውያን ልጆቻቸውም አብረው አላፈነገጡም:: ከሃይማኖት የሚያወጣ ከምግባር የሚለይ ሥራቸውን መንፈሳውያን ነበሩ ብለው አልተቀበሉትም አወገዙት እንጂ:: «ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል» ተብሏልና:: የሐቸ. 5-29:: ከእግዚአብሔር ይልቅ የእነዚህ መናፍቃን ትምህርት አምላካቸውን ያደረጉት ጠፍተዋል ተለይተዋል::

ከኅሊና ጋር የሚቃረን ለአእምሮ የማይመተ የሰውን የማንነት ሚዛን ያለፋ እንዲሁም እግዚአብሔርን ከማምለክ ጋር የሚጋጭ መታዘዝ እግዚአብሔር የሚሻው አይደለም:: ሰው ውስጣዊ ሰላሙን የሚያናጋውን ከራሱ ነፃ ኅሊና ጋር የሚያጣላውን ሃይማኖቱንና የክርስትና ሕይወቱን የሚፈታተነውን ትእዛዝ እንዲቀበል የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም::

መንፈሳዊ መሪና አባትም የእግዚአብሔር እንደራሴ በመሆኑ የመንፈሳዊ ልጁን ውስጣዊ ሰላም የሚያናጋ መንፈሳዊ ቅድስናውን የሚያደፈርስና የሚፈታተን ተእዛዛ ማዘዝ የለበትም:: ይህን መሰሉ ሥራ አባታዊ አይደለምና::

ስለዚህ ታላላቆችንና መሪዎችን በሚገባ መጠን መታዘዝ እንጂ ማምለክ ከእግዚአብሔር ሊያጣላ የሚችል ትእዛዛቸውንም መቀበል አይገባም:: ታላቅነታቸው የልጆች መንፈሳዊ ሆነ አካላዊ ችግር የሚያቃልል እንጂ በራሱ ችግር መሆን የለበትም:: ይህም ከፍርሃት የተነሣ ወደ አምልኮ ሊለወጥ ይችላልና::

5. ዓለምንና የዓለምን ፍላጎት ማምለክ

ዓለም ሌላኛዋ ጣዖት ናት:: ከዓለም ጋር በፍቅር የተሳበረ ሁሉ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለእርሱም ያለውን ታዛዥነት እና እምነት ሁሉ ይረሳል ይተዋልም:: ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ በመልእክቱ «ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሐር ጥል እንዲሆን አታውቁምን? እንግዲህ የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ኾኗል::» በማለት ይህንን ገልጦታል:: ያዕ. 4-4:: ፍቁረ እግዚአ ቅዱስ ዩሐንስም በበኩሉ ይህንን በመጀመሪያው መልእክቱ አጉልቶታል:: «ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ:: በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለገንዘብም መመንት ከዓለም ስለሆነ እንጂ ከአባት ስላለሆነ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም:: የዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ:: የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላዓለመ ይኖራል::» 1ዩሐ. 2-15:17::

አንድ ጥያቄ ለራሳችን ኅሊና እናቅርብ:: የምናመልከው እግዚአብሔርን ወይስ ዓለምንና ፍላጎቷን? በእውነት እግዚአብሔርን የምናመልክ ከሆነ ዓለምን ድል መንሣት ይገባናል:: ፈቃዷም በእኛ ላይ መሠልጠን የለበትም:: ይህን አስመልክቶ ቅዱስ ዩሐንስ «ከእግዚአብሔር የተወለደው ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና ዓለምን የሚያሸንፈው እምነታችን ነው:: እንዳለ:: 1ዩሐ. 5-4:: የዓለም ፍላጎት ባሸነፈን ጊዜ ግን እምነታችን ከውስጣችን ፈጽሞ ይጠፋል:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ከባድ ፈተና «ዴቃስ የአሁኑን ዓለም ወድዶ ትቶኛልና » 2ኛ ጢሞ. 4-10 በማለት ተናግሮአል:: የሥጋ ፍትወታታ ሰዎችን ረግጠው የሚገዙ አማልክት ናቸው:: ለምኞታቸው የሚገዙ ሰዎችም እግዚአብሔርን በፍጹም ልባቸው በፍጹም ሐሳባቸው እና በፍጹም ኃይላቸው ያመልካሉ ማለት ያስቸግራል::

አንዳንድ ሰዎች የአካላቸውን ውበት ያመልካሉ:: ሁልጊዜም ስለ ውበታቸወ ቢናገሩ ይወዳሉ:: እነዚህ ሰዎች «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ» የሚለውን ቃል አማልክት አይሁኑልህ» የሚለውን ቃል አፍርሰዋል:: «ከላይ በሰማይ ካለው ከምድር በታችም በውኃ ካለው ነገር የማንኛውንም ምሳሌ የተቀረፀውንም ምስል ለአንተ አታድርግ» የሚለውን የእግዚአብሔርን ቃል መሻራቸው አይታወቃቸውም :: ለእነርሱ የሚታያቸው ድንጋይ ጠርበው እንጨት አለዝበው አለማምለካቸው ብቻ ነው:: ነገር ግን ማንም ቢሆን እግዚአብሔርን ብቻ ማምለክና ልቡናውንም ለእግዚአብሔር ብቻ አሳልፎ መስጠት እንጂ ራሱን እንደ ጣዖት ማምለክ የለበትም::

ሌሎች ደግሞ ትኩረታቸው ሁሉ መብል እና መጠጥ ላይ ብቻ ነው:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለእነርሱ «ሆዳቸው አምላካቸው ነው ክብራቸው በነውራቸው ነው ሐሳባቸው ምድራዊ ነው::» ፊልጵ. 3-19:: በማለት አስተምሯል:: ከዚህም በላይ እነርሱ የመስቀሉ ጠላቶች መሆናቸውንና ስለዚህም የሚያቀቅስላቸው መሆኑን ጨብሮ ተናግሯል:: በእርግጥ አንድ መስኪያ አረቄ አምላካቸው የሆነ ፈቃዳቸውም ሁሉ ወደመብልና መጠጥ ያዘነበለ ብዙ ሰዎች አሉ:: እሥራኤላውያንስ በአንድ ወቅት ስለሥጋ ዓሣ ዱባ በጢኽ ቀይ ሽንኩርት ነጭ ሽንኩርት አልቅ ሰው አልነበረም? ዘፍ. 11-4-5:: ኤሣውስ ብኩርናውን ከነበረከቱ ለበስር ወጥ አልሸጠምን? ዘፍ. 25-29:34:: አዳምና ሔዋንስ ለመብላት ያማረች ለዓይን የምታስጎመጅ ከሆነችው ዛፍ ፍሜ በመብላት በሰወ ሁሉ ላይ ርኩሰትንና ሞትን አምጥተው የለምን? ዘፍ. 3-6::

ቅዱሳን አበው ለጣዖት ከመንበርከክ ይልቅ ሰማዕትነትን ይመርጡ እንደነበር ገድላቸው ይነግረናል:: የዘመኑ ትውልድ ደግሞ በተቃራኒው በየቀኑ ለጣዖት መሥዋዕት ሲያሳርድ ይውላል:: የዘመኑ ሰው በየቀኑ የሚሠዋላቸው እነዚህ ጣዖታትም ገደብ የሌላቸው የሥጋው ፍላጎቶች የዓይኑ አምሮቶች ናቸው::

ሥልጣንን ማዕረግን ክብርን የተለያዩ ንብረቶችን እንደ አምላክ የሚመካባቸው እና ፍላጎቶቹ ሲል ፈጣሪው እግዚአብሔርንና ኅሊናውን ይሸጣል:: «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ» የሚለውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ወደ ጎን

በመተውና በመዘንጋት ፍላጎቱን ለቋፈጸም አስፈላጊ ነው ያለውን መሥዋዕትነት ሁሉ ከመክፈል ወደኃላ አይመለስም:: ለዚህም መድኃኒቱ ለሥጋዊ ፍላጎት ከመገዛትና እርሱንም ከማምለክ መራቅ ነው::

6. ራስን ማምለክ

ከጣዖታት ሁሉ የበለጠውና አደገኛው ራስን ማምለክ ነው:: ሰው ከሥጋዊ ፍላጎቱ ማየል የተነሣ ሁልጊዜ ራሱን ከፍ ከፍ ለማድረግ ይፈልጋል:: በዚህ ደግሞ ራሱን ማምለክ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም እንዲያመልኩት እርሱነቱ በሁሉም ዘንድ እንዲገን እንደከብርና እንዲፈራ ይሻል:: ሰዎች መልካምና ያማረ ነው የሚሉት ሁሉ በእርሱ ማንነት ውስጥ እንዲገኝና ሰዎችም ሁሉ እንዲያደንቁት ይፈልጋል::

እስቲ አንድ ጥያቄ እናንሣ:: ሐዋርያው ያዕቆብን ባስገደለው በንጉሥ ሄሮድስ ላይ አደጋ ያመጣበት ምንድን ነበር? የእግዚአብሔር መልአክስ ለምን ቀሰፈው? ለምንስ በትል ተበልቶ ሞተ? ሰዎች እንደ አምላክ የማይገባውን ክብር ሲሰጡት ባለመታወሙና የማይገባውን ክብር በመሻቱ አልነበረምን? የሐዋ. 12-21:23::

ቀደም ብለን የጠቀስናቸውን ጣዖታት ሁሉ ድል ነሥተው ነገር ግን ራስን ማምለክን ማሸነፍ የተሣናቸው ሰዎች የሄሮድስ መሰሎች ናቸው:: ይህን የመሰሉት ሰዎች ከራሳቸው በቀር ሌላ አስተዋይ የተሻለ ጠቢብ የደመቀ ያማረ አለ ብለው ስለማያምኑ ራሳቸውን ያመልካሉ:: ሰውም እንዲያመልካቸው ይሻሉ:: ለዚህ ዓይነቱ ሰው የእርሱ ማንነት እርሱ ብቻ የሚያውቀውና በእርሱ አእምሮ የተሣለው እርሱነቱ ብቻ ነው:: በምኞት ብቻ የቀረ ማንነት:: ለእርሱ እንደሚመስለው ከእርሱ በቀር ሁሉም ስህተተኛ ነው:: ከሌሎች ጋር ቢጋጭ እንኳ እነርሱ እንጂ እርሱ እንዳልሳሳት ያምናል:: ምክንያቱም በፍጹም ስህተት አይሠራምና:: «ሰዎች ሊረዱኝ አይቻሉ እንጂ የእኔ ጠባይ ትክክለኛ ነው» የሚል የራሱ እምነት አለው::

በዓለም ላይ የሚነሡትና የተነሡት አምባገሮዎች በአብዛኛው ራስን የማምለክ ውጤቶች ናቸው:: በመሆኑም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ከመሰለው አምልኮ እንድንጠበቅ እንዲህ ብሏል «በኃላዬ ሊመጣ የሚወድ ማንም ቢኖር ራሱን ይካድ» ማር. 8-34::

ራስን መካድ ምን ማለት ነው? ሰው ራሱን ማምለክን ከልቡናው ያጥፋ ራሱን አመድ የምድርም ትቢያ እንደሆነ ይመን ማለት ነው:: ነገር ግን ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር እንደጣላና ከአምላኩ ጋር እንዲፎካከር ከሚያደርጉት ነገሮች አንደኛው የራሱን ታላቅነትና ከሁሉ በላይ መሆኑን መሻቱ ሲሆን ሁለተኛው ራሳችንን መውደዳችን አይደለምን? ፍላጎታችን ከእግዚአብሔር ትእዛዛት ጋር በሚጋጭበት ጊዜ ፈቃዳችንን ከቋፈጸም ይልቅ « እርሱ ፈቃዳችንን ከመፈጸም ይልቅ «እርሱ እግዚአብሔር ሊልቅ እኔ ላንስ ያስፈልጋል» ዮሐ. 3-30:: ያልን እንደሆነ ያንጊዜ ራሳችንን እንደንድን በዚህ ይታወቃል:: በእርግጥም ራሳችንን እንድናመልክ ይሚያደርገን ደግሞ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የሚጋጩ የተወሰኑ ፍላጎቶችን ለማሟላት ያለን ዓላማ ነው::

የመላእክት አለቃ የነበረውን ሳጥናኤልን ለመውደቅ ያበቃው ምንድነው? ራሱን የሁሉ የበላይ ማድረጉ አይደለምን? ምክንያቱም የተሰጠውን ትቶ ከሚገባው በላይ ታላቅና ክፍ ያለ ለመሆን ሽቷልና:: እናም እንዲህ ብሏል:: «ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ ዙፋኔንም ከእግዚእብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ ከደመናዎች ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ ከደመናዎች ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ በለዐልም እመሰላለሁ::» ኢሳ. 14-13-14:: ሳጥሀኤል እንደ እግዚአብሔር ለመሆኝ ከፍ ከፍ ማለትን ፈለገ:: ነገር ግን ትዕቢቱ ውርደትን እንጂ ክብርን አላስገኘለትም:: አዳምና ሔዋንን ባሳታቸውም ጊዜ በተመሳሳይ ፈተና ነበር ያታለላቸው:: ዘፍ. 3-5

ስለዚህ ማንም ሰው እራሱን መግዛትና መካድ ከቻለ ዋነኛውን ጣዖት ከልቡናው አጠፋ ማለት ነው::

አሥራትን ለእግዚአብሔር ከመስጠት ይልቅ ለራሳችን ስንወስድ ሰንበትን ለሥጋዊ ፈቃድ መፈጸሚያ ስንጠቀም ራሳችንን መውደዳች አይደለምን? ፍላጎታችን ከእግዚአብሔር ትዕዛዝ ጋር በሚጋጭበት ጊዜ ፈቃዳችንን ከቋፈጸም ይልቅ« እርሱ እግዚአብሔር ሊልቅ እኔ ላንስ ያስፈልጋል» ያልን እንደሆነ ያን ጊዜ ራሳችንን በመካድ ሕይወታችንን ለዘለዓለም እንደምንጠብቃት እርግጠኞች እንሆናለን:: ራስን ከማምለክ ነፃ እንድንወጣ ራሳችንን ለመካድ የሚያበቃ የጸጋ ስጦታን የሚያድል መድኃኔዓለም ክርስቶስ በቸርነቱ እመቤታችንን ቅድስት ድንግል ማርያም በአማላጅነቷ ይርዱን:: አሜን::

## ሁለተኛው ትእዛዝ

## «የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ»

እግዚአብሐር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና።» ዘጸ. 20-7።

ይህ ሁለተኛው ትእዛዝ ደግሞ የሚያተኩረው በስመ እግዚአብሔር ላይ ነው። ስለሆነም ስመ እግዚአብሔርን አስመልክቶ ጥቂት ነገር መነጋገር ያስፈልጋል ብለን እናምናለን።

**የአምላካችን ስም ቅዱስ ታላቅና ድንቅ ነው፡-**

ከዚህ የተነሣም የአምላካችን ስም እንደማንኛውም ሰው ስም በልማድ የምንጠራው አይደለም። በመኃልየ መኃልየ «ዘይትና መልካም መዐዛ አለው ስምህም እንደሚፈስ ዘይት ነው» እንደተባለለት ስሙን ስንጠራ ባማረ ቃልና በአክብሮት ነው። መኃ. 1-3። አምላክን የወለደች በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም «ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ ነገር አድርጓልና ስሙም ቅዱስ ነው።» በማለት ምስክርነቷን ሰጥታለች። ሉቃ. 1-49። አባቷ የሚሆን ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊትም የስመ እግዚአብሔርን ቅድስና ሲናገር «ስሙ የተቀደሰና የተፈራ ነው።» ብሏል። መዝ 110-9። የእግዚአብሔር ስም ቅዱስ ስለሆነ ነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ ባስተማረው ጸሎት «ስምህ ይቀደስ » እንድንል የነገረን። ማቴ. 6-9። እኛም ታዲያ የእግዚአብሔርን ቅድስና በምናስታውስበት ጊዜ ሁሉ ክብርና መፈራት የሚገባውን ስሙን «ስምህ ይቀደስ » ልንጠራው ይገባናል። የፈጣሪያችንን ስም በመፍራትና በመንቀጥቀጥ መጥራት እግዚአብሔርን ከሚፈራና ከሚወድ ከሚያከብረውም ትሑት ልብ የሚመነጭ ፈሪሃ እግዚአብሔር በውስጣችን መኖሩ ከሚታወቀውም ለቅዱስ ስሙ ከምንሰጠው ፍቅር የተሞላበት አክብሮት ነው።

ካህናተ ሰማይ የሆኑ ሱራፌልም «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች» እያሉ ያመሰግናሉ። ይህም ስሙን የሚጠሩት ጌታ የሚፈሩት የሚያከብሩትና የሚገዙለት ቸርና ቅዱስ አምላክ በመሆኑ ነው። ይህን ታላቅና ቅዱስ ስመ አምላክ በሚጠሩ ጊዜም «በመፍራትና በመንቀጥቀጥ ከመንበሩ ፊት ቆመው በክንፎቻቸውም ፊቶቻቸውንና እግሮቻቸውን ሸፍነው ነው።» በዚህን ጊዜም «ከድምፃቸው የተነሣ የመድረኩ መሠረት ይናወጣል ቤቱንም ጢስ ይሞላበታል። ይህን ግሩም ራእይ የተመለከተ ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስንም «እኔም ከንፈሮቹ የረከሱብኝ ሰው በመሆኔ ዓይኖቼ እግዚአብሔርን ስላዩ ጠፍቻለሁና ወዮልኝ» እንዲል አድርጎታል። ኢሳ. 6-1:5።

ሱራፌል በመፍራትና በመንቀጥቀጥ የሚጠሩትን ይህን ቅዱስ ስም አርባዕቱ እንስሳም በመንበሩ ፊት ቆመው ያለ አንዳች ዕረፍት «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የነበረውና ያለው የሚመጣው ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ» በማለት የሚያመሰግኑት መሆኑን ሐዋርያው ቅዱስ ዩሐንስ በራእዩ መዝግቦታል። ራእ. 4-8:10። ከፍጹም ክብሩና ከቅድስናው የተነሣም «በዙፋን ላይ ለተቀመጠው ምስጋናም ባቀረቡለት ጊዜ ሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ በዙፋን ላይ በተቀመጠው ፊት ወድቀው ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም በሕይወት ለሚኖረው እየሰገዱ በዙፋኑ ፊት አክሊላቸውን ያኖራሉ።» ራእ. 4-11።

ነቢዩ ሚልኪያስ «የአምላካችን ስም ቅዱስ ነው። ስሙም በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ነው።» በማለት ተናግሮለታል። ኤር 10-6 ኢያሱ ወልደነዌም በበኩሉ « ለታላቁ ስምህም የምታደርገው ምንድነው?» ያለ ሲሆን ኢያ. 7-9። ነቢዩ ቅዱስ ዳዊት ደግሞ «የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የእሥራኤል አምላክ ነው ይባል ዘንድ ስምህ ለዘለህለም ታላቅ የሁን» በማለት ዘምሯል። 2ሳሙ 7-36። ነቢዩ ኤርምያስም በሌላ ሥፍራ «ተቤዢአቸው ብርቱ ነው ስሙም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው።» ብሏል። ኤር. 50-34። እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው ጥቅሶች ሁሉ ስለ ስሙ ቅዱስነት እና ታላቅነት በቅዱሳን አበው የተሰጠ ምስክርነት ነው። ከዚህም ሌላ ነቡዩ ኢሳይያስ ስለወልደ እግዚአብሔር ልደት በተናገረው ትንቢት «ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ የዘለዓለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል» ማለቱ የአምላንችን ስም ቅዱስ ብቻ ሳይሆን ታላቅና ድንቅ መሆኑንም የሚያስረዳ ነው። ኢሳ. 9-6።

ይህ ስም ቅዱስ ታላቅ ድንቅና መልካም መሆኑን ከተረዳን ዘንዳ« የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና» የሚለውን የፈጣሪ ትእዛዝ መዘንጋት የለብንም። የዚህ ትእዛዛ

መስጠት ዋና ዓላማም ቅዱሳን መላእክት እንኳ በመፍራትና በመንቀጥቀጥ የሚጠሩትንና የሚገዙለትን ቅዱስ ስም በማክበር እኛም በትህትና እና በክብር ልንጠራው ይገባል::

የእግዚአብሔር የአምላካችን ስም ድንቅ ተአምራትን ያደርጋል:: ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በቤተመቅደስ ደጃፍ ተቀምጦ ይለምን ለነበረው ሰው የሰጠው መልስ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው:: «ብርናወርቅ የለኝም ይህን ያለኝን ግን እሠጥኻለሁ በናዝሬቱ በኢየሱስ ስም ተነሣና ተመላለስ ባለው ጊዜ ተነሥቶ ሊመላለስ ችሏል:: የሐዋ. 3-6:: በዘህን ጊዜ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ የአምላካችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ከመጥራት በቀር ያደረገው አንዳችም ነገር አልነበረም:: ሽባውን የተረተረው ተነሥቶም እንዲመላለስ ያደረገው ይህ ቅዱስ ስም ነው:: ይህን የተመለከቱት የአይሁድ ሊቃነ ካህናት ቅዱስ ጴጥሮስንና ቅዱስ ዩሐንስን ይዘው በመካከል ከአቆሙአቸው በኃላ «በምን ኃይል ወይስ በማን ስም እናንተ ይህን አደረጋች?» በማለት በጠየቋቸው ጊዜ «እናንተ በሰቀላችሁት በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው::» በማለት ቅዱስ ጴጥሮስ የሰጠው መልስ እውነተኛ የሆነው ድንቅና ተአምራት ሁሉ ሊደረግበት በሚችለው በእግዚአብሔር ስምና በእርሱም ኃይል መሆኑን የሚያስረዳ ነው:: የሐዋ 4-7:8:: አባቶቻችን ሐዋርያትም «አሁንም ጌታ ሆይ ለመፈወስም እጅህን ስትዘረጋ በቅዱስ ልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ምልክትና ድንቅ ሲደረግ ባሮችህ ቃልህን በፍጹም ግልጥነት እንዲናገሩ ስጣቸው» በማለት እዚአብሔርን በጸሎት መጠየቃቸው ለዚህ ነው:: የሐዋ 4-29:30::

ይሁን እንጂ እኛ ባለንበት ዘመን ይህን መነሻ በማድረግ በስሙ ልዩ ልዩ ተአምራትን እናደርጋለን የሚሉ መናፍቃን በምትሐታዊ ተአምራት የዋሆችን የሚያሞኙ ስለሆነ እጅግ መጠንቀቅ ያስፈልጋል:: ስለ እነዚህም ጌታችን በወንጌል «ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም:: በዚያ ቀን ብዙዎች ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ በስምህ ብዙ ተአመራት አላደረግንምን? ይሉኛል:: የዚያን ጊዜም ከቶ አላወቅኋችሁም እናንተ ዓመፀኞች ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ::» ሲል ተናግሮባቸዋል:: ማቴ. 6-21:23::

የአምላካችን ስም ለአጋንንት አስፈሪና አስዳንጋጭ ነው

በቅዱስ ወንጌል እንደተጣፈው «ሰባ ሁለቱም በደስታ ተመልሰው ጌታ ሆይ አጋንንት እንኳ በስምህ ተገዝተውልናል አሉት »የሚለው ቃል ስሙ አጋንንትን የሚያስደነግጥ መሆኑን የሚያመለክት ነው:: ሉቃ 8-17:: ይህን ከላይ የተጠቀሰውን ቃል የተናገሩት ሰባ ሁለቱ አርድእት ለተላኩበት አገልግሎግ አዲሶች ቢሆኑም በእግዚአብሔር ስም አጋንንትን የማውጣት ሥልጣን ተሰጥቷቸው እንደነበረ ካከናወኑት ተግባር ለመረዳት እንችላለን:: ይህንን ጸጋ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስትስ ከትንሣኤው በኃላ በተናገረው ቃሉ «ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል:- በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ» በማለት አጽንቶታል:: ማር 16-17::

ቅዱሳን ሐዋርያት ሁሉ በዚህ ቃል ኪዳን መሠረት አጋንንትን ሲያወጡ እንደነበር በቅዱስ መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኛል:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በፊልጵስዩስ ሀገር በአጋንንት መንፈስ በመታገዝ እየጠነቆለች ለጌቶቿ ገንዘብ ታስገባ የነበረችውን ሴት ከአደረባት ጋኔን መፈወሱ ለዚህ አንዱ ማስረጃ ነው:: በሴቲቱ ያደረውን ርኩስ መንፈስም «ከእርሷ እንድትወጣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝዤኻለሁ አለው:: በዚያም ሰዓት ወጣ::» የሐዋ. 16-18:: ይህም የእግዚአብሔር ስም ሲጠራ የአጋንንት ሠራዊት ሁሉ የሚንቀጠቀጡ መሆኑን የሚያሳይ ነው:: ቅዱሳንም በዚህ መልክ ነው አጋንንትን በስመ እግዚአብሔር ሲያንቀጠቅጧቸው የኖሩት ዛሬም ቢሆን ይኸው የእግዚአብሔር ቅዱስ ስም አጋንንትን የሚያንቀጠቅጣቸው መሆኑን በየቅዱሳት መካናቱ የጠበል ቦታዎች በማየት የምናደንቀውና የምናስተውለውም ነው::

የአምላካችን ስም በችግር ጊዜ መጠጊያ ነው

ጠቢቡ ሰሎሞን በመጽሐፍ ምሳሌ «የእግዚአብሔር ስም የጸና ግምብ ነው ጻድቅ ወደእርሱ ሮጦ ከፍ ከፍ ይላል » ሲል የተናረው ቃል ስመ እግዚአብሔር የምንመካበት የምንሸሸግበትና ከፍ ከፍ የምንልበት መሆኑን የሚያስረዳ ነው:: ምሳ. 18-8:: ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት ደግሞ ይህንን በተግባር ስለአየውና ስለአረጋገጠው «አሕዛብ ሁሉ ከበቡኝ በእግዚአብሔር ስም አሸነፍኳቸው በማለት ተናግሯል:: መዝ. 117-10::ከዚህ ቀደም ብሎም በተመሳሳይ አነጋገር «በአንተ ጠላቶቻችንን እንወጋቸዋለን በስምህም በላያችን የቆሙትን እናዋርዳቸዋለን» ሲል የተናገረው የእግዚአብሔር ስም በችግር ጊዜ መሣሪያ መሆኑን ስለሚያውቅ

ነው:: መዝ 43-5:: በሌላ ስፍራ ደግሞ «አቤቱ በስምህ አድነኝ» በማለት የለመነው ልመና የእግዚአብሔር ስም ከጭንቅ እና ከመከራ የሚያድን መሆኑን የሚያስረዳ ነው:: መዝ. 53-1::

አምላካችን እግዚአብሔር ሁል ጊዜ በቅዱስ ስሙ እንድንታመን ይፈልጋል:: በነቢዩ በኢሳይያስ አድሮ «በእግዚአብሔር ስም የሚታመን በአመላኩም የሚደገፍ ማነው?» ሲል የጠየቀው ጥያቄ ይህንኑ ፈቃዱን የሚገልጥ ነው:: ኢሳ 50-10:: ይህ አባባል የሰው ዘር ሁሉ መታመኛውና መመኪያው የአምላካችን ስም ሊሆን እንደሚገባ የሚያስገነዝብ ነው:: በዘመናችን ግን ሰዎች ከስመ እግዚአብሔር ሌላ ኃላፊና ጠፊ በሆነ በዚህ ምድር ሀብትና ንዋይ በሥልጣንና በዘመድ አዝማዶቻቸው ሲታመኑ ይታያሉ:: እንዲህ ዓይነቱም ትምክህት ከንቱና የማይጠቅም ነው:: እግዚአብሔር በነቢዩ በሶፎንያስም አድሮ « በመካከልሽ የዋህና ትሑት ሕዝብን አስቀራለሁ በእግዚአብሔርም ስም ይታመናሉ» በማለት የተናገረው ቃል በሌላ ማለትም በሚጠፋና በሚያልፍ ነገር መመካት እንደማይገባ የሚያስተምር ነው:: ሶፎ. 3-12:: ነቢዩ ዳዊትም በመዝሙሩ «ነፍሳችን እግዚአብሔርን ተስፋ ታደርጋለች ረዳታችንና መጠጊያችን እርሱ ነውና ልባችን በእርሱ ደስ ይለዋልና በቅዱስ ስሙም ታምነናልና» ብሏል:: መዝ. 32-20:21::

የአምላካችን ስም ጸጋን የምናገኝበት ነው

በቤተክርስቲያናችን የልጅነት ጸጋ የሚገኘው በስመ ሥላሴ ምሥጢረ ጥምቀት በሚፈጸምበት ጊዜ ነው:: ማቴ. 28-19:: የተቀሩትም ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን የሚፈጽሙት በዚሁ ዓይነት በአምላካችን ስም «በእግዚአብሔር » ነው ለምሳሌ ስለ ምሥጢረ ቀንዲል የተጻፈውን ብንመለከት «ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተክርስቲያንን ሽማግሌዎች /ካህናትን/ ወደ እርሱ ይጥራ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸለዩለት::» ይላል ያዕ. 14:: ካህኑም ምእመናንን የሚባርከው የአምላክን ስም በመጥራት ነው:: ዘኍ 6-24:26:: በአጠቃላይ የጸጋው ግዳጃ ቤት በሆነች ቤተክርስቲያን የሚሠራው ሥራ ሁሉ የሚከናወነው ቅዱስ ስሙን በመጥራት መሆኑን መገንዘብ ይገባል::

ለስም አጠራሩ የሚገባው ክብር

ይህ ቅዱስ ስም የፈጣሪያችን ስም በመሆኑ በክብር ልንጠራው ይገባል:: ነቢዩ ሙሴ «አምላክህ እግዚአብሔር የተባለውን የተመሰገነውንና የተፈራውን ስም ባትፈራ » በማለት ያስጠነቀቀው ለዚህ ነው:: ዘዳ. 28-58 ስሙን የሚፈሩና የሚያከብሩትም የሚገባቸውን መንፈሳዊ ዋጋ ያገኛሉ:: ይህንን በተመለከተ በራእይ« ለባሪያዎችህ ለነቢያትና ለቅዱሳን ስምህንም ለሚፈሩት ለታናናሾችና ለታላላቆችም ዋጋቸውን ትሰጥ ዘንድ» የሚል ተጽፏል:: ራእ. 11-18::

ቅዱሳንና ንጹሐን የሆኑ የሰማይ ሠራዊት በመፍራትና በመንቀጥቀጥ የሚጠሩትን ቅዱስ ስም በታላቅ ትሕትና ሆነን «የተቀደሰ ስምህን ኃጢአት ባረከሰው አንደበታችን መጥራት የሚገባን አይደለም::» እያልን በክብር ልንጠራው ያስፈልጋል:: ነቢዩ ቅዱስ ዳዊትም «በእግዚአብሔር ከእኔ ጋር ታላቅ አድርጉት በአንድነትም ስሙን ከፍ ከፍ እናድርግ» በማለት ሰው ሉ የእግዚአብሔርን ስም ከፍ ባ ክብር እንዲጠራው አስተምሯል:: መዝ 33-3::

የአምላካችን የእግዚአብሔር ስም የከበረና ቅዱስ ሲሆን በተራ ነገር ሁሉና በየአጋጣሚው ልንጠራው አይገባም:: መክንያቱም በሆነውም ባልሆነውም ስሙን የምንጠራ ከሆነ ይህ ተግባራችን ወደልማድነት ይለወጥና ለስሙ የሚገባውን ክብር ወደመዘንጋት እና ፍቅሩን ወደማጣት ሊያደርስ ይችላል:: ከዚህ ይልቅ ስሙን ልንጠራ የሚገባው በጸሎት ጊዜ ከቸርነቱ ስንለምንና ስለ በጎነቱ ስናመሰግነው መሆን እንዳለበት የእግዚአብሔር ባለሟል የሆነው ቅዱስ ዳዊት «በቅዱስ ስሙ ተጓደዱ» መዝ 104-3 «ለልሁል እግዚአብሔር ስም እዘምራለሁ» በማለት የተናገራቸው ሐረጎችም የሚየስረዱት የእግዚአብሔርን ስም እንዴት ባለ ጊዜና ሁኔታ እንደምን ባለ ክብርም ልንጠራው የሚገባ መሆኑን ነው:: መዝ 7-17::

በመዘመር በምናመሰግንበትና በመጸለይ እርሱን በምንለምንበት ጊዜ ሁሉ እርሱ ከእኛ ጋር መሆኑን በማሰብ ቅዱስ ስሙን በትህትና ልንጠራው ይገባናል:: እርሱ ራሱ በቃሉ «ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በስሜ በተሰበሰቡት በዚያ እኔ ደግሞ በመካከላቸው እሆናለሁ» በማለት የተናገረወ ይኸንኑ የሚያረጋግጥ ነው:: ማቴ. 18-20::

ፍጹም የሆነው ልባዊ ፍቅርና እውነተኛው አክብሮት ሳይኖር የእግዚአብሔርን ስም በልማድ ብቻ መጥራት ተገቢ አይደለም:: የእግዚአብሔርን ስም መጥራታችንና ጸሎታችን ሁሉ ለታይታና የክብር ወንበር ለማግኘት ይደክሙ ከነበሩ ጻፎችና

ፈሪሳውያን የተለየና የሚበልጥ መሆን አለበት:: ሉቃ.20-47:: በልቡናቸው የእግዚአብሔር ፍቅር ሳይኖር በሰዎች ፊት ለመታየት ብቻ ብለው የሚጸልዩና የከበረ የእግዚአብሔርን ስም የሚጠሩ ሰዎች ሁሉ በዚህ ከንቱ ተግባራቸው ሌሎችን ያሰናክሉበታል እንጂ የሚያገኙት መንፈሳዊ ጸጋ የለም:: ከዚህ የተነሣም ሰዎች ጸሎትንና የእግዚአብሔርንም ስም እንደከንቱ ነገር ይቆጥሩታል:: ስለዚህ በእነርሱ ኃጢአት ምክንያት የአምላክን ስም የሚያሰድቡ ሁሉ መቀጣታቸው ስለማይቀር ከዚህ መሰሉ ድርጊት መቆጠብ ይገባቸዋል::

በጸሎት የጀመሩትን መንፈሳዊ ስብሰባ በጭቅጭቅ የሚዘጉ በመንፈስ የጀመሩትን በሥጋ የሚፈፅሙ የጸሎትን ዓላማና የእግዚአብሔርን ስም ክብር የሚያቃልሉ ሰዎችም ሁሉ ስሙን በከንቱ ከሚጠሩት ጋር የሚመደቡ ናቸው::

በአጠቃላይ የፈጣሪያችን ቅዱስ ስም የከበረ ኃይል በረከትና ጸጋን የምናገኝበት ከክፍ የአጋንንት ፈተና የምንጠበቅበት በመሆኑ ለስም አጠራሩ ክብርን መስጠት ይገባናል:: በማይገባ ሥፍራና አጋጣሚ ሁሉ በልማድ ብቻ ቅዱስ ስሙን በማንሣት ክርስቲያን መስሎ ለመታየት መሞከሩ ምንም ጥቅም አይኖረውም:: የተከበረ ስም አጠራሩን ከክርስቲያናዊ ምግባር ጋር አዋሕዶ መገኘት ግን በረከትን ያስጣል::

## *ሦስተኛ ትእዛዝ*

## ሰንበትን አክብር

*የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ ስድስተኛ ቀን ሥራ ተግባርህንም ሁሉ አድርግ ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር አምላክህ ሰንበት ነው:: አንተ ወንድ ልጅህም ሴት ልጅህም ሎሌህም ገረድህም ከብትህም በደጆችህም ውስጥ ያለ እንግዳ በእርሱ ምንም ሥራ አትሥሩ:: እግዚአብሔር በስድስት ቀን ሰማይንና ምድርን ባሕርንም ያለባቸወንም ሁሉ ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን አርፏልና ስለዚህ እግዚአብሔር የሰንበት ቀን ባርኮታል ቀድሶታልም:: ዘዳ 3:10-11*

### የሰንበትን ቀን ትቀድስ ዘንድ አስብ

ይህ ትእዛዝ አሥርቱ ትእዛዛት ከመጻፋቸው በፊት እግዚአብሔር ራሱ አብነት በመሆን ሕዝቡ እንዲጠቀሙበት ለእሥራኤል የሰጠው ቀዳማዊ ትእዛዝ ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርም ሰባተኛውን ቀን ባረከው ቀደሰውም እግዚአብሔር ሊያደርገው ከፈጠረው ሥራ ሁሉ በእርሱ አርፏልና በማለት የተናገረው ቃል ይህን ቀዳማዊ ትእዛዝ እግዚአብሔር ለዕረፍት የሠራልን ሕግ መሆኑን የሚያስረዳ ነው:: (ዘፍ 2:3) እግዚአብሔር ዓለምንና በውስጧ ያሉትን ፍጥረታት ከፈጠረባቸው ዕለታት ሁሉ በተለየ ክብር የሰንበትን ቀን ባርኮታል:: ቀድሶታልም:: ሌሎቹን ቀናት ግን እርሱ ሠርቶባቸው ለሥራ ሰጥቶናል በመሆኑም በእግዚአብሔር ተባርኮና ተቀድሶ የተሰጠንን ዕለተ ሰንበትን ልናከብረው ይገባናል::

### ሰንበትን የማክበር ትእዛዝ መቼ ተሰጠ?

ሰንበትን ማክበር ከአሥርቱ ትእዛዛት በፊት የነበረ ነው:: ይህም ይታወቅ ዘንድ እግዚአብሔር የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስበው ብሏል:: በዚህም እሥራኤል ቀድሞ የሚያወቁትን ትእዛዝ እንዲያስታውሱት አድርጓል:: እግዚአብሔር አሥርቱን ትእዛዛት በሕግ መልክ ከመስጠቱ አስቀድሞ በነቢዩ በሙሴ አማካኝነት እግዚአብሔር የተናገረው ነገር ይህ ነው ነገ ዕረፍት ለእግዚአብሔርም የተቀደሰ ሰንበት ነው የምትጋግሩትን ጋግሩ የምትቀቅሉትም ቀቅሉ የተረፈውንም ሁሉ ለነገ እንዲጠበቅ አኑሩት በሰባተኛው ቀን ማንም ከሥራው አይሂድ ... ሕዝቡም ሰባተኛው ቀን ዐረፉ:: በማለት ለሕዝበ እሥራኤል የነገራቸው ቃል ይህ ተእዛዝ ቀደም ብሎ የሚታወቅ መሆኑን ያስረዳል:: ዘጸ 16:23-30:: እንግዲህ ከፍ ብለን እንደተመለከትነው ሰንበትን የማክበር ትእዛዝ ከሕግ አስቀድሞ በሥነ ፍጥረት መጨረሻ ላይ የተሰጠ መሆኑን አረጋግጠናል:: ይህም የሚያስረዳው ከአሥርቱ ትእዛዛት አንዱ ክፍል ሆኖ ከቋስጠቱ አስቀድሞ ሰንበትን ማክበር በእሥራኤል ዘንድ የሚታወቅና በሥራም ላይ የነበረ መሆኑን ነው::

### ሰንበትን አለማክበርና ቅጣቱ

አንዳንድ ሰዎች ይህን ትእዛዝ አትግደል አታመንዝር አትስረቅ ወዘተ ከሚሉት ትእዛዛት ያነሰ ክብደት ይሰጡታል:: ይሁን እንጂ ከእነዚህ ከተጠቀሱት ትእዛዛት ያላነሰ መሆኑ በመጽሐፍ ሰባተኛው ቀን ለእግዚአብሔር የተቀደሰ የዕረፈት ሰንበት ነው በሰንበት ቀን የሚሠራ ሁሉ ፈጽሞ ይገደል:: ሲል በተናገረው ቃል ይታወቃል:: ዘጸ 31:15:: ስለዚህ ሰንበት መሻር ቀላል ኃጢአት አይደለም:: ቅጣቱም ከባድ ነውና ለዚህም ይህ ቅጣት የተፈጸመበት አንድ ሰው ታሪክ በቂ ማስረጃ ሊሆን ይችላል:: ዘኁ 15:32-36

ነቢዩ ሕዝቅኤልም ሰንበትን ስለሚሽሩ ሰዎች ብዙ ጊዜ ተናግሯል:: ከእነዚህም እግዚአብሔር ልጆች ግን አመፁብኝ... በሥርዓቴም አልሄዱም ሰንበታቴንም አረከሱ:: በዚህም ጊዜ መዓቴን አፈስባቸዋለሁ:: ይላል በማለት የተናገረው ይገኝበታል:: ሕዝ 20:21

ዛሬ ዛሬ ግን ብዙቻዎች ሰንበትን ማክበር እንደሞኝነትና ሥራ ፈትነት በመቊጠር ሰንበትን በሚያከብሩ ክርስቲያኖች ላይ ሲሳለቁ ይስተዋላሉ:: በዚህ ዘመን ሰንበትን ባለማክበሩ የሚገደል በድንጋይም የሚወገር ከመንደር ወጭም የሚጣል ላይኖር ይችላል:: ነገር ግን ሰንበተን በማክበር የሚገኘውን በረከት ማጣት እንዳለ ግን ማስተዋል ያስፈልጋል:: ስለሆነም በግድ የለሽነት በጭፍን አስተሳሰብ እየተነዳን ትእዛዘ እግዚአብሔርን ከመሻር በመቆጠብ የእግዚአብሔርን የተቀደሰ ሰንበት በማክበር ራሳችንን ከቅጣት ማዳን ይኖርብናል::

## ስለ ሰው ደካማ ባሕርይ እግዚአብሔር ሰንበትን ሠራልን::

ነቢዩ መሴ እግዚአብሔር ሰንበትን እንደሰጣችሁ እዩ ሲል የተናገረው ሰንበት የእግዚአብሔር ስጦታ እንጂ በሰው ላይ የተጫነ ሸክም አለመሆኑን የሚጠቁም ነው:: ይህ ሰባተኛው የዕረፍት ቀን ለሰው መሰጠቱም ሰው በባሕርዩ ደካማ ከመሆኑ የተነሣ ማረፍ ስለሚያስፈልገው ነው:: ስለዚህም ሰንበት ሕግ ሆኖ ከመሰጠቱ ለሰው ልጅ ጥቅም መሆኑን አናስተውላለን:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰንበት ለሰው ተፈጥሯል እንጂ ሰው ለሰንበት አልተፈጠረም በማለት ያስተማረው ትምህርት ይኸንኑ የሚያረጋግጥ ነው:: ማር 2:27 የእግዚአብሔር ሕግ ለሁሉም እኩል ነው:: ጌታው ዐርፎ ሎሌው ቢሠራ አግባብ አይደለም:: አእሩግ አርፈው ወራዙት መሥራታቸውም ትክክል አይሆንም:: ሰንበት ለሁሉም የሰው ዘር የተፈጠረች በመሆኗ ሁሉ የዐርፉ ዘንድ ይገባቸዋል:: በእርሱ ምንም ሥራ አትሥሩ አንተ ልጅህም ሎሌህም በሬህም አህያህም ከብትህም አንተም በግብጽ ባሪያ እንደነበርህ አስብ ተብሏል:: ዘዳ 5:14-15:: እንስሳትም ድካም የሚስማማው አካል አላቸውና ማረፍ አለባቸው :: ዘጸ 23:12 :: እግዚአብሔር በሰንበት አማካይነት ዕረፍት የሰጠው ለግዑዙ መሬትም ጭምር ነው:: እርሱ ስድስት ዓመት ምድርህን ዝራ ፍሬዋንም አግባ ሰባተኛው ዓመት ግን ተዋት አሳረፋትም ብሏልና:: ዘጸ 23:10::

እንግዲህ ሰንበት በእግዚአብሔር ቸርነት ከሥጋ ድካማችን እናርፍበት ዘንድ የተሰጠች ጸጋ መሆኗን አውቆ በሚገባ ማክበር ይገባል:: ሰንበትን ብናከብር በአካልም በመንፈስም እንጠቀማለን:: ከሁሉም በላይ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት እንባረካለን:: እርሱ ፈጣሪያችን እዳያረክሱት ሰንበቴን የሚጠብቁትን ቃል ኪዳኔንም የሚይዙትን ሁሉ ወደ ተቀደሰው ተራራዬ አመጣቸዋለሁ... የማይጠፋ የዘለዓለም ስም እሰጣቸዋለሁ በማለት ተናግሯልና:: ኢሳ 56:2-7:: ስለዚህ ለበረከት የተሰጠንን ሰንበት በማክበር ትእዛዙን ለመፈጸም መትጋት ያስፈልጋል::

## ሰንበት የዘለዓለማዊው ዕረፍት ምሳሌ ነው::

አምላካችን እግዚአብሔር እንደተናገረው ሁሉ ዕለተ ሰንበት የዘለዓለማዊው መንፈሳዊ ዕረፍት ምልክት እንዲሆን የተሰጠ ጸጋ ነው:: ይህንኑ ለማመልከት እኔ የምቀድሳችሁ እግዚአብሐር እንደሆንኩ ታውቁ ዘንድ በእኔና በእናንተ መካከል ለልጅ ልጅ ምልክት ነውና ሰንበቶቼን ፈጽማችሁ ጠብቁ በማለት ተናግሮአል:: ዘጸ 31:13:: በብሉይ ኪዳን ሕግ መሠረት በሰንበት ዕረፍተ ሥጋ ይደረጋል ይኸውም በኋለኛው ዘመን በሐዲስ ኪዳን በክርስቶስ ቤዛነት በተገኘው ድኅነት በክርስቶስ ትንሣኤ በተሰጠው ዕረፍተ ነፍስ ተፈጽሟል:: የብሉይ ሰንበትም በሐዲስ ኪዳን ሰንበት፤ በሰንበተ ክርስቲያን ተተርጉሟል:: ይህም ማለት ክርስቶስ ሰንበትን ሻረው ማለት አይደለም:: ረቂቁን ምሥጢር በመግለጥ የበለጠ የከበረ ሥራን ሠርቶት አከበረው፤ ትርጉሙንም የበለጠ አጠናከረው ማለት እንጂ:: አስቀድሞ «እኔ እንደምቀድሳችሁ ታውቁ ዘንድ በእኔና በእናንተ መካከል ምልክት ነው:: እንዳለው በሰንበተ ክርስቲያን እርሱ መድኃኔዓለም ክርስቶስ በክበረ ደሙ ፈሳሽነት በነፍሱ ቤዛነት የኃጢአትን ኃይልና የሞትን ሥልጣን ድል ነሥቶ ከፍርድ ተገዢነት ነፃ በማውጣት እንዳሳረፈን እናስባለን:: የዠርነቱንም ሥራ እናስታውሣለን::

ሰንበት የነፃነት ምልክት ነው:: ይህንንም መጽሐፍ ቅዱስ አንተ በግብጽ ባሪያ እንደነበርክ አስብ እግዚአበሐር አምላክ ከዚያ አወጣህ ስለዚህ እግዚአበሐር አምላክህ የሰንበትን ቀን ትጠብቅ ዘንድ አዘዘህ ሲል መዝግቦታል:: ዘዳ5:15:: ይህ ስለ ሰንበተ አይሁድ የተነገረ ነው:: ግብጽ የሲኦል ባርነትና ከአጋንንት ግዞት ነፃ የማውጣት ምሳሌ ነበር::

በእርሱ ምንም ሥራ አትሥሩ በሰንበት ምንም ሥራ እንዳይሠራ ሕግ አዝዟል:: በዚህ ትእዛዝ ውስጥ በእርሱ ምንም አትሥሩ የሚለውን ሐረግ አይሁድ የሚፈጽሙት በደረቁ እንጂ በመንፈሳዊ ፍችው አንፃር አልነበረም:: ከዚህ የተነሣም በሰንበት በጎ ነገር ማድረግ ሁሉ በእነርሱ ዘንድ ሰንበትን መሻርና ኃጢአትም ነበር:: በዚህም ምክንያት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰንበት ድውያንን በመፈወሱ አብዝተው ይቃወሙት ነበር:: በዚያ ቀን ሥራ አትሥሩ ማለት በሰንበት ተጠምታችሁ ሥራ ፈትታችሁ ዋሉ ማለት ሳይሆን ተግባረ ነፍስ ፈጽሙበት ማለት ነው:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ሰንበት ለመንፈሳዊ ሥራ የተሰጠች መሆኗን ለማስተማር በሰንበት ድውያንን ይፈውስ በምኵራብም እየተገኘ ያስተምር ነበር:: ዮሐ 5:2-11 ዮሐ9:14 ሉቃ14:1-6:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እጁ የሰለለችውን ሰው በፈወሰ ጊዜ በሰንበት መልካም መሥራት የተፈቀደ መሆኑን ሲነግራቸው ከእናንተ አንድ በግ ያለው በሰንበትም በጉ በጉድጓድ ቢወድቅበት ይዞ የማያወጣው ሰው ማነው? እንግዲህ ሰው ከበግ ይልቅ እንደምን አይበልጥም? ስለዚህ በሰንበት መልካም መሥራት ተፈቅዷል ብሏቸዋል:: ማቴ 12:10-13:: ከአሥራ ስምንት ዓመት ጀምሮ የድካም መንፈስ ያደረባትም ሴት ከፈወሰ በኋላ የተናገረው ቃል የዚህ ተመሳሳይ ነው:: ሉቃ 13:10-16:: ከዚህም ሌላ መድኃኒታችን ሰንበት ስለሰው ተፈጥሯል እንጂ ሰው ስለ ሰንበት አልተፈጠረም ማለቱ ሰንበት ሰው መልካም ሠርቶ መንፈሣዊ በረከተ እንዲናገኝበት የተሰጠው መሆኑን የሚያመለክት ነው:: ማር 2:23

ከሁሉ በላይ ደግሞ ሰንበት ለመንሳዊ ሥራ እንዲውል በእግዚአብሔር መታዘዙን መጽሐፍ ቅዱስ ሰባተኛው ቀን ግን የዕረፍት ሰንበት ነው የተቀደሰ ጉባኤ ይሆንበታል:: በማለት መዝግቦታል ዘሌ 23:3:: በተጨማሪም እግዚአብሔር አምላካችን በየሰንበቱ ሥጋ ለባሽ ሁሉ በፊቴ ይሰግድ ዘንድ ዘወትር ይመጣል ሲል የተናገረው ሰንበት የአምልኮት መፈጸሚያ ቀን መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው:: ኢሳ 66:23:: ደቀመዛሙርቱም በሰንበት ያስተምሩ ነበር:: ማር 6:2:: የሐዋ 18:4 የሐዋ17:1-2

ቅዳሜና እሑድ

በቤተክርስቲያናችን ቅዳሜና እሑድን እንደ አንድ ቀን አድርገን አስተካክለን እናከበራለን:: የቅዳሜ መከበር በብሉይ ኪዳን የታዘዘ በመሆኑ ነው:: ያዘዘውም እግዚአብሐር ከዕለታት ሁሉ ለይቶ ስላከበረው እናከብረዋልን:: የአከባበራችን ሁኔታ ግን እንደ አይሁድ አይደለም:: ስለ ሰንበት ክብር የአይሁድ ሊቃውንት ብዙ ዓይነት አተረጓጐም ነበራቸው:: አክብር የሚለውን ቃል ለእግዚአብሐር እንደሚስማማ አድርገው ለመተርጐም ያላዩት መዝገበ ቃላት የለም:: ካህናቱም ሆኑ ሕዝቡ በዚህች ዕለት ሰንበት ስር መማስ ቅጠል መበጠስ ይቅርና የዘረጉትን አያጥፋም ያጠፉትንም አይዘረጉም የዘረጉትን አይከፍቱም የከፈቱትንም አይዘጉም ነበር:: አይሁድ በዕለተ ሰንበት ወደ ሽንት ቤት እንኳ አይሄዱም ነበር:: ከዚህም ሁሉ ጋር ቤት ቢቃጠል ሰው ቢሞት ጦር ቢመጣ በዕለተ ሰንበት ከሆነ መንቀሳቀስ ክልክል ነው:: ለምሳሌ በመቃቢያን ታሪክ እንደሚታወቀው 36 ሺህ አይሁዳውያን በወራሪ ጦር በአንድ ቀን ያለቁት በዚህች በዕለተ ሰንበት ነበር:: እኛ ግን ጌታ በወንጌል እንደተናገረው በሰንበት መልካም መሥራት ተፈቅዷል ብለን እናምናለን:: ማቴ 12:12:: መልካም ሥራ የተባለውም ተግባረ ነፍስ ነው:: ጌታችን እጁ የሰለለችበት ሰው ሆዱ የተነፋበትን ሰው እና መጻጉዕን የፈወሳቸው በዕለተ ሰንበት ነው:: ማቴ 12:10 ሉቃ14: 2 ዮሐ 5:10:: ከመወለዱ ጀምሮ ዕውር የነበረው ብላቴናም ፈውስ ያገኘው በዚሁ ዕለት ነው:: ዮሐ9:14

በፍትሐ ነገሥት ላይ ለክርስቲያን እንደ አይሁድ ዕለተ ሰንበትን ማክበር አይገባም ለክርስቲያን እንደሚገባ በመንፈሳዊ ሥራ በመትጋት ነው እንጂ:: ይላል:: ቅዱስ አትናቴዎስ ደግሞ በቅዳሴው ዕለተ ሰንበት የዕረፍት ቀን ናት ሲባል በደዌ እንደተያዘ ሰወ ከአልጋ ተጣብቆ ተኝቶ በመዋል አይደለም:: የዕለቲቱ ወዳጆች ለመሆን በመዓልትም በሌሊትም ለመንፈሳዊ ሥራ በመትጋት ነው እንጂ:: ብሏል::

እሑድ ደግሞ ጌታ ከሙታን ተለይቶ የተነሣበት ስለሆነ የጌታ ቀን ተብሎ በአዲስ ኪዳን የከበረ ነው:: ራእ1:10:: ከዚህም ሌላ ጊታችን የተጸነሰበት እና ዳግመኛም ለፍርድ የሚመጣበት ዕለት እሑድ ነው:: መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት የወረደበትም ዕለት እሑድ ነው:: በሐዋርያት ዘመንም በጢሮአዳ ያሉት ክርስቲያኖች እሑድ ቀን ይሰበሰቡ ነበር:: የሐዋ 20:7:: ቅዱስ ጳውሎስም ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሲጽፍ በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ያለው ዕለተ እሑድን ነው:: 1ኛ ቆሮ 16:1-4 ነቢዩ ዳዊትም በመዝሙሩ እግዚአብሔር የሠራት ቀን ይህች ናት ሐሴትን እናድርግ በእርስዋም ደስ ይበለን:: በማለት የተናገረው ስለ ዕለተ እሑድ ነው:: መዝ 117:24 ሌላው ቀርቶ በብሉይ ኪዳን እንኳ ሕዝቡ በኩራቱንና ቀዳሜያቱን ወደ ቤተ መቅደስ ወስደው ለካህኑ የሚያስረክቡት በቀዳሚት ሰንበት ማግሥት በዕለተ እሑድ ነበር:: ዘሌ 23:9-16:: በመሆኑም በመዝሙር በቅዳሴ በመንፈሳዊ ጉባኤ የታሰረ በመጉብኘት ለድኾች በመመጽወት የተጣላ በማስታረቅ ወዘተ ማክበር ይገባል:: በአጠቃላይ ሰንበትን ትቀድሰው ዘንድ አስብ ማለትም በሰንበት እግዚአብሐር በማገልገል በረከት የሚገኝበትን ሥራ በመሥራት ማክበር ማለት ነው:: ሰንበት የወደድነውን ሁሉ ልንፈጽምበት አልተሰጠንም:: የሰንበት ውሎአችንን ለእግዚአብሐር ሰጥተን በዚህች ቀንም እርሱ ያደረገለንን ቸርነት እያሰብን በማመስገን በመንፈስ የምናድግባቸውን ቅዱሳት ተግባራት ማከናወን ይኖርብናል:: ይህም ከሰንበት ረድኤት በረከትን ለመሳተፍ ያበቃናል ይህን ትእዛዝ በመተላለፍ ከመከሰስም ያድነናል:: ፈጣሪያችን እግዚአብሔር በቸርነቱ ይጠብቀን አሜን::

## *አራተኛው ትእዛዝ*
## *አባትና እናትህን አክብር*

"አባት እና እናትህን አክብር እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም መልካምም እንዲሆንልህ የሚል" ነው ዘጸ 20:12

ይህ ትእዛዝ በሰዎች መካከል ስላለው ግንኙነት የተሰጠ የመጀመሪያው ትእዛዝ ነው:: እስከ አሁን የተነገሩትና ከላይ ያሉትን ሦስቱን ትእዛዛት የሰው ልጅ ለእግዚአብሔር ሊያደርጋቸው የሚገባውን ሲያመለክቱ ይህኛው ትእዛዝ ደግሞ የሰው ልጅ ለሰው ልጅ ሊያደርግ የሚገባውን ያመለክታል::

ይህ ትእዛዝ ከሌሎች ትእዛዛት የሚለየው ከሚገኘው የበረከት ዋጋ ጋር አብሮ የተሰጠ የመጀመሪያ ትእዛዝ በመሆኑ ነው:: አባትና እናቱን የሚያከብር ልጅ እግዚአብሔር በሰጠው ምድር ዕድሜው ይረዝማል መልካምም ይሆንለታል ተብሏል:: ለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም "መልካም እንዲሆንልህ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም አባትና እናትህን አክብር እርሷም የተስፋ ቃል ያላት ፊተኛይቱ ትእዛዝ ናት" በማለት እግዚአብሔር ከሚሰጠን የበረከት ዋጋ ጋር ቃል በመግባት የሠራልን ትእዛዝ መሆኑን ገልጦታል:: ዘዳ 5:16 ኤፌ 6:2-3

<u>*ወላጆችን ማክበር እንዴት ነው?*</u>

1. በማፍቀር :- ሰው መጀመሪያ የሚያውቀው የእናቱን ቀጥሎም የአባቱን ፍቅር ነው:: ልጅም የሚቻለውን ሁሉ በማድረግ ለወላጆቹ ያለውን ፍቅር በምግባር መግለጥ ይጠበቅበታል:: ወላጆቹን ከልቡ የሚወድ ልጅ ቃላቸውን ያከብራል የሚሉትንም ይፈጽማል:: በመሆኑም ወላጆችን ማፍቀር አንዱ አክብሮትን መግለጫ ነው::

2. <u>በፈቃደኝነት መታዘዝ:-</u> ጌታችን ለእናቱና ለጠባቂዋ ለጻድቁ ለዮሴፍ ይታዘዝላቸው ነበር:: ሉቃ 2:51:: ፈጣሪያችን ለእናቱና ለአሳዳጊው ለዮሴፍ አረጋዊ እንደታዘዘ ሁሉ ልጆችም ለወላጆቻቸው በፍጹም ፈቃደኝነት እየታዘዙ በረከትን መቀበል ይገባቸዋል:: ለዚህም የይስሐቅ እስከ መሥዋዕትነት የዘለቀ ታዛዥነትና ፈቃደኝነት ጠቃሚ ትምህርት ይሆናል:: ዘፍ 22:1-14 ፈቃደኝነትና ታዛዥነት የትኅትናና የመልካም ምግባር ፍሬዎች ራስንም ዝቅ የማድረግ ውጤቶች ናቸው:: በእነዚህ ምርኩዝነት ወላጆችን ማክበር ያስፈልጋል::

3. <u>በመርዳት:-</u> ልጅ ወላጆቹ የእርሱን ዕርዳታ በሚሹት ጊዜ እንደ አቅሙ የመርዳት ግዴታ አለበት:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ነገር ግን ለእርሱ ስለሆኑት ይልቁንም ስለቤተሰቦቹ የማያስብ ማንም ቢሆን ሃይማኖትን የካደ ከማያምን ሰው ይልቅ የከፋ ነው::" በማለት የተናገረውን ይህንኑ ግዴታ ለማስገንዘብ ነው:: 1ጢሞ 5:8:: ጻድቁ ዮሴፍ አባቱን አስጠርቶ ይረዳው እንደነበር:: ዘፍ 45: 9ሀ11:: በዚህ አንጻር ወላጆቹን መርዳት የክብሮት አንዱ መልክ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል::

4. <u>በመልካም ፍሬ:-</u> በመጽሐፍ "ጠቢብ ልጅ አባቱን ደስ ያሰኛል ሰነፍ ልጅ ግን ለእናቱ ሐዘን ነው" "የጻድቅ አባት ደስ ይለዋል ጠቢብንም ልጅ የወለደ ሐሴትን ያገኛል" እንደተባለ መልካም ፍሬ እያፈሩ ሥራ ወጤታማ እየሆኑ ወላጆችን ማስደሰት ወላጅን የማክበር ገጽታ ነው:: ምሳ 10: 1 23:24

5. <u>ወላጆቹ ያደረጉለትን በማሰብ:-</u> ምንም እንኳን ወላጆች ከፅንስ እስከ ጉልምስና ድረስ ለልጆቻቸው የሚያበረክቱትን መሥዋዕትነት በእርጅናቸው ዘመን በሚደረግላቸው ዕርዳታ የሚካካስ ውለታ ባይሆንም ልጅ አባቱና እናቱ ያደረጉለትን ሁሉ ዘወር ብሎ መመልከትና ፍቅራቸውንም ማስታወስ አለበት::

ከዚህም ሌላ ከወላጅ አባትና እናት በተጨማሪ ሌሎች የአባትና እናት ክብር የሚገባቸው አሉ:: እነዚህም መንፈሳዊያን አባቶችና እናቶች አረጋውያን በማዕረጋቸው ታላቅ የሆኑ የቤተሰብ የመሥሪያ ቤት የቤተክርስቲያን ወዘተ . . . አባላት ናቸው:: እነዚህ ሁሉ አክብሮት ሊሰጣቸው የሚገባ እንደ ወላጅ አባትና እናት የሚቆጠሩ ናቸው:: እነዚህ ላይ አንድ ጥያቄ እናነሣ ይሆናል:: አባትና እናትን ማክበር ለእነርሱም መታዘዝ ሲባል ገደቡ እስከምን ድረስ ነው?

ይህንንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሚገባ መልሶልናል:: ልጆች ሆይ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ ይህ የሚገባ ነው::" ኤፌ 6:1:: በመሆኑም "በጌታ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የወላጆች ትእዛዝ በሕገ እግዚአብሔር መሠረት መሆን እንዳለበት ነው:: ከሕገ እግዚአብሔር ጋር የሚቃረን ትእዛዝ ለመፈጸም ልጁ ወይም ታዛዡ አይገደድም:: አባትና እናትን ማክበር ለእርሱም መታዘዝ ትእዛዙ መንፈሳዊና በሕገ እግዚአብሔር መሠረት የሆነ እንደሆነ ብቻ ነው:: ከማንም ከሁሉም በፊትና በላይ መታዘዝ የሚገባው ለእግዚአብሔር አምላክ ነው:: ከወላጆች አግባብነት የሌለው ትእዛዝ የተነሣ የሚያስጨንቅ ነገርና ለመወሰን የሚያስቸግር ጉዳይ ሲገጥም ለሰው ታዝዞ እግዚአሔር ከማሳዘን ለእግዚአብሔር መታዘዝ ይገባል::

# አምስተኛው ትእዛዝ

## «አትግደል»

ዘጸ.20÷13።

«አትግደል» የሚለው ትእዛዝ ወንጀለኞችንና ነፍስ ገዳዮችን ብቻ የሚመለከትና ለክርስቲያኖች አስፈላጊ ያልሆነ የሚመስላቸው አንዳንድ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ይሁን እንጂ በዚህ ርእስ ሥር የዚህን ትእዛዝ አስፈላጊነ ትና ጠቀሜታ በማሳየት በሕይወታችን ላይ ያለውን ተጽ እኖ፤ ምን ያህል እየተላለፍነው ወይም እያከበርነው መሆኑን ለመዳሰስ እንሞክራለን። ከሁሉ አስቀድሞ አንድ ጥያቄ እናነሣለን፤ እግዚአብሔር መግደል ፈጽሞ ከልክሎ ይሆን ወይም እንደኃጢአት ወይም እንደወንጀል የማይቆጠር የተፈቀደ መግደል ይኖር ይሆን?

## የተፈቀደ መግደል

እግዚአብሔር አምላክ አትግደል የሚለውን ትእ ዛዝ ሕግ አድርጎ የሰጠ ሲሆን በአንዳንድ ሥፍራዎች ደግሞ መግደል የፈቀደበት ሁኔታ መኖሩን እናስተውላለን። መፍ ቀድ ብቻ ሳይሆን መግደልን አስፈላጊ ያደረገባቸው አን ዳንድ ሥፍራዎችም አሉ። በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንደ ምናገኘው ኃጢአት የሠራ ሰው እንዲገደል ሕግ ተሠርቷል።

## ትእዛዛትን የተላለፈውን በሞት መቅጣት

ለምሳሌ «አታመንዝር» የሚለውን ትእዛዝ የተላለፈ ሰው በሞት ይቀጣ ነበር። በመጽሐፍ «አመንዝራውና አመንዝራይቱ ፈጽሞ ይገደሉ።» ይላልና። ዘሌ.20÷10–16። በዝሙት ያገኟትን ሴት በጌታ ፊት በከሰሷት ጊዜ ጸሐፍት ፈሪሳውያን የጠቀሱት ይህን ሕግ ነበር። ዮሐ.8÷5። ከዚህም ሌላ ማንም ይሁን ትእዛዝ ተላልፎ ሰውን ቢገድል በተን ኮልም በባልንጀራው ላይ ቢሸምቅበትና ቢገድለው ፈጽሞ ይገደል የሚል ትእዛዝ አለ። ዘጸ.21÷12–14። በቀጥታ የገደለ ብቻ ሳይሆን በተዘዋዋሪ ለአንዱ ሰው መሞት ተጠ ያቂ የሚሆን መገደል እንደነበረበት በሕግ ተደንግጎ ነበር፤ «በሬው ግን አስቀድሞ ተዋጊ ቢሆን፥ ሰዎችም ለባለቤቱ ቢመ ሰክሩለት ባይጠብቀውም፥ ወንድንም ወይም ሴትን ቢገድል፥ በሬው ይወገር፤ ባለቤቱ ደግሞ ይገደል።» ተብሎ ነበርና። ዘጸ.21÷29።

በብሉይ ኪዳን እንደተጻፈ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ የሚጠራ እንዲገደል ሕግ ይናገራል፤ ከትእዛዛት አንዱን ተላልፏልና። ዘሌ.24÷16። የመጀመሪያውን ትእዛዝ

በመተላለፍም ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ ያመለከ ለጣዖትም የሰዋ ሁሉ እንዲገደል እንዲጠፋም እግዚአብሔር አዝዞአል:: የበአልን ካህናት ነቢዩ ኤልያስ ያስገደላቸው በዚሁ ትእዛዝ መሠረት ነበር:: ዘጸ.22÷20:: 1ነገ.18÷40::

በሌላ ሥፍራ ደግሞ አረመኔዎች፣ ምትሐተኞችና ጠንቋዮች የሐሰት ነቢያትና ሐሰተኛ ሕልም አላሚዎች እንዲገደሉ ሕግ መኖሩን መጻሕፍት ያረጋግጣሉ:: ዘሌ.20÷27:: ዘፍ.22÷18:: ዘዳ.13÷15::ዘዳ.13÷5::

ከፍ ብለን ከጠቀስናቸው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንደተረዳነው አመፀኞችንና ሕግ ተላላፊዎችን መግደል የተፈቀደ በመሆኑ እንደኃጢአት ተቆጥሮ ወይም «አትግደል» የሚለውን ትእዛዝ እንደመሻር ተወስዶ የሚያስቀጣ አይደለም:: በሐዲስ ኪዳንም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ለቀደሙት አትግደል እንደተባለ ሰምታችኋል የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል» በማለት ሲናገር የጠቀሰው ሕግ በዘጸአት «አትግደል» የተባለውንና በዘሌዋውያን ደግሞ «ሰውን እስኪሞት ድረስ የሚመታ ፈጽሞ ይገደል» የሚለውን ነው:: ዘጸ.29÷13:: ዘሌ.24÷17:: ከዚህም በላይ መግደል ብቻ ሳይሆን በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ወንድ ሙንም የሚሰድብ የሸንጎ፤ የገሃነምም ፍርድ የሚገባው መሆኑን በመግለጥ ይህን ሕግ እንደአጠበቀው እንመለከታለን:: ማቴ.5÷21–23::

## የትእዛዙ ጠቃሚነት

በዚህ ምድር በምንኖርበት ዘመን በምንሠራው በማንኛውም ኃጢአት በምንም መንገድ ይሁን በምን አንድን ወይም ብዙ ሰዎችን እንጎዳለን:: የገደልነው እንደሆነ ግን እናጠፋዋለን:: በምድር ላይ የመኖር ዕድሉም ፈጽሞ ይወድማል:: መግደል የሰውን ሕይወት በእጅጉ ይጎዳል:: የሰው ሕይወት የራሱ ባለመሆኑና የሰውን መድረሻና ፍጻሜ ሊወስነው የሚችለው ፈጣሪው እግዚአብሔር ብቻ በመሆኑ መግደል በእግዚአብሔር ሥልጣን ገብቶ በደል መፈጸምም ጭምር ነውና ያስጠይቃል:: የሰውን ሕይወት ሊቆጣጠርና ከጠፋም በኋላ ሊተካው የሚችል ማንም የለም፤ እግዚአብሔርም እርሱ እስከወሰነው ዘመን ብቻ እንዲኖር ነው የፈጠረው:: የሕይወትና የሞት ቁልፍ በእግዚአብሔር እጅ ብቻ የተያዘ ነው::

በመግደል የሚፈጸም ኃጢአትም ሊጠገን የማይችል በመሆኑ ከባድ ነው:: ሰው በሌላ ሰው ላይ ስለሠራው በደል ሊክስ ይችላል፣ የሰደበውን ሰው ክብር ለመግለጥ ይቅርታ ሊጠይቀው ይችላል፤ የነጠቀውን ንብረትም ሊመልስለት ይችላል:: መግደል ግን ከዚህ የተለየ ነው፤ ማንም የገደለውን ሰው ሕያው ሊያደርግ አይችልምና:: ንስሐ

ያልገባውን ሰው መግደል ደግሞ የመግደልን ኃጢአት
የበለጠ ያከብደዋል፤ምክንያቱም ሟቹ በንስሐ ስለዘለዓለ
ማዊ ሕይወቱ የነበረውን ተስፋ ፈጽሞ የሚያጨልምበት ስለ
ሆን ነው:: የሞተው ሰው ሞቱ በሥጋም በነፍስም በመሆኑ ዕ
ጣ ፈንታውም ወደ ሲኦል መጣል ነውና የገዳዩ ኃጢአት
እጅግ ከባድ ይሆናል:: ይህን እንግዲህ መግደል ምን ያህል
የከፋና የሚያስጠይቅ ከባድ በደል መሆኑን የሚያስረዳ ነው::

ነፍሰ ገዳይ ሰው የራሱም ገዳይ ነው፤ የሠራው ኃጢ
አት ራሱንም ቢሆን ወደ ሞትና ወደሲኦል የሚያደርሰው
ነውና:: ይህ ሁሉ የተነገረው፤ መግደልም እጅግ ከባድ ነው
ያልነው ለንስሐ ያልበቁ በኃጢአት ዓለም ወይም በክፉ ሥራ
የሚኖሩ እግዚአብሔርም በገባላቸው ቃል ኪዳን መሠረት
የመዳን ተስፋ ያላቸውን ሰዎች በተመለከተ ነው:: ንስሐ
ገብቶ የሚጠራበትን ቀን የሚጠብቀውንና የዘለዓለም ሕይ
ወት ተስፋው የተረጋገጠለትን ሰው የገደለውስ የሚል ጥያቄ
መነሣቱ አይቀርም::

ማንም ይሁን ማን ሰውን መግደል ኃጢአት ነው::
በተለይም በሕይወቱ ቅድስና፣ በአገልግሎቱ፣ በተሰጠው
ማንኛውም ጸጋ ቢሆን ወገኖቹን ሊረዳ፣ የተቻለውንም
ለኅብረተሰቡ ሊያበረክት የሚችለውን ጠቃሚ ሰው መግደል
የእግዚአብሔርን ሕንፃ ከማፍረስ በተጨማሪ በዚያ ሰው
ለሚጠቀመው ሕዝብ ጉዳት ነው:: የበደሉ መጠንና የኃጢ
አቱ ክብደትም በሟቹ ጠቃሚነትና አስፈላጊነት መጠን
የሚመዘን ነው:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም «ነቢ
ያትን የምትገድል ወደእርሷ የተላኩትንም የምትወግር» በማ
ለት ኢየሩሳሌምን የወቀሳት በእግዚአብሔርም በሕዝብም
ዘንድ ከፍተኛ ጠቃሚ አገልግሎት ሊያበረክቱ የሚችሉት
ቅዱሳን በክፉት ልጆች በመገደላቸው ነው:: ማቴ.23÷37::

በሌላም ቃል «ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ በቤተ
መቅደስና በመሠዊያው መካከል እስከገደላችሁት እስከ በራ
ክዩ ልጅ እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ በምድር ላይ የፈሰሰው
የጻድቅ ደም ሁሉ ይደርስባችሁ ዘንድ» በማለት የተናገረው
በግፍ ስለተገደሉት ደጋግ አበው ነው:: ማቴ.23÷35:: በዚህ
ምንባብ ውስጥ «የጻድቅ ሁሉ ደም» የሚለው ሐረግ የደጋግ
ሰዎችን ደም ማፍሰስና መግደል ከባድ ኃጢአት መሆኑንና
የሚያስከትለውንም የተጠያቂነት አደጋ የሚያመለክት
ነው::

ቃየን ወንድሙን አቤልን በገደለው ጊዜ እግዚአብሔር
ቃየንን «የወንድምህ የደሙ ድምፅ ከምድር ወደእኔ
ይጮኻል::» ማለቱ የቃየን በደል ከባድ መሆኑን የሚያሳይ
ነው:: ዘፍ.4÷10:: አቤል ስለመገደሉ የተናገረው ነገር
አልነበረም፤ ቢሆንም ሰማያዊ ፍርድ ይህን ይሻል፤ እግዚ
አብሔር ደም የሚያፈሱትን ይበቀላልና:: ስለዚህ እግዚ
አብሔር አምላክ የተበቀለው ስለአቤል ብቻ አይደለም፤
በጭካኔ ወንድሙን የገደለው ቃየን እግዚአብሔርን «እነሆ
ዛሬ ከምድር ፊት አሳደድኸኝ፤... የሚያገኘኝም ሁሉ ይገ
ድለኛል::» ባለው ጊዜ እግዚአብሔርም መልስ «እንግዲህ

ቃየንን የገደለ ሁለ ሰባት እጥፍ ይበቀልበታል» በማለት ቃየንን ያገኘው ሁሉ እንዳይገድለው ምልክት አደረገበት:: ዘፍ.4÷14–15:: ይህን ያደረገበት ምክንያት ሰው ሁሉ ነፍሰ ገዳዩን ለመበቀል እጁን እንዳያነሣ ነው፤ በቀል የእርሱ የልዑል እግዚአብሔር ነውና:: ነፍሰ ገዳዩን በመግደል መልካም ያደረገ እንዳይመስለውም ነው:: የተገደለው ሰው ደግሞ ደግም ሆነ ክፉ ነፍሰ ገዳዩን ከተጠያቂነት የማያድነው ከመሆኑም በላይ መግደል ደግሞ ከባድ ኃጢአት ነው::

እግዚአብሔር አምላክ ደም የሚያፈሱትን በራሱ መንገድ ሳይበቀላቸው አይቀርም::ሰዎቹ ደጋግ እንኳ ቢሆኑ ሰው የገደሉ ከሆነ እግዚአብሔር በሆነው ነገር ይበቀላቸዋል:: ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን ቅዱስ ዳዊት ነው:: እርሱ ከመንፈሳዊ ቅናት በመነሣት ቤተ መቅደሱን ለማነፅ በወሰነ ጊዜ እግዚአብሔር የነገረውን እንመልከት:: «ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ:– እጅግ ደም አፍስሰኻል፤ ታላቅም ሰልፍ አድርገሃል፤ በፊቴ በምድር ላይ ብዙ ደም አፍስሰሃልና ለስሜ ቤት አትሠራም::» አለኝ ሲል ተናግሮአል:: 1ዜና.22÷8:: እግዚአብሔር ዳዊትን ደግ መሆኑን ቢያውቅ እንኳ በእጁ ስለፈሰሰው እጅግ ብዙ ደም ይህን ክብር ሊሰጠው አልፈቀድም፤ በዚህም ተበቀለው፤ ቀጣው:: ቸሩ እግዚአብሔር በሚወደው ዳዊት እንዲህ አደረገ:: እርሱ እግዚአብሔር ስለዳዊት «ዳዊትን ፈተንኩት፤ ልቡንም እንደልቤ ሆኖ አገኘሁት» በማለት ተናግሯል:: ልጁ ሰሎሞንም ሲጸልይ «ስለባሪያህ ስለዳዊት ብለህ ፊትህን ከእኔ አትመልስ» ብሏል፤ ፈጣሪው እግዚአብሔርም «ስለባሪያዬ ስለዳዊት» እያለ ብዙ መልካም ነገሮችን ለሰው ልጆች አድርጓል:: ዳዊት እንደዚህ ደግና ጻድቅ ሲሆን ባፈሰሰው ደም የተነሣ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ እንዳይሠራ ተከለከለ:: ቤተመቅደሱንም ከእርሱ አብራክ የተገኘውና በዘመኑ ሰላምና ጸጥታ የሆነለት ንጉሡ ሰሎሞን ሠርቶታል::

እግዚአብሔር «በቀል የእኔ ነው እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ» በማለት የተናገረውን ቃሉን የሚያጥፍ አይደለም:: ስለቃሉ ክብር ብለው በመታገሥ መከራን ተቀብለው በሰማዕትነት ስለሞቱት እንኳን ሳይቀር እግዚአብሔር በፍርድ ወንበር ተቀምጦ የሚበቀልላቸውና እውነተኛውን ፍርድ የሚሰጥ መሆኑን በቃል ኪዳን ገልጦአል:: ራእ.6÷10:: ስለዚህ እጅን ከደም አካልንም ከመግደል መከልከል ተገቢ ነው::

## የአገዳደል ዓይነቶች

«አትግደል» የሚለው ትእዛዝ ሰፊ ትርጉም ያለው ነው:: እግዚአብሔር አምላክ አትግደል በማለት ሲያዝዝ ማንም ሰው ራሱንም ሆነ ሌላውን ሰው መግደል የማይችል መሆኑን የሚያመለክት ነው:: ይህም በማንኛውም ምክንያት የትኛውንም ዓይነት ግድያ የሚከለክል ትእዛዝ ነው:: ኃጢአት በማሰብ፣ በመናገርና በማድረግ እንደሚፈጸምና ሁሉም

ኃጢአት እንደሆነ ሁሉ ግድያም የሚጀመረው በማሰብ
በመፈለግና በመመኘት ነው። ሰማያዊው ሕግ ከምድራዊው፣
መንፈሳዊው ሕግ ከሥጋዊው/የወንጌል/ ሕግ የሰፋ በመሆኑ
ለግድያ የሚሰጠውም ትርጉም ጥልቅና ሰፊ ነው። በዚህ ዓ
ለም በወንጌል ሕግ የግድያ ሙከራና ግድያው የተፈጸመ
እንደሆነ ብቻ የሚያስቀጣ ሲሆን ሌላውን ሰው ለመግደል
የሚያስበውና የሚመኘው ግን ምኞቱና ሃሳቡ በተግባር
እስካልተገለጠ ድረስ የሚያስቀጣ አይደለም። እግዚአብሔር
ግን ስለክፉ ምኞቱና ሃሳቡ በዚህ ሰው ይፈርድበታል እርሱ
ልብንና ኩላሊትን የሚመረምር አምላክ ነውና።

በአንዱም ሆነ በሌላው ሁኔታ የተለያዩ የአገዳደል ዓይ
ነቶች አሉ። አካልን መግደል፣ መንፈስን መግደል፣ ሥጋን
መግደል፣ ነፍስን መግደል፣ በቀጥታ መግደል፣ በተዘዋዋሪ
መግደል፣ በግል መግደል፣ ተባባሪ ሆኖ መግደል ወዘተ
ሁሉም መግደል ነውና ሕግን በመተላለፍ የሚያስቀጣ ነው።

ጦርነት መግደልን በሚከለክለው በአምስተኛው ትእ
ዛዝ ይጠቃለላልን? የሚሉ ጠያቂዎች መኖራቸው አይቀርም።
ለዚህ ጥያቄ የምንሰጠው መልስ በሁለት መልክ የሚታይ
ነው። በመጀመሪያ ደረጃ እግዚአብሔር አንድ ሰው እንዳይ
ገደል ከከለከለ የብዙዎችን መግደልም የማይፈቅድ መሆኑ
ግልጽ ነው። ከዚህ አንፃር የብዙዎች ነፍሳት እንዲጠፉ
የጥፋት መሣሪያዎችን በማምረት እነዚህን መሣሪያዎች
ለመሞከሪያ ወይም አምባገነንነታቸውን ለማሳየት ጦርነት
በመክፈት በሌሎች ላይ ዘምቶ የብዙዎቹን ሕይወት መቅጠፍ
የአምስተኛው ትእዛዝ ተቃራኒ ነው። የዚህ ዓይነቱ ጦርነት
የፈጠረውን የሕዝቡን ሰላማዊ ሕይወት በሚፈልገው በእግዚ
አብሔር ዘንድ የተጠላ ነው። በእግዚአብሔር ሕግ ብቻ
ሳይሆን በዓለም አቀፍ መንግሥታትም ይህንን የሚከለክል
ስምምነት መፈረሙ በግፍ በሚነሡ ጦርነቶች የሚጠፋው
የሰው ሕይወት እንዲተርፍ ሰላማዊ ኑሮ አስፈላጊ ስለሆነ
ነው።

በሁለተኛ ደረጃ እግዚአብሔር ሰው ራሱን ከሚደርስ
በት ማንኛውም አጥፊ አደጋ እንዲከላከል ፈቃዱ መሆኑ
የታወቀ ነው። ይህን በመሰለ ሁኔታ እሥራኤልን እንዴት
ከፍልስጥኤማውያን ጥቃት ራሳቸውን መከላከል እንደሚገባ
ቸው ያስተምር እንደነበር ቅዱስ መጽሐፍ መዝግቦታል። ከዚህ
አንፃር ራስን ከአብሪተኞች ጦርነት መከላ ከል ሕዝቡን ከጥፋት
መከላከል በመሆኑ ይህ የአምስተኛው ትእዛዝ ተቃራኒ አይ
ደለም። ገዳዮችን መከላከል ተገቢ ነውና እግዚአብሔርም ይህን
የመሰለውን እርምጃ የወሰዱ ብዙ ሰዎችን እንዳልተቃወማቸው
መጽሐፍ ምስክር ነው።

ዘመናችን የቴክኖሎጂ ውጤቶች በተራቀቀ ሁኔታ
በአገልግሎት ላይ የዋሉበት መሆኑ በሁላችን ዘንድ የታወቀ
ነው። ይሁን እንጂ ይህን የጥበብ ውጤት ለጥፋት መጠ
ቀም በተለይም የእግዚአብሔርን ሕንፃ ለማፍረስ መጠቀም
ከፍተኛ ኃጢአት ነው። ለምሳሌ በአንዳንድ የሕክምና ተቋ
ማት ወሊድን ለመቆጣጠር በሚል ሰበብ የወንዴውን የዘር
ምንጭ ከሰውነቱ በማስወገድ የማደረግ ቀዶ ጥገና ተተኪ

የሰው ዘር እንዳይፈጠር የተደረገ የረቀቀ የግድያ ወንጀል
በመሆኑ አትግደል ለሚለው ትእዛዝ ተቃራኒ ነው።

በሌላም በኩል ያልተወለደውንና ወደፊትም በሕ
ይወት የመኖር እድል ያለውን ፅንስ የማኖሩም ሆነ
የመግደሉ ሥልጣን የእግዚአብሔር ሆኖ ሳለ በውርጃ እንዲ
ወጣ ማድረግና ማስወገድ ራሱ የአምስተኛው ትእዛዝ
ተቃራኒና የግድያ ወንጀልም ነው። በሕገ እግዚአብሔር
አትግደል ከመባሉም ሌላ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግም የዚ
ህን ተግባር ፈጻሚዎች ወንጀለኞች የሚያደርጋቸው ድን
ጋጌ አለ። «በእግዚአብሔር ፈቃድ ከተፀነሰ በኋላ ሕልው
ናው በሰው ባልተፈለገ ፅንስ ላይ በሚደረግ የማስወረድ ወን
ጀል የተሳተፉት ሁሉ በምድራዊ ሕግም በወንጀል በእግዚ
አብሔር ሕግም በኃጢአት ተጠያቂዎች ናቸው። ውርጃን በማ
ንኛውም መንገድ የሚያግዙ ሰዎች የግድያ ወንጀል ተ ባ
ባሪ መሆናቸውን ማወቅና ከዚህ ኃጢአት መከልከል
ይኖርባቸዋል።

ሰው እስከ አሁን ከገለጥናቸው ተግባራዊ የግድያ ዓ
ይነቶች ሌላ በሃሳቡም ሌላውን ሊገድል ይችላል። አንድን
ሰው ለመግደል ወይም በሌሎች ተገድሎ ለማየት ይፈልግና
ይህንኑ ያውጠነጥን ይሆናል። በሰውየው መሞት የሚያ
ገኘውን ዕርካታ /ደስታ/ እያሰበ ይደሰት ይሆናል። በዚህ
ሁሉ ድርጊቱ በፍላ ጎቱና በሃሳቡ ያንን ሰው ገድሎታልና
ተጠያቂ ነው። የአንድን ሰው መሞት ማሰብና መመኘት
ከፍቅር የተነሣ ለባልንጀራ በጎ ነገር ከማሰብ ጋር የሚቃረን
ነውና በልቡና ውስጥ ተደብቆ የሚሠራ ኃጢአት ነው።
ይህን መሰሉ ጥላቻም የግድያ ዓይነት ነው። ሐዋርያው
ቅዱስ ዮሐንስ «ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው»
በማለት ማስተማሩ ለዚሁ ነው። 1ዮሐ.3÷15። ከዚህ በመ
ነሣት አትግደል የሚለው ትእዛዝ በተግባር የገደሉትን
እንጂ እኛን አይመለከተንም የሚሉ ሰዎች ይኖሩ አይ
ችልም።

ከዚህ ሌላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራ ስብከቱ
«ለቀደሙት፡- አትግደል እንደተባለ ሰምታችኋል፤ የገደለም
ሁሉ ፍርድ ይገባዋል። እኔ ግን እላችኋለሁ÷ በወንድሙ ላይ
የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል» በማለት መቆጣትን ከግድያ
ጋር አስተካክሎ ተናግሮአል። ማቴ.5÷21-22። በመሆኑም
ሰው የሚወደውን ወንድሙን ሊገድለው ቀርቶ ከቶም ሊያስ
ብበት አይገባውም የፍቅር ሕግ ይከለክለዋልና።

በሌላ በኩልም ተዘዋዋሪ የግድያ ዓይነቶች አሉ።
እነዚህ በቀጥታ ለጊዜው ለሞት የሚያበቁ ሳይሆኑ ቀስ በቀስ
ግን ወደሞት የሚያደርሱ ናቸው። ለጊዜው መግደል
በጥይት ወይም በዱላ መትቶ ወይም በጩቤ ወግቶ ወይም
በድንጋይ ወግሮ ብቻ አይደሉም። ሰውን የሚያሳዝን
ንግግር፣ አስጸያፊ ጠባይ፣ ሰውን መናቅና መስደብም ሁሉ
የሰውን ኅሊና የሚያቆስሉና ዕረፍትና ሰላም የሚነሡ ነገሮች
ናቸው። እነዚህ ሁሉ ቀስ በቀስ የሚጎዱ እንጂ በአንድ ጊዜ
ለሞት የሚያበቁ አይደለም። ከጊዜ በኋላም ሲገድሉ የሞቱን
ምክንያት ሰዎች አያውቁትም እግዚአብሔር ግን ያውቀዋል።

ከዚህ ሰው ግድያ ውስጥ በማበሳጨትም ሆነ በማሳደብ ወዘተ የተሳተፉ ሁሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሥራቸውን ያገኛሉ በተዘዋዋሪ የግድያው ተሳታፊዎች ናቸውና።

በመጽሐፍም «እነሆ፥ እርሻችሁን ያጨዱት የሠራተኞች ደመወዝ በእናንተ ተቀምቶ ይጮኻል፤ የአጫጆችም፥ ድምፅ ወደጌታ ፀባዖት ጆሮ ገብቶአል።» እንዳለው ለቀጠረው ሠራተኛ ከአገልግሎቱ ጋር የሚመጣጠን ዋጋ የማይከፍለው አሠሪ በተዘዋዋሪ ሠራተኛውን ወደሞት እየነዳው መሆኑን ማወቅ አለበት። ያዕ.5÷4። ሊያገኝ የሚገባውን የደመወዝ ጭማሪና ዕድገት መከልከል ሠራተኛውን በተዘዋዋሪ መግደል ነው። መጽሐፍ «የሞያተኛው ዋጋ እስከ ነገ ድረስ በአንተ ዘንድ አይደርብህ።» «ድሀና ችግረኛ የሆነውን ምንደኛ፥ ከወንድሞችህ ወይም በምድርህ በአገርህ ደጅ ውስጥ ከሚቀመጡት መጻተኞች ቢሆን፥ አታስጨንቀው። ድሀ ነውና፥ ነፍሱም ጠንክራ ትፈልገዋለችና ወደ እግዚአብሔር እንዳይጮኽብህ፣ ኃጢአትም እንዳይሆንብህ ደመወዙን ፀሐይ ሳይገባ በቀኑ ስጠው።» በማለት ይመክራል። ዘሌ.19÷13። ዘዳ.24÷14። ያለበቂ ምክንያት ሠራተኛን ከሥራ ማባረርም በእርሱና በቤተሰቡ ሁሉ ላይ በተዘዋዋሪ የግድያ ወንጀል መፈጸም ነው።

በበሽታ ወይም በሌላ ችግር ምክንያት ሞት ጥላውን አጥልቶበት ዕርዳታ ለሚሻ ሰው ተገቢውን ዕርዳታ አለማድረግ በተዘዋዋሪ መንገድ መግደል ነው። መጽሐፍም ይህን በተመለከተ «የድሀውን ጩኸት እንዳይሰማ ጆሮውን የሚደፍን ሰው፥ እርሱ ራሱ ይጮኻል፤ አይሰማለትም።» በማለት ያስገነዝባል። ምሳ.21÷13። መልካም ማድረግ ሲቻል አለማድረግ የሚያስጠይቅ መሆኑን ሲገልጽ «በጎ ለማድረግ ዐውቆ ለማይሠራው ኃጢአት ነው» ይላል። ያዕ.4÷17። በዓለማችንም የሰዎችን ዕርዳታ ሲሹ በሞት አፋፍ ሆነው የሚያጣጥሩ እጅግ ብዙ ነፍሳት እንዳሉ ይታወቃል። እነዚህን ድሆች በተቻለ መጠን አለመርዳት በተዘዋዋሪ መግደል መሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው። በግቢው ደጃፍ ወድቆ ፍርፋሪ ለለመነው አልዓዛር ያልራራለት ነዌ የሚገባውን ቅጣት ከመቀበል አላመለጠም። ሉቃ.16÷19። በመንገድ የወደቀውን በሽተኛ መርዳት ሲገባቸው ጥለውት የሄዱት ካህኑና ሌዋዊው ሰው የየራሳቸውን ምክንያት ያቀርቡ ይሆናል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ምክንያታቸውን አይቀበላቸውም። እርሱ «ምሕረትን እወዳለሁ መሥዋዕትንም አይደለም» በማለት ምሕረት በሌለበትና ክፋት በሞላበት ልብ የምታቀርቡልኝ መሥዋዕት አያስደስተኝም ብሏልና። ማቴ.9÷13። እግዚአብሔር ግን ደጉን ሣምራዊ ልኮ ታድጎታል። ካህኑና ሌዋዊው ግን በተዘዋዋሪ ለሞት ጥለውት በመሄዳቸው አምስተኛውን ትእዛዝ በመጣስ ከመጠየቅ አይድኑም። ይኸውም የሥጋን ግድያ በተመለከተ ነው።

# ነፍስን መግደል

ነፍስን መግደል በተለያዩ መንገዶች ይፈጸማል:: ነፍስ ከእግዚአብሔር እንድትለይ ማድረግ መግደል ነው:: ይኸውም ነፍስ ከአምላኮተ እግዚአብሔር ተለይታ በገቢረ ኃጢአት ጸንታ እንድትኖር ማድረግ ነው:: ስለዚህም ለኃጢ አት የተገዛች ነፍስ ምዉት ናት:: እግዚአብሔር በሰሎሞን አድሮ ኃጢአት «ወግታ የጣለቻቸው ብዙ ናቸው፤ እርስ ዋም የገደለቻቸው እጅግ ብዙ ናቸው» በማለት የተናገረው የዚህ ማረጋገጫ ነው:: ምሳ.7÷26::

ጌታችን ከአይሁድ ጋር ሲነጋገር «እናንተ ከአባ ታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ፤ የአባታችሁንም ምኞት ልታ ደርጉ ትወዳላችሁ» በማለት ሰይጣናዊ ስለሆነውና ከእግዚ አብሔር በመለየትም ገዳይ ስለሆነው ክፋታቸው ተና ግሮ አቸዋል:: ሰይጣንም ሰውን በተለመደው መንገድ በሥጋ እንደገደለ አልሰማንም፤ ነገር ግን «እርሱ ከመጀመሪያው ጀምሮ ነፍስ ገዳይ ነበረ» የሚለው ዐረፍተ ነገር ሰይጣን የሰውን ነፍስ እንደሚገድልና ለዘለዓለም በገሃነም እንዲጣል የሚያደርግ መሆኑን ያመለክታል:: ዮሐ.8÷44::

«ፊደል ይገድላል» የሚለው የቅዱስ ጳውሎስ ትምህርት የእግዚአብሔርን ቃል፣ ትእዛዛቱንም በጥሬው እየቀነጻጸሉ በተሳሳተ ትርጉም ሰዎችን በማይገባ መንገድ መምራትና መንፈሳዊ ሕይወትን ወይም ነፍስን ከእግዚ አብሔርና ስለእርሱ ከሚነገረው የቀና ትምህርት በመለየት መግደል መሆኑን የሚያመለክት ነው:: 2ቆሮ.3÷6:: ሰው እውነተኛና ትክክለኛውንም እምነት ከመረዳት የራቀና ከሃይማኖት የወጣ እንደሆነ መንፈሳዊ ሞት /ሞተ ነፍስ/ ደርሶበታል ማለት ነው:: በዚህ መልክ ነፍሳትን እያጠመዱ ከእግዚአብሔር ሕግ በመለየት የኃጢአት ባሪያ ለማድረግ ቀንና ሌሊት የሚደክሙ ዓለማውያን በየዕለቱ ስንት ነፍሳትን እየገደሉ ይውሉ ይሆን? የዚህ ወንጀልና ኃጢአት ተሳታፊና ተባባሪ ከመሆን ይሰውረን::

ከዚህም ሌላ የተሳሳተ ትምህርተ ሃይማኖት በማስተ ማር የሰው መንፈሳዊ ሕይወት በኑፋቄ የሚመርዙና በተዛባ መንገድ የሚመሩ ሰዎችም ነፍሰ ገዳዮች ናቸው:: በቀጥተኛ ሃይማኖት ጸንቶ ምግባር ትሩፋት ሠርቶ የዘለዓለምን ሕይ ወት እንዳይወርስ እንቅፋት ሆነዋልና:: ይህም በሥጋ ከመግደል የከፋ ነው:: በሥጋው የሞተ በነፍሱ የመዳን ዕድል ሊኖረው ይችላል፤ በነፍሱ የሞተ ግን የሚጠብቀው የዘለዓለም መከራ ነው:: በዚህ አንፃር በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩትን ምእመናን ከእውነተኛው የሃይማኖት መንገድ በማስወጣት ለመናፍቅነት የዳረጉአቸው እነአርዮስ፣ መቅዶንዮስ፣ ንስጥ ሮስ፣ ሉተር፣ ይይሆዋ ምስክሮች መሥራች ቻርልስ ራስል ወዘተ እና የእነዚህ ሁሉ ኑፋቄ የወለዳቸው መናፍቃንና ሌሎችም ሁሉ በነፍሰ ገዳይነት ከሚጠየቁት መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው፤ የግድያውን መንገድ የከፈቱት እነርሱ ናቸው::

ስለዚህ ነገረ ሃይማኖትን የሚያስተምር ሁሉ ቀደምት አበው ካስተማሩት የተለየ እንዳይናገር መጠንቀቅ ይገባዋል:: መጽሐፍም «አባቶችህ የሠሩትን የቀድሞውን የድንበር ምልክት አታፍልስ::» ብሏልና:: ምሳ.22÷28:: ሃይማኖት በሰው ፍልስፍና ያልተመሠረተ በሰው በጎ ፈቃድም የማይጸና ሰማያዊ ነውና በምድራዊ ዕውቀት እንደተፈለገ የሚነዳ አይደለም:: እንደተገኘ የሚዘነጠልም አይደለምና እነዚያ «እንደፈለግን እንተረጉማለን» የሚሉ ሁሉ ለብዙዎች ስሕተት ምክንያት በመሆናቸው በነፍሳት መንፈሳዊ ሞት ከመጠየቅ አያመ ልጡም::

የንስሐ ልጆቻቸው የሆኑ ምእመናንን ነቅተው እንዲጠ ብቁ በተሰጣቸው የክህነት ሥልጣን ባለመጠቀምና መንፈሳዊ ትምህርትን ባለማስተማር ልጆቻቸውን ለጠላት ዲያብሎስና ለመናፍቃን አሳልፈው የሚሰጡ ካህናትም ከነፍስ ገዳይ የሚመደቡ ናቸው:: እነዚህን ካህናት እግዚአብሔር «ለእሥራ ኤል ቤት ጠባቂ አድርጌሃለሁ፤ ስለዚህ የአፌን ቃል ስማ ከእኔም ዘንድ አስጠንቅቃቸው:: እኔ ኃጢአተኛውን፦ በእርግጥ ትሞታለህ ባልኩት ጊዜ÷ አንተም ባታስጠነቅቀው ነፍሱም እንድትድን ከክፉ መንገዱ ይመለስ ዘንድ ለኃጢ አተኛው አስጠንቅቀህ ባትነግረው ያ ኃጢአተኛ በኃጢአት ይሞታል፤ ደሙን ግን ከእጅህ እፈልጋለሁ::» በማለት ስለኃላፊነታቸው አስገንዝቦአቸዋል:: ሕዝ.3÷16–18::

በመቀጠልም ኃጢአት ምን ያህል የከፋ መሆኑን ሲ ገልጥ «ነገር ግን አንተ ኃጢአተኛውን ብታስጠነቅቅ እርሱም ከኃጢአትና ከክፉ መንገዱ ባይመለስ÷ በኃጢአቱ ይሞታል÷ አንተ ግን ነፍስህን አድነሃል::» በማለት የካህኑን የመጠበቅ ኃላፊነት ዘርዝሮአል:: ሕዝ.3÷19:: በመሆኑም ካህኑ ሕዝቡን ችላ በማለቱና እያንዳንዳቸውን ባለማስተማሩ ፣ ባለመጠበቁና ባለመከታተሉ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ምውታን ስለሚሆኑ በእግዚአብሔር ዘንድ ስለእነዚህ ነፍሳት ከመጠየቅ አያምልጥም::

ካህኑ የምእመናንን ነፍሳት ከፍርድ ለማዳንና ለጽድቅ እንዲበቁም ለማድረግ በቀንም በሌሊትም ስለ እነርሱ ሕይወት በመጾምና በመጸለይ ኃላፊነቱን በሚገባ መወጣት ይጠበቅበታል:: በራሱ ብቻ የግል ሕይወቱ መል ካም መሆኑ በቂ አይደለም:: ስለዚህም በአደራ ይጠብቃ ቸው ዘንድ ለተሰጡት የምእመናን ነፍሳት ግድ የሌለው ካህን ለውድቀታቸውና ለዘለዓለማዊ ሞታቸው ምክንያት በመሆኑ በእግዚአብሔር ዘንድ በዕዳ መጠየቁ አይቀርም:: በተለይ የምእመናንን ሕይወት ከእውነተኛው ሃይማኖት ለመለየት የሚጥሩ መናፍቃን ባሉበት የካህኑ ኃላፊነት የከበደ ከመሆኑም በላይ በምእመናን ሞተ ነፍስ የተነሣ ተጠያቂነቱም ከፍተኛ ነው::

የክህነት አገልግሎቱን በሚገባ ባለመወጣቱ የተነሣ ቢያስተምራቸው ኖሮ በሃይማኖት ጸንተው በምግባር ተጠ ብቀው በፍርድ ቀንም ዘለዓለማዊ ሕይወትን ማግኘት ሲችሉ

በነፍሳቸው ለዘለዓለም ሞት እንዲዳረጉ ምክንያት የሆነው ካህን ነፍስ ገዳይ ነውና እግዚአብሔርም ይፈርድበታል:: ስለሆነም ለክህነት አገልግሎት የሚመረጠው ሰው በብርቱ ጥንቃቄ የተፈተነና ብቃቱም የተረጋገጠለት መሆን ይኖርበታል:: በሚመራቸው ምእመናን ጉባኤ በመገኘት የማይጎበኛቸውና የማያስተምራቸው ቄስ የነፍሳቸው /የመንፈሳዊ ሕይወታቸው/ ገዳይ ነውና ነፍሰ ገዳዮች እንዳይሾሙ ቤተክርስቲያን ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ አለባት:: እግዚአብሔርም «ሕዝቤ ዕውቀት ከማጣት የተነሣ ጠፍቷል» በማለት የተናገረው ቃል፤ የማያስተምር ሕዝቡንም ወደ እውነት መዳንም ወደሚገኝበት የተቀደሰ ሕይወት የማያደርስ ካህን ስለጠፉት ነፍሳት ተጠያቂ መሆኑን የሚያመለክት ነው:: ሆሴ.4÷6:: ልጆቹን ከማስተማርና ከማስጠንቀቅ ችላ በማለቱ ካህኑ ኤሊም በእግዚአብሔር መቀጣቱ የዚሁ ምሳሌ ነው:: 1ሳሙ.2÷29–34::

ከካህኑ በተጨማሪም ማንም ሰው ለወለዳቸው ልጆቹ መንፈሳዊውን ሕይወትና ፈሪሃ እግዚአብሔርን በያስተምራቸውና ሥርዓት አልባ እንዲሆኑ ቢተዋቸው ስለእነርሱ መንፈሳዊ ጉስቁልና፣ ስለነፍሳቸውም ሞት ከተጠያቂነት ሊድን እንደማይችል ማወቅ አለበት:: ልጆችን ስለማሳደግም «እኔም ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ:: ለልጆችህም አስተምረው÷ በቤትህም ስትቀመጥ÷ በመንገድም ስትሄድ÷ ስትተኛም÷ ስትነሣም ተጫወተው /ተነጋገረው/» በማለት መነገሩ የወላጆችን ኃላፊነት የሚያሳይ ነው:: ዘዳ.6÷6–7::

ማንም የቤተሰብ ኃላፊ እግዚአብሔርን በመፍራትና በጥንቃቄ ልጆቹን ማሳደግ አለበት:: እርሱ የቤተሰቡ ራስ ነውና ስለሚስቱም፣ በቤቱ ስለሚኖሩ ሁሉ ኃላፊነት አለበት:: የሁሉንም መንፈሳዊ ሕይወት በሚገባ ካልመራና ማኅበራዊ ኑሮውን ብቻ የሚመለከት ከሆነ እንደ ኢያሱ «እኔና ቤቴ እግዚአብሔርን እናመልካለን» ለማለት አይችልም:: ኢያ.24÷15:: ስለእነዚህ በግድየለሽነት ስለሚያስተዳድራቸው የቤተሰቡ ነፍሳትም እግዚአብሔር ይጠይቀዋል÷ በነፍስ ገድሏቸዋልና:: እንዲህ ዓይነቱ ሰው ጋብቻና ትዳር መንፈሳዊና ሰማያዊ መሆኑን ዘንግቶ ቤቱን «አነስተኛ ሲኦል» አድርጓታል:: ከልጆቹ አንድ እንኳን የእግዚአብሔርን መንገድ መከተል ቢፈልግ ብዙ መከራ መቀበል አለበት:: ይህን የመሰለው አባት በፍርድ ቀን ከመጠየቅ አይድንም:: ከሁሉ ነገር በፊት ጋብቻ መንፈሳዊና ለእግዚአብሔርና ለቤተክርስቲያን የሚያገለግሉ ፍሬዎች የሚገኙበት መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው:: ይህን በመገንዘብ ልጆቻቸውን በቀና ሃይማኖት አጽንተው በሥነ ምግባር አሳድገው በመንፈሳዊ የሕይወት ጎዳና የሚመሩትን አባቶች ሁሉ በአድናቆትና በታላቅ ክብር እንመለከታቸዋለን:: እነርሱ ረቂቁንና ከእነርሱ የሚጠበቀውን መንፈሳዊ ግዴታ የተረዱና የጋብቻቸውን ዋና ዓላማም ጠንቅቀው ያውቁ ናቸው::

ለልጆቻቸው የመጥፎ ሥራ፣ የክፉ ምግባርም ምሳሌ የሚሆኑ፤ በቤት ውስጥም ዘወትር የሚጨቃጨቁና ክፉ ቃላትን በመመላለስ የሚነጋገሩ፤ በቤታቸውም ሰላም የሌላቸው ወላጆች የልጆቻቸውን የኑሮ አቅጣጫ በማበላሸት ለውድቀታቸው ከፍተኛ የሆነ ተጽእኖ ያደርጋሉ። እነዚህ ወላጆችም ልጆቻችንን አልገደልንም ለማለት አይችሉም። እነርሱም የልጆቻቸውን የመንፈሳዊ ሕይወት ተስፋ ገድለውታል፤ አጨልመውታል፤ ለልጆቻቸው ያሳዩአቸውና በአእምሮአቸው ውስጥ የቀረፁት እግዚአብሔር የማይወደውንና የትእዛዛቱም ተቃራኒ የሆነውን ዓለማዊና ሥጋዊ ምግባር ነውና።

ስለዚህ ወላጆች በአነጋገራቸው፣ በአለባበሳቸው፣ በኑሮአቸው በአመጋገባቸው፣ በሥርዓትና በምግባራቸው ሁሉ የልጆቻቸውን መንፈሳዊ ሕይወት በማበላሸት የገሃነም ባሮች በማድረግ ለዘለዓለም እንዳይገድሏቸው መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል። መግደል የአንድን አካላዊ ሕይወት ሕልውና ማጥፋት ብቻ ወይም ምድራዊ ሕይወቱን ማሳለፍ ብቻ እንዳ ይመስለን፤ የአንድን ሰው ሃሳብ ማጥፋት መንፈሳዊ ሕይወቱ ለዘለዓለም ወደማይወጣበት የሞት ኑሮ መጨመርም ነፍሰ ገዳይነት መሆኑን ማወቅ ይገባል።

አንድ ሰው ኃጢአትን እንዲሠራ ምቹ ሁኔታ መፍጠርና ማሰናከልም የነፍስ ግድያ ነው። ሰው በእኛ ምክንያት በኃጢአት የወደቀ እንደሆነ በኃጢአቱ የተነሣ ምዉት ነውና ይህን ሰው የገደልነው እኛ መሆናችንን ማወቅ ያስፈልጋል፤ ለውድቀቱ ምክንያት ነንና። ስለዚህም እግዚአብሔር ይጠይቀናል። በመጽሐፍም «በእኔም ከሚያምኑ ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ÷ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታሥሮ ወደ ጥልቅ ባሕር መስጠም ይሻለው ነበር፤ ወዮ ለዓለም ስለማሰናከያ፣ ማሰናከያ ሳይመጣ አይቀርምና፤– ነገር ግን በእርሱ ጠንቅ ማሰናከያ ለሚመጣበት ለዚያ ሰው ወዮለት።» በማለት ጌታችን የተናገረው የሚያመለክተው ይህንኑ ነው። ማቴ.18÷6–7።

በመሆኑም ሰዎችን ከመንፈሳዊ ጉዞአቸው እንዳናሰናክልና በፍርድ ቀን በእግዚአብሔር ፊት እንዳንጠየቅ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ክርስቶስ ስለፍርድ ቀን ባስተማረበት አንቀጽ ኃጢአት ከሠሩ ይልቅ ለኃጢአት ምክንያት የሆኑትን አስቀድሞ አውስቷቸዋል፤ «የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል÷ ከመንግሥቱም እንቅፋትን ሁሉ አመፃንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ÷ ወደ እቶን እሳትም ይጥሏቸዋል፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።» በማለት የሚያሰናክሉ ቅጣታቸው ከፍተኛ መሆኑን ገልጧል። ማቴ.13÷41–42።

## ራስን መግደል

ራስን መግደል ሌሎችን ከመግደል እኩል ነው። ሰው የነፍሱ ባለቤት አይደለም፤ በነፍሱም ላይ የወደደውን ሊያደርግ ሥልጣን የለውም። የሰው ነፍሱ የእግዚአብሔር ገንዘብ ናት፤ በክርስቶስ ደም፣ በቤዛነቱ ወደቀደመ ክብሯ ለመመለስ የበቃች የእግዚአብሔር ሀብት ናት። የፈጠራ

ትም እርሱ እግዚአብሔር ነው። ሰው እንደፈለገ ሊያደርጋት ሳይሆን ለእግዚአብሔር ለስሙም ክብር የተፈጠረች እርሱንም በማመስገን ጸንታ እንድትኖር የተሰጠች ስጦታ ናት። ስለዚህ ነው ራሱን የገደለ ሰው በቤተ ክርስቲያን ጸሎተ ፍትሐት የማይደረግለት። ይህ ሰው በንስሐ ሊፈወስ /ሊድን/ የማይችል ኃጢአት ሠርቶ ነው የሞተው።

ተስፋ መቁረጥም ደግሞ ራስን እንደመግደል የሚቆጠር ነው። አስተዋይ ሰው ተስፋ አይቆርጥም፤ እግዚአብሔር ፈጽሞ እንደማይተወው ያውቃልና። ራሱን የሚገድል ሰው ተስፋው የተሟጠጠ ነው። ተስፋ መቁረጥ ደግሞ በራሱ ኃጢአት ነው፤ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ምሕረት ቸል ማለት ነውና። ይህም በእግዚአብሔር ፍቅር፣ ጥበቃና ታዳጊነት ላይ እምነት በማጣትና በመጠራጠር የሚመጣ

ራስን መግደል ትዕግሥት ማጣትንም ያመለክታል። ከሞት በኋላ ያለውን ሕይወት አለማመንንም የሚያመለክት ነው። ከሞት በኋላ ያለውን ሕይወት የሚያምን ቢሆን ኖሮ ራሱን ከማጥፋት ከመከልከሉም በላይ ራሱን በመግደሉ ወደዘለዓለም ስቃይ ወደገሃነም እሳት መውረዱን ያስተውል ነበር። ከችግር እላቀቃለሁ በማለት ራሱን የሚገድል ሰው ከችግሩ አይገላገልም፤ ይልቁኑ ወደባሰና ወደተወሳሰበ ሌላ ችግር ነው የሚገባው «ከድጡ ወደማጡ» እንዲሉ። ራስን መግደል ችግርን ለማቃለል መንፈሳዊም ሆነ ተግባራዊ መፍትሔ ሊሆን አይችልም። ራሱን የሚገድል ሰው የአእምሮ በሽታ ያለበትና አስተሳሰቡ የተዛባ ነው። ራስን መግደል ነፍስን በተግባር ማጥፋት ነውና አትግደል ለሚለው ትእዛዝ ተቃራኒ ነው።

ሰዎች ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ጤናማና ንጹሕ ሰውነትና ሙሉ አካል በማጎሳቆልና እግዚአብሔርም ለማይደሰትበት ተግባር በማዋል በተዘዋዋሪ ራሳቸውን ይገድላሉ። ክርስትና እግዚአብሔር የፈጠረልንን አካላችንን እንድናጎሳቁል አይፈቅድም። ክርስትና የሚያዝዘው የሥጋ ፍላጎትን በማሸነፍና በመቆጣጠር ለሕገ እግዚአብሔር ማስገዛትና በዚህ ሂደት ምግባር ትሩፋትን እየሠራን የእምነት ጥንካሬን ገንዘብ እንድናደርግ ነው። በመጽሐፍ እንደ ተጻፈው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ስለአንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን» እንዲሁም «ስለዚህ ሞቱ በእኛ... ይሠራል» ያለውና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ደግሞ «የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች፤ ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች።» በማለት መናገሩ አካልን ስለማጎሳቆል ሳይሆን የሥጋን ፈቃድ ስለመግደል የተነገረ ነው። ሮሜ.8÷36። 2ቆሮ.4÷12። ዮሐ.12÷24። የሥጋ ፍላጎትን መግደል ማለትም ከፈቃደ ነፍስ ጋር የሚቃረነውን ፍትወተ ሥጋ ማስቀረት ነው እንጂ ሞተ ሥጋ ማለት አይደለም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ።» በማለት ያስተማረው ሥጋን ለፈቃደ ነፍስ ስለማስገዛት ነው። 1ቆሮ.9÷27።

በቅዱስ መጽሐፍ ሰው ሥጋውን «ይመግበዋል ይከባከበውማል» ተብሎ እንደተጻፈ፤ በዚያ ቀን እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገውን እንድንሠራ ስለሰውነታችንም ዕረፍት የሰንበትን ሕግ ሰጥቶናል:: ኤፌ.5÷29:: መድኃኒታችንም ብዙ ድውያንን የፈወሰው ስለሰው አካል ጤንነት የሚያስብ በመሆኑ ነው:: ስሙን ለማመስገን ክብሩንም ለመግለጥ እን ድንችል እግዚአብሔር ጤናማ አካላችንን ይፈልጋል:: ጤናማ አካል ቆሞ ለመጸለይ፣ ለመስገድ፣ ነቅቶ ለመቆየት፣ ሰዎችን ለማገልገል፣ ለመጸም፣ ይረዳል:: ስለሆነም በእግዚአብሔር ፊት የተወደደ አገልግሎትን ለመፈጸምና የዘለዓለምን ክብር ለመውረስ ሰው ሁሉ አካሉን በጤና መጠበቅ አለበት እንጂ በግድየለሽነትና በቸልታ አካሉን እያጎሳቆለ ሸባ ሊያደርገው አያስፈልግም አካሉ የእግዚአብሔር ገንዘብ ነውና:: 1ቆሮ.6÷20::

በዚህ መልክ ሰዎች አካላቸውን በማጎሳቆል ራሳቸውን ከሚገድሉባቸው መንገዶች መካከል በመጠጥ ብዛት በመስ ከር፣ በማጨስ፣ የሱስ ምንጮች የሆኑ ዕፅዋትን በመብላትና የመሳሰሉት ይገኙበታል:: እነዚህ ሁሉ ቀስ በቀስ የሰውን አካል በማዳከም ለጽድቅ ሥራ ቀርቶ ቆሞ ለመሄድ ከማ ይቻልበት ደረጃ በማድረስ ወደሞት የሚያንጉዙ ናቸው::

ከሁሉ የከፋው ራስን የመግደል ዓይነት ግን ኃጢ አትን መሥራት ነው:: ኃጢአት ሞት ነውና ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «በበደላችን ምውታን ነበርን» «የኃጢአትም ደሞዝ ነው» «ስለሥጋ ማሰብ ሞት ነውና» እንዳለ:: ኤፌ.2÷5:: ሮሜ.6÷32:: ሮሜ6÷8:: በዚህ መሠረትም ሰው ኃጢአትን በመሥራት መንፈሳዊ ማንነቱን ይገድላል:: ይህ ሞትም ነፍሱን ከእግዚአብሔር በመለየት ወደ ሲኦል ቀጥሎም ወደገሃነም እሳት እንድትጣል፣ ለዘለዓለምም ያለተስፋ እንድትቀር ያደርጋታል::

ስለሆነም ኃጢአት ሰው ራሱን የሚያጠፋበት መንፈሳዊ /ረቂት/ ግድያ ነው:: ሰው ከኃጢአት የተነሣ ከመንፈሳውያን ምግባራት፣ ከጸም፣ ከጸሎት፣ ከመስገድ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከመመልከት፣ከኑዛዜ፣ ከሥጋውና ከደሙ፣ ከሌሎችም ጸጋና ድኅነት ከሚገኝባቸው ምግባራት የተለየ እንደሆነ መንፈሳዊ ማንነቱን /ነፍሱን/ ገድሏል::

የራሱን ሥጋዊ ፍላጎት ተከትሎ ለጊዜያዊና ምድራዊ ለሚያልፍም እርካታ ብሎ ወደዓለም ያጋደለ ፈቃደ ነፍሱንም የተወ ሰው አምስተኛውን ትእዛዝ በመተላለፍ የራ ሱን ነፍስ ገድሏል። በወንጌልም «ነፍሱን የሚያገኝ ያጠፋታል» ቲብሎ የተነገረው ለእንደዚህ ዓይነቱ ሰው ነው። ማቴ.10÷39። ለምድራዊ ተድላ ሲሮጥ፤ ለሚያልፍ ጊዜያዊ እርካታ ሲደክም የዘለዓለም ሞትን ገንዘብ አድርጓልና። ስለዚህ «አትግደል» የሚለውን ሕግ ስፋትና ጥልቀት ከራሳችን ማንነት ጋር በማገናዘብ ከመግደል ተጠብቀን ልንኖር ይገባናል።

# ሰድስተኛው ትእዛዝ
## አታመንዝር

ማመንዘር ሁለት ዋና ዋና ትርጉም አሉት እነዚህም

1. አንድ ሰው የራሱ የኑሮ ጓደኛ ካልሆነ ሰው /ባለ ወይም ሚስት/ ጋር ቢገናኝ አመንዝራ ይባላል:: ይኸውም በብሉይ ኪዳን የሞት ፍርድ ሊያስፈርድበት ይችል ነበር:: /ዘሌ 20:10/:: በሐዲስ ኪዳን ደግሞ ከሰማያዊ መንግሥት ይለያል:: ሰፋና ዘር ዘር ብሎ ሲተረጉምም

ሀ. ከአንድ በላይ ማግባት

በአዲስ ኪዳን አንዲት ሚስት ለአንድ ባል ለአንዲት ሚስት የሚለው ሕግ ጸንቷል:: "... ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው ለእያንዳንዲቱ ደግሞ ለራስዋ ባል ይኑራት " ማቴ7:2:: በመሆኑም ምንም በቂ ሐብትና ንብረት ቢኖረው ሁሉንም እኩል እወዳለሁ አስተዳድራለሁ ቢል ከአንድ በላይ ያገባ ሁሉ /ወንድም ሆነ ሴት / አመንዝራ ነው::

ከጋብቻ ውጭ ግንኙነት መፈጸም

ይኸኛውን ደግሞ እንደገና በተለያዩ መንገዶች መመልከት ይቻላል:: የመጀመሪያው /ሚስት ወይም ባል እያለው ወደ ሌላ የሚሄድ ማለት/ ካገባት ሚስቱ ወይም ከአገባችው ባሏ ውጭ ግንኙነት የሚፈጽሙ አመንዝራ ነው:: ሁለተኛው ትርጉሙ ደግሞ አንድ ሰው ጋብቻ ከመፈጸሙ በፊት ከእጮኛው ሊሆን ወይም ላይሆንም ይችላል/ የሚፈጽመው ግንኙነት ሁሉ ዝሙት ነው:: ከዚያ በፊት የሚፈጸመው ሁሉ ግን ሕጋዊ አይደለምና ዝሙት ወይም ማመንዘር ይባላል::

ሐ. የቅርብ ዘመድ ማግባት

ሕገ ቤተክርስቲያን ጋብቻ እንዲፈጽም ከሚፈቅድበት የዝምድና ገደብ ውጪ ከቅርብ ዘመድ ጋር የማፈጸም ጋብቻ ዝሙት /አመንዝራነት/ ነው:: ይኸውም እስከ ሰባት ትውልድ የሚደርስ የሥጋ ዝምድና ወይም በክርስትና ማንሣትና መነሣት የሚፈጠር የመንፈስ ዝምድና ሊሆን ይችላል:: ማር 6:18 ዘሌ 18:6

መ. ሕግ ከሚፈቅደው ውጭ በዝሙት ወይም የተፈታውን/ችውን/ ማግባት

ከሁለት አንዱ በዝሙት ተገኝቶ ወይንም በሞት ተለይቶ ካልሆነ በቀር መፍታት ማመንዘር ነው:: ሕገ እግዚአብሔር ከሚፈቅደው ውጪ በሞት መለየት ወይም በዝሙት ምክንያት ሳይሆን መፍታት ማመንዘር ነው:: እንዲሁም ያለ ሕግ የተፈታችውን ማግባት ከዚህ የተለየ አይደለም:: "ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱንም ፈትቶ ሌላይቱንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል" "ሚስቱንም ፈትቶ ሌላይቱንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል" ማቴ 19:9 ሉቃ 16:18:: ስለሆነም በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት በዝሙት ምክንያት ብቻ ከተፈቀደው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ፍቺ ውጭ ራሱንም ሆነ ሌሎችን ሊያሳምን ይችላል ተብሎ በሚታሰብ በማናቸውም ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሰው ፍቺው በክርስትና ሕግ ተቀባይነት የለውም:: ጋብቻውም እንዳልፈረሰ ጋብቻ ይቆጠራል:: ቢያገባም በሚስቱ ላይ ሁለተኛ እንደደረበ እንዳመነዘረም ይቆጠራል::

ሠ. ምኞት

አንድ ሰው /ሴት ወይም ወንድ/ በማይገባ መመልከት /ለዝሙት መፈለግ / ማመንዘር ነው:: ምንም እንኳን ይህ ሰው በግብር ባይፈጽመውም ተመኝቷል ቢመቸው ሊፈጽመው ይችላልና በልቡ አመንዝሯል:: "ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመለከታትም ያን ጊዜ በልቡ ከርሷ ጋር አመነዘረ" ማቴ 5:28

አንድ ሰው እግዚአብሔር ትቶ ሌላ አምላክ ሲያመልክ አመነዘረ ይባላል:: ይህም ጣኦት ማምለክንና እምነት መቀየር /ከእውነተኛው ሃይማኖት ወጥቶ ወደ ሌላ መሄድን/ ያጠቃልላል:: ኤር 3:8-9 ያዕ1 ማቴ 12:39:: በዘመነ መሳፍንት እሥራኤል ጣዖትን ባመለኩ ጊዜ "ሌሎች አማልክትን ተከትለው አመነዘሩ ስገዱላቸውም እንደ መሳፍንቶቻቸውን አልሰሙም" ተብለዋል:: መሳ.2:17::

በማናቸውም መንገድ ቢተረጉም ማመንዘር ከባድ ኃጢአት ነው:: ይህንንም ቅዱስ ጳውሎስ ሲገልጥ "ከዝሙት ሽሹ ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ወጭ ነው:: ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሠራል::" 1ቆሮ 6:18 :: የዚህም ሰው ሥጋው ላይ የሚሠራው ኃጢአት አስከፊነትም በሁለት ምክንያቶች ነው::

የመጀመሪያው የሰው አካል የእግዚአብሔር አካል /ብልት/ በመሆኑ ነው:: ለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ "ሥጋችሁ የክርስቶስ ብልቶች እንደሆነ አታወቁምን?" በማለት ተናግሯል:: 1ቆሮ6:15::

ሁለተኛው ደግሞ "ሰውነታችን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በመሆኑ ነው:: ይህንንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ አታውቁምን . . . ለራሳችሁ አይደላችሁም ስለዚህም በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ!" "እናንተ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ናችሁ::" የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ አታውቁምን? ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና ያውም እናንተ ናችሁ" በማለት ገልጿል:: 1ቆሮ 6:16 6:19-20 3:16-17

በመሆኑም ይህ ቅዱስ የሆነ ሰውነት በዝሙት ሊቆሽሽ ወይም የእግዚአብሔር ማደሪያ መሆን ሲገባው ለሌላ አምላክ ሊገዛ አይገባውም ማመንዘር በሰማይ ከእግዚአብሔር መንግሥት ይለያል:: በምድርም ደግሞ ከፍተኛ ሥቃይን ያስከትላል:: ለምሳሌ እግዚአብሔር በዓለም ላይ ካመጣቸው መቅሰፍቶች መካከል ዋነኞቹ ከዝሙት የተነሣ የደረሱ ናቸው:: የጥፋት ውኃ /ዘፍ 6:7 የሰዶምና የገሞራ ጥፋት /ዘፍ19/:: /በብንያም ነገድ የነበረው ጥፋት መሳ20 በቆሮንቶሱ ሰው ላይ የተወሰነው ብያኔ 1ቆሮ4:5 በአመንዝራነት የተነሣ የመጡ ቅጣቶች ናቸው:: ይህም ሳይበቃው አመንዝራ ሰው ሰማያዊ ቅጣትም የሚጠብቀው መሆኑን ሲገልጽ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «አትሳቱ ሴሰኞች ቢሆኑ ወይም ጣዖት የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም» ብሏል::" 1 ቆሮ 6:9-10

ከአረማዊነት ወደ ክርስትናው የተመለሱትም በመጀመሪያይቱ የሐዋርያት ጉባኤ ከዚህ እንዲጠበቁ ታዝዘዋል:: ስለዚህ ከአሕዛብ ወደ እግዚአብሔር የዞሩትን እንዳናስቸግራቸው ነገር ግን ከጣዖት ርኩሰትና ከዝሙት ይርቁ ዘንድ እንድንጽፍላቸው እቆርጣለሁ:: የሐዋ 15:19-20:: ስለዚህ በምድርም ላለመጎዳት ከሰማያዊም መንግሥት ላለመለየት ራስን ከአመንዝራነት መጠበቅ ያስፈልጋል:: ለዚህም ልቦናን ለፍቅረ እግዚአብሔር ማስገዛት በቃለ እግዚአብሔር መታነጽ በጾምና በጸሎት መትጋት ዘወትርም ንስሐ እየገቡ ቅዱስ ቊርባን መቀበል ይገባል:: እንዲሁም ወደ አመንዝራነት ከሚመሩ ነገሮች መራቅም ያስፈልጋል:: የክህደት መጻሕፍትና ዘፈኖች መራቅ ይገባል::

ጠላት ዲያቢሎስ ሰዎችን ለዝሙት አዘቅት የሚዳርጋቸው ስሜታቸውን ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ በመሳብ ነው:: በመሆኑም በመንፈሳዊ ኑሮ ራስን አንጾ በጾም በጸሎት ሰውነትን ቀጥቶ የሰው ልጅን ስሜት ላልተፈለገ ነገር ከሚቀሰቅሱ ዘፈን የዝሙት ፊልም ያልተገባ የጾታ መቀራረብ እጾችን መጠጥ እና ቅንጦት ራስን በመጠበቅ ለሰማያዊ ክብር መብቃት ይገባናል ዝሙትን ማሸነፍ ሰማዕትነት ነው:: ስለዚህም ፈተና ተጋድሎ ይጠይቀናል ለጊዜአዊ ነገር ብለን ዘላለማዊ ነገር እንዳናጣ እንጋደል::

## ሰባተኛው ትእዛዝ

## አትስረቅ

እግዚአብሔር አስቀድሞ የሰው ልጆች ትእዛዙን እንዳይተላለፉ ካስቀመጠላቸው ሕግጋት መካከል አንዱ ነው:: እግዚአብሔር ያዘዘን በወዛችን ጥረን ግረን እንድንበላ እንጂ የሌላውን /የሰውንም ሆነ የእግዚአብሔርን/ እየሰረቅን እንድንበላ አይደለም:: ዘፍ 3:19:: ለዚህም ነው "አትስረቅ" ሲል ቃሉን ያወጀው:: ይህ ትእዛዝ በጽሑፍ ከመሰጠቱም በፊት ስርቆት ኃጢአት መሆኑ በሕገ ልቡና ይታወቅ ነበር:: ዘፍ 31: 30:: ስርቆትና ሌብነት ተመሳሳይ ሲሆኑ ስርቆት ሰፋ ይላል:: ሌብነት የራስ ያልሆነን ንብረት ባለቤቱ ሳያይ ተደብቆ ያለ ባለቤቱ ፈቃድ መውሰድ ሲሆን ስርቆት ግን ከዚህ በተጨማሪም መስጠት የሚገባን አለመስጠትን ወይም ማድረግ የሚገባን አለማድረግ ያጠቃልላል:: ለምሳሌ አንድ ሰው አሥራት ማውጣት ሲገባው ባያወጣ እግዚአብሔር እንደሰረቀ ይቆጠራል:: ሚል3:7:: ስርቆት ከመፈጸሙ በፊትም ሆነ ከተፈጸመ በኋላ ከሌሎች ኃጢአቶች ጋር ይያያዛል:: ከመፈጸሙ በፊት "የባልንጀራህን ቤት አትመኝ" ከሚለው ጋር ከተፈጸመ በኋላ ደግሞ "የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ" ከሚለው እና "በሐሰት አትናገር" ከሚለው ጋር ይገናኛል:: ምክንያቱም አንድ ሰው የባልጀራውን ንብረት ሰው አየኝ አላየኝ እያለ የሚሰርቀው የእግዚአብሔርን ቃል ተላልፎ በሚያዝበት ጊዜ "ፈጽሞ አላየሁም" ብሎ ይዋሻል ሐሰት ይናገራል:: ነገሩንም እውነት ለማስመሰል መሐላ እየደረደረ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ ይጠራል:: ከዚህም በላይ ስርቆት ከነፍስ ግድያም ጋር ይያያዛል:: ምክንያቱም ሌባ ጨለማ ለብሶ አጥር አፍርሶ በሚሰርቅበት ወይም አሳቻ ሥፍራ ጠብቆ በሚዘርፍበት ጊዜ ባለቤቱ ከነቃበት ወይም ከከለከለው ሊገድለው የሚቻልበት አጋጣሚም ሊኖር ይችላልና:: እንዲያውም

አንዳንዶች ሆን ብለው ስርቆት በሚፈጽሙበት ጊዜ ማጅራት መትተው በስለት ወግተው ከገደሉ በኋላ ቢሆኑም ይህንኑ ያጐላል:: የስርቆት ዓይነት ብዙ ቢሆንም ጠቅለል ተደርጐ በሁለት ሊከፈል ይችላል::

**1 ከእግዚአሔር መስረቅ**

ሰዎች ብዙውን ጊዜ ስርቆት የሚመስላቸው ከሰው ሲሆን ብቻ ነው:: ነገር ግን የሰው ልጅ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከእግዚአብሔር ይሰርቃል::

አስራቱንና በኵራቱን አውጥተን ለእግዚአብሐር መስጠት ሲገባን ለፈቃደ ሥጋ በማድላት ለራስ መስቀረት ስርቆት ነው:: ይኽንን በተመለከተ በነቢዩ በሚልክያስ አንደበት "ወደ እኔ ተመለሱ እኔም ወደ እናንተ እመለሰሰሁ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአበሐር እናንተም የምንመለሰው በምንድር ነው ብላችኋል ሰወ እግዚአብሔርን ይሰርቃልን? እናንተ ግን እኔን ሰርቃችኋል" ተብሎ ተነግሯል:: ሚል 3:7:: በተጨማሪም ለመንፈሳዊ አገልግሎት ልናውለው የሚባንን ገዜ ለሥጋዊ አገልግሎት ማዋል ይህም የእግዚአብሔርን ሰዓት መስረቅ ነው:: ምክንያቱም አሥራት ማውጣት ከገንዘብ ከእህልና ከእንስሳት ብቻ ሳይሆን ከጊዜም ነውና:: ለምሳሌ ጥንት እግዚአብሔር ሰባተኛውን ቀን የባረከውና የቀደሰው ያ ቀን የእርሱ ቀን ስለሆነ ነው:: እንዲሁም የስርቆት ኃጢአት እየተለመደ ፈሪሃ እግዚአብሔርም እየጠፋ ሲሄድ ወደ ሰው ቤት ብቻ ይመለከት የነበረው ዓይን ወደ እግዚአብሐር ቤትም መመልከት ይጀምራል:: ስርቆቱንም በንግሥ ጊዜ ከሚጋፋ ምእመናን ኪስ በማውለቅ እና የአስቀዳሾችን ጫማ በመሰረቅ ተሳላሚ መስለው ከሙዳየ ምጽዋት ወደ መስረቅ ይሸጋገራሉ:: ቀጥለውም ወደ ንዋያተ ቅድሳቱ ያተኩራሉ:: ሰርቀውም ለቤተክርስቲያን ጠላቶች አሳልፈው ይሰጣሉ::

ከዚህም ሌላ የእግዚአብሐር በግ /ምእመንን/ ከእግዚአበሐር ቤት መለየት /መናፍቅ ማድረግ/ ስርቆት ነው:: ይህም ምእመናንን ድኅነት ከሚያገኙበት የሃይማኖት ጉዞ እንዲለዩ ከእውነተኛውም መንገድ እንዲወጡ የሐሰት ትምህርት በማስተማር የሚፈጸም ነው:: እንደዚህ ዓይነቱም ሌባ የነፍስ ሌባ ይባላል:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ከእኔ በፊት የመጡት ሁሉ ሌቦችና ወንበዴዎች ናቸው:: ሲል የተናገረው የተሳሳተ ትምህርት ያስተምሩ የነበሩት መምህራን መምህራነ ሐሰት እንደሆነ የታወቀ ነው:: ዮሐ 10:8:: ይህንንም ሲያብራራ ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም ብሏል:: ዮሐ 10:10:: ለዚህም ነው "የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውስጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኩላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ:: ያለው ማቴ 7: 15:: ቅዱስ ጳውሎስም "በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጐ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ:: ከሄድሁ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች እንዲገቡባችሁ ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገር የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሱ እኔ አውቃለሁ::" ብሏል የሐዋ20:28-30:: በመሆኑም መናፍቃን የነፍስ ሌቦች ናቸው::

**2 ከሰው መስረቅ**

ሌባ የአንድ ሰው /ግለሰብ/ ሀብት ንብረቱ ሳያይ ሊሰርቅ ኀብረተሰቡ /ሕዝቡ/ የሰጠውን አደራ ላይወጣ ወይም ደግሞ ከመንግሥት የተሰጠውን ኃላፊነት ለግል ጥቅም ሊያውል ይችላል:: ይህ ሁሉ ስርቆት ነው::

ለምሳሌ :- ለመሥሪያ ቤት ሥራ የተገዙ ወይም የተሰጡ ንብረቶችን ያለፈቃድ በግል ጥቅም ማዋል

- የተዋሱትን ዕቃ ወይም ንብረት በጊዜው ባለመመለስ ለባለንብረት በጊዜው ባለመመለስ ባለ ንብረቱ ሲረሳው እንደግል ንብረት መጠቀም፣
- የተበላሸውን ዕቃ ደህና አስመስሎ በማጭበርበር መሸጥ፣

- ትክክል ባልሆነ መለኪያ ሚዛን ወዘተ መሸጥ፣
- ለሠራተኛ ከሚገባው በታች እየከፈሉ ጉልበቱን መበዝበዝ፣
- በሥራ ጊዜ በሰዓቱ አለመገኘት የሥራ ጊዜን በመዝናናት ማሳለፍ ሕጋዊ ያልሆነ የሕመም ፈቃድ ማውጣት ሥራን መሥራት እየቻሉ ከግዴለሽነት የተነሣ በተገቢው ጥራት አለመሥራት ከመግቢያ ሰዓት ዘግይቶ መግባትና ከመውጫ ሰዓት ሳያስፈቅዱ ቀድሞ መውጣት፣
- ከሌላ የተገኘውን ሃሳብ እንደራስ አድርገ ማቅረብ ከሌላ የወሰዱትን ጥቅስ አባባል ድርሰት ወዘተ የፈጠሩት በማስመሰል ማቅረብ፣
- ያልተፈቀደ የሰውን ምሥጢር በድብቅ መስለልና ማየት፣
- የሰውን ገንዘብ ያለ አግባብ መበዝበዝ ወይም ጉቦ መቀበል፣
- ከሌባ ጋር መተባበር /ምሳ 29:24/ ወዘተ

በአጠቃላይ የእኛ ያልሆነውን ነገር ያለ አግባብ መውሰድ ሁሉ ስርቆት ነው:: እንዲህም ሲልና የስርቆት ነገር ሲነሣ እኛን የማይመለከት የሚመስለን ሰዎች እንኖራለን:: ይሁን እንጂ ከላይ እንደተመለከትናቸው ስርቆት የማይመለከተው ሰው አለ ማለት በጣም አስቸጋሪ ነው:: ለምሳሌ በስንፍና የሥራ ሰዓት አሳልፎ መግባት እና ሰዓቱ ሳይደርስ መውጣት ሳይታመሙ ታምሜአለሁ ያልሞተን ዘመድ ሞቷል እያሉ ከሥራ መቅረት ወዘተ ከመለመዱ የተነሣ ብዙዎች ኃጢአት ሳይመስላቸው የሚፈጽሙት ነው:: እንዲሁም አንድ የመሥሪያ ቤቱ የዕቃ ግዢ ክፍል ሠራተኛ የሆነ ሰው አሮጌ ቢገዛ ወይም ያልተገዛበትን ዋጋ በደረሰኝ ቢያሠራ የሰረቀ አይመስለውም::

ወደ ነጋዴውም ኅብረተሰብ ስንገባ የባሰ እንጂ የተሻለ ነገር አናገኝም:: በሜትርና በሚዛን ከማጭበርበር አልፈው ብዙ ሲሰሩ እናገኛቸዋለን:: እህል ነጋዴው አፈርና ገለባ ይደባልቅበታል ኪሎ እንዲያነሣም ውኃ ያርከፈክፍበታል:: በርበሬ ነጋዴው ሽክላ ቅቤ ነጋዴው ደግሞ ሙዝ ድንች ይቀላቅላል:: አሮጌውን እንደ አዲስ የሚሸጠውን እጅ መንሻ መስጠት ሕጋዊ ያልሆነውን ንግድ የሚያካሂደውን ቤት ይቁጠረው:: ይህ ሁሉ የራስ ያልሆነው አለአግባብ መውሰድ ነውና ስርቆት ነው:: ለመሆኑ ሰዎች ለምን ይሰርቃሉ? አንድ ሰው ወደ ስርቆት ኃጢአት የሚገፋፉት ነገሮች/ ምንጮች/ ምንድን ናቸው?

1. ምኞት:- ያልተሰጠንና የራስ ያልሆነውን ነገር ወይም ያዩትን ሁሉ ለራስ እንዲሆን መመኘት ወደ ስርቆት ያመራል:: አንድ ገንዘብ የሌለው ሰው ገንዘብ ሳይኖረው ብዙ ነገሮች እንዲያሟሉለት ቁጭ ብሎ ማይሰራ የሚመኝ ከሆነ የግድ ያንን የፈለገውን ነገር ለማሟላት ወደ ስርቆት ሊያመራ ይችላል:: ፊልጵ 4:11
2. ችግር :- አንዳንድ ሰዎች ሳይወዱ በችግር ምክንያት ሲሰርቁ ይችላሉ:: ለምን እንደሠረቁም ሲጠየቁ ቸግሮኝ ነው ይላሉ:: ይሁን እንጂ ቢቸግርም ጠይቆ /ለምኖ/ መውሰድ /ማግኘት/ ሲቻል መስረቅ አይገባም::
3. አለማወቅ:- አንዳንድ ሰዎች ከላይ እንደተገለጠው ባለማወቅ በየዕለቱ የሚሰርቁት ነገር ሁሉ ስርቆት አይመስላቸውም:: የሥራን ሰዓት አለማክበራቸው አሥራት አለማውጣታቸው በገንዘብ በዕውቀትና በጉልበታቸው እግዚአብሔር አለማገልገላቸው ስርቆት አይመስለቸውም:: ይሁን እንጂ አለማወቅ ከፍርድ አያድንም:: ሮሜ 2:12-16
4. ያለ አቅም መኖር :- አንዳንድ ሰዎች እንደራሳቸው ገቢና እንደ አቅማቸው ሳይሆን እንደ ጉረቤታቸው ወይም እንደሚያዩት መኖር ይወዳሉ:: የሚለብሱት የሚመገቡት የሚገለገሉበት የቤት ዕቃ መኖሪያቸው ሁሉ እንደ ገቢያቸው ሳይሆን ከአቅማቸው በላይ ይሆናል:: በዚህም የተነሣ የመንግሥት ንብረት ሲዘርፉ እጅ መንሻ ሲቀበሉ ሲያጭበረብሩ አለያም በግልጽ ሲሰርቁ ይታያሉ::
5. የኅብረተሰቡ አመለካከት:- ጥንት ኅብረተሰቡ ስርቆትን /ሌብነትን/ በጣም ያወግዝ ነበር:: በዚህም የተነሣ የራስ ያልሆነን ነገር ወድቆ እንኳን ቢያገኙ መውሰድ የተወገዘ ነበር:: ማንም ሰው የራሱ ያልሆነውን አይፈልግም:: እያደር

ስርቆት እየተለመደና ሌባውም ትንሽ ተቀጥቶ ሲፈታ ይህ አመለካከት እየተለወጠ መጣ:: በዚህም ምክንያት ጉቦ መቀበል በሥልጣን ያለ አግባብ መጠቀም የመንግሥትን ንብረት ለግል ጥቅም ማዋል ወዘተ የተለመደ ነው::

ከዚህ ሌላ ስርቆት ከሰይጣን ጾር ሊመጣ ይችላል:: ከላይ የተጠቀሱት ክፍተቶች ሲኖሩ ሰይጣን በደካማ ጎን ገብቶ ኃጢአትን ሊያሠራ /ሊያሰርቅ/ ይችላል:: ለዚህ ነው አንዳንድ ሰዎች ሳይቸግራቸው የሚሰርቁት:: ምክንያቱም ስርቆት ሱስ እስከ መሆን የሚደርስ ከሰይጣን የሚመጣ ጾር ነውና:: እንግዲህ ከሰርቆት ኃጢአት ለመጠበቅ ዘወትር ከቃለ እግዚአብሔር ሳይርቁ በጸሎት እየተጉ "ኑሮዬ ይበቃኛል" ማለት ያስፈልጋል:: ብዙዎች ኑሮዬ ይበቃኛል ማለት ተስኗቸው በምኞት ለሰይጣን መግቢያ ቀዳዳ ከፍተውለት ሰርቀው እግዚአብሔርን አሳዝነዋልና:: ስለዚህ ክርስያን በእምነት "ኑሮዬ ይበቃኛል" ሊለምድ ያስፈልጋል:: እምነቱ ካለ ከመስረቅ ይልቅ አምስቱን አንጀራና ሁለቱን ዓሣ ባርኮ ሴቶችና ሕፃናት ሳይቆጠሩ አምስት ሺ ወንዶች መግቦ አሥራ ሁለት መሶብ ያትረፈረፈ አምላክ የእኔንም ሕይወት በበረከት ይሞላዋል ማለት ይቻላል:: ማቴ 14:13-21 ያን ጊዜ ነው አሥራት ማውጣትና የራስ ያልሆነውንም አለመፈለግ የሚቻለው:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም "ኑሮዬ ይበቃኛል" የሚለው ግን እግዚአብሔርን መምሰል እጅግ ማትረፊያ ነው ወደ ዓለም ምንም እንኳ አላመጣንምና አንዳችም ልንወስድ አይቻለንም ምግብና ልብስ ከኖረን ግን እርሱ ይበቃናል:: ዳሩ ግን ባለጠጎች ሊሆኑ የሚፈልጉ በጥፋትና በመፍረስ ሰዎች በሚያሰጥምና በሚያሰንፍ በሚጎዳም በብዙ ምኞትና በፈተና ወጥመድም ይወድቃሉ:: ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና አንዳንዶችም ይህን ሲመኙ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ ብሏል:: 1ጢሞ 6:6-10:: ስለሆነም ከሥርቆት ኃጢአት ለመጠበቅ በሁሉ እያመሰገንን "ኑሮዬ ይበቃኛል" ልንል ይገባናል:: ፊልጵ4:11:1 በጽድቅ የሚገኝ ጥቂት ነገር በዓመጽ ከሚገኝ ብዙ ትርፍ ይሻላልና ምሳ 16:8::

እንግዲህ በተለያዩ ምክንያቶች በማወቅም ይሁን ባለማወቅ በስርቆት ላይ የተሰማራን ሰዎች መፍትሔው ንስሐ መሆኑን አውቀን አሁኑኑ ንስሐ መግባት አለብን:: ማቴ 6:34:: የበደልነውን ክሰን የቀማነውን መልሰን ዛሬውኑ ከሰውም ከእግዚአብሔርም ጋር መታረቅ ይገባናል:: ዘሌ 6:4 ዘጸ 22:7-8 ምሳ 6:30-31 ሉቃ 19-8 ::

# ስምንተኛው ትእዛዝ

## «በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር»

ዘጸ.20÷16::

በሐሰት መመስከር መዋሸት ነው:: በቅዱስ መጽሐፍም ስለሐሰት የተነገሩት ቃላት የመዋሸትን አስከፊ ገጽታ የሚያሳዩ ናቸው:: ስለዚህም ነገር ጠቢቡ ሰሎሞን «ውሸተኛ ከንፈር በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ ነው» በማለት ተናግሯል:: ምሳ.12÷22:: መዋሸት በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ በመሆኑም ቀደም ብሎ በዘሌዋውያን «እናንተም እርስ በርሳችሁ ሐሰት አትነጋገሩ»የሚል ትእዛዝ ተሰጥቶ ነበር:: ዘሌ.19÷11:: ይህም በሰዎች ዘንድ ሐሰት መናገር ያለተፈቀደ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው:: ከዚህ በመነሣት ሐሰት ወይም ውሸት ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠቱ አስፈላጊ ነው:: ሐሰት /ውሸት/ የሆነውን አልሆነም፣ ያለሆነውን ሆነ ብሎ ለሌላው ሰው መናገር ወይም አሉታዊውን አዎንታዊ አዎንታዊውን ደግሞ አሉታዊ አድርጎ በማቅረብ የተሳሳተ መረጃ መስጠት ማለት ነው:: ሐሰት የእውነት ተቃራኒ ነው::

በዚህ ላይ በመመሥረት ነው መምህረ አሕዛብ የተባለው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ምእመናን በላከው መልእክቱ «ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ÷...እያንዳንዳችሁ ከባልንጀሮቻችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ::» በማለት የመከረው:: ኤፌ.4÷25:: በዚህ ምንባብም ቢሆን እውነትን መናገር የክርስትና መሠረት መሆኑ በግልጥ ነው የተመለከተው:: ብሉያትም ሆኑ ሐዲሳት ተባብረው ሐሰትን አውግዘውታል፤ ክፉ ነውና::

መዋሸት በሰውም በእግዚአብሔርም ዘንድ መጠላቱ ኃጢአት ስለሆነ ነው:: ውሸት ከፍርሃትና ከደካማ ባሕርይ የሚመነጭ ሊሆን ይችላል:: በራሱ የሚተማመንና እውነተኛ ሰው አይዋሽም፣ የተሰጠውንም ኃላፊነት በሚገባ ይወጣል:: በራሱ የማይተማመን ደካማና ሰነፍ ሰው መዋሸትን የስንፍናው መሸፈኛና ቀላል የመፍትሔ አማራጭ አድርጎ ይጠቀምበታል:: አልፎ አልፎም ውሸትን ለቀደመ ሐሰት መሸፈኛ ሲጠቀሙበት የሚታዩም አሉ:: እንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች ከአንዱ ውሸት ወደሌላው እየቀጠሉ ሲዋሹ ይኖራሉ፣ መዋሸታቸውን ለመሸፈን መዋሸትን ለምደዋልና::

የሐሰተኛ ሰው ቃሉ አይታመንም÷ የሚያምነውም የለም፤ እውነትን እንኳ ቢናገር፣ እውነተኛነቱንም ለማረጋገጥ ቢምል፣ ከቀደመው ውሸቱ የተነሣ ነገሩን አምኖ የሚቀበለው አያገኝም፤ አንድ ጊዜ ተአማኒነቱን አጥቷልና:: መዋሸት በጀርባ ሌላ ኃጢአትን የከለለ፣ ያለፈውን መሸፈኛ ወይም የሚመጣውን መከለያ እጥፍ ኃጢአት ነው:: ስለሆነም እንደ

ዋሽ ያመነውን ተነሳሒ የሚያናዝዘው ካህን ለመዋሸት የገፋፋው ምን እንደሆነ ይነግረው ዘንድ ሊጠይቀው ይገባል፤ ከውሸት በስተጀርባ ሌላ ኃጢአት ሳይኖር አይቀርምና።

ሐሰትን ወደዓለም ያስገባው የመጀሪያው ውሸተኛ ጠላታችን ዲያብሎስ ነው። እርሱ በሥጋ ከይሲ በእባብ ተሰውሮ የመጀመሪያ ወላጆቻችንን አዳምንና ሔዋንን «ሞትን አትሞቱም» በማለት በሐሰት በተናገራቸው ጊዜ ዋሸ። ዘፍ.3÷4። ለዚህ ውሸት ያነሣሣውም ክፋቱና እነርሱን ለማጥፋት የነበረው ፍላጎቱ ነው። እግዚአብሔርም ስለዚህ ክፉ ጠላታችን ሲናገር «እርሱ ...ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና።» ማለቱን በወንጌል ተጽፎ እናገኘዋለን። ዮሐ.8÷44። እነዚህ ምንባባት ሐሰተኛ ሰው በግብሩ የዲያብሎስ ልጅ መሆኑን ያስተምሩናል።

ሐሰት ቀጥተኛ ወይም ተዘዋዋሪ ሊሆን ይችላል። የሐሰት መልእክትን የሚያስተላልፍ ሰው ሁሉ በተዘዋዋሪ ስለሚዋሽና የውሸትም ተባባሪ ስለሆነ ሐሰተኛ ነው። አንዳንድ የዋህ ሰዎች መድኃኒታችን «እንደ እባብ ብልህ እንደ ርግብ የዋህ ሁኑ» ያለውን በመዘንጋት የሰሙትን ሁሉ እውነት መሆኑን ሳያረጋግጡ መልሰው በማውራት የሐሰት ተባባሪና ሐሰተኞች ይሆናሉ። የክርስቲያኖች የዋህነት ግን በማስተዋልና በጥበብ ላይ የተመሠረተ መሆን ይገባዋል። ሳያረጋግጡ መናገር ሳያውቁ መመስከር በተለይ ከክርስቲያኖች የሚጠበቅ አይደለም።

ዓለማችን እውነትም ሐሰትም፣ እውነተኛም ሐሰተኛም የመላባት በመሆኑዋ በውስጧ የሚኖር ሰው ሁሉ የሚሰማውን በደፈናው ከማመን አስቀድሞ መመርመርና እውነተኛውን ነገር ማረጋገጥ ግዴታው ሊሆን ይገባል። በብሉይም ሆነ በሐዲስ ኪዳን ነገር ሁሉ በምስክር የተረጋገጠ ሲሆን እንደሚጸና መነገሩ ስለዚህ ነው። ዘዳ.17÷6። ማቴ.18÷16። 2ቆሮ.13÷1። በዚሁ የተነሣም በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ «ነገር ሁሉ በሁለት ወይም በሦስት ምስክር ይጸናል» የሚለው ቃል በተደጋጋሚ ተጽፎ እናገኘዋለን። ስለአንድ ነገር ምስክርነቱን የሰጠ ወይም የሰማውን ለሌላ ሰው የተናገረ ሰው ስለነገሩ እውነቱን ላያውቀው ስለሚችል፣ ስለተናገረው ነገር የተረጋገጠ ዕውቀት ላይኖረው ስለሚችል፣ ነገሩም የተጋነነ ሊሆን ስለሚችል፣ የተሳሳተ ነገር ሰምቶ ሊሆን ስለሚችል፣ ስለሰማው ነገር የማይታመን ወይም አጠራጣሪ መረጃ ሊያገኝ ስለሚችል፣ በግል ምክንያት የሰውን ዝና ለመጉዳት ብሎ ሊያደርገው ስለሚችልና በመሳሰሉት ምክንያቶች እንደ እርግጠኛ ምስክር ሊቆጠር አይገባም።

ባልንጀራ ወይም ጠላት የተናገረውን ነገር ከማጣራትና ከማረጋገጥ በፊት በጥላቻ መመልከትና በክፉ መጠርጠር ተገቢ አይደለም። ስለሆነው ነገር ሁሉ እርምጃ ከመውሰድ አስቀድሞ መመርመርና በቂ መረጃ ማግኘት ያስፈልጋል። ያልተጣራና ያልተረጋገጠን ነገር መናገርና ባልተረጋገጠ ነገር ላይ ተመርኩዞ መወሰን ከሐሰተኛነት አይለይም። የዚህ ዓ

ይነቱ ተግባር በጥንቃቄ ላይ ካልተመሠረተ እውነተኛውንና ጻድቁን ወደመኮነን ሊያደርስ ይችላል፤ በመጽሐፍም «በድፍረትና በትዕቢት በመናቅም በጻድቅ /በእውነተኛው/ ላይ የሚናገሩ የሽንገላ ከንፈሮች ድዳ ይሁኑ።» የተባለው ሳይረጋገጥ ስለሚነገር ነገር አደገኛነት ለማመልከት ነው። መዝ.30÷18። ይህም የተባለበት ምክንያት ብዙዎች የአይሁድ ሊቃነ ካህናት እንደአደረጉት ሁሉ በቅዱሳን ላይ በሐሰት ስለሚመሰክሩ ነው። እነዚህ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የሐሰት ምስክር ይፈልጉ ነበርና።» ማቴ.26 ÷59።

## በቅዱሳን ላይ በሐሰት መመስከር

በመጽሐፍ እንደተመዘገበው ቅዱስ እስጢፋኖስን አይሁድ ሊገድሉት በፈለጉ ጊዜ ብዙ ሰዎች በሐሰት መስክረውበት ነበር። በሐሰት ቃላቸው «ይህ ሰው በዚህ በተቀደሰው ስፍራ በሕግም ላይ የስድብን ነገር ለመናገር አይተውም» በማለት እነርሱን ትክክለኛ፤ እርሱን ደግሞ ተሳዳቢና ሕግን ተላላፊ አድርገው በመናገር መስከረውበት ነበር። የሐዋ.6÷13። ቀደም ብሎም በብሉይ ኪዳን ንግሥቲቱ ኤልዛቤል በኢይዝራኤላዊው በናቡቴ ላይ ያቆመቻቸው የሐሰት ምስክሮች «ናቡቴ እግዚአብሔርንና ንጉሡን ሰድቦአል ብለው በናቡቴ ላይ መሰከሩ። የዚያን ጊዜም ከከተማ አውጥተው እስኪሞት ድረስ ወገሩት»። 1ነገ.20÷13።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «በክብርና በውርደት÷ በክፉ ወሬና በመልካም ወሬ ራሳችንን እናማጥናለን፤ አሳቾች ስንባል እውነተኞች ነን» በማለት የተናገረው በሐዋርያዊ አገልግሎታቸው ላይ በሐሰት ይናፈስ የነበረውን አሉባልታ የሚመለከት ነበር። 2ቆሮ.6÷8። ከዚህም በላይ በቅዱሳን ላይ ስለተነገረው የሐሰት ምስክርነት ሁሉ እንጻፍ ቢባል ጊዜም አይበቃም። ብዙ ቅዱሳን በሐሰት ምስክርነት የተነሣ ያለ በደላቸው መከራን ተቀብለዋል፤ የነፍስ መሥዋዕትነትንም ጭምር ከፍለዋል። ለምሳሌ ያህል ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ በዝሙትና በነፍስ ግድያ፤ ሶርያዊው ቅዱስ አብርሃም፣ ታላቁ መቃርዮስ፣ አባ መሪና በዝሙት የተከሰሱት በሐሰት እንደነበር ቅዱሳት ድርሳናት ያስረዳሉ። እነዚህ ቅዱሳን አበው በሐሰት ከተከሰሱበት ኃጢአት ነፃ መሆናቸው ተረጋግጧል። ስለዚህ እንግዲህ በሐሰት ለሚነገር ክስም ሆነ ወሬ ጆሮን ከመስጠት መቆጠብ ለሰው ሁሉ ጠቃሚ ነው።

«በሐሰት አትመስክር» የሚለው ትእዛዝ ዋሽቶ የሚናገረውንና ሐሰተኛ ወሬን የሚሰማውንም ሰው ሁሉ የሚመለከት ነው። ሐሰት ወሬን የሚሰማና የሚቀበል ሰው ውሸተኛውን የበለጠ እንዲዋሽ ይገፋፋዋልና በኃጢአት ላይ ኃጢአት እንዲሠራ ምክንያት ይሆነዋል። በዚህ መሠረትም በሐሰት ኃጢአት ተናጋሪውና አድማጩ ሁለቱም ተሳታፊዎች ናቸው። በቅዱስ መጽሐፍ የምናገኘው የመጽሐፍ ቃል የሚያስተምረው ሐሰተኛ ወሬን መስማትና ማስተጋባትም ተገቢ አለመሆኑን ነው። ምሳ.29÷12። የቤተ

ክርስቲያን ሕግም ከዚሁ በተመሳሳይ ካህኑ ሐሰተኛ ነገርን እንዳይሰማ ያዝዛል::

## ቃላት ለአድማጭ እስኪደርሱ ድረስ ስለመበረዛቸው

አንዳንድ ሰዎች ስለአንድ ነገር የሰሙትን እንዳለ ከማስተላለፍ ይልቅ የራሳቸውን ሃሳብ ጨምረው፣ በራሳቸው መደምደሚያ አበጅተውለት፣ የራሳቸውንም ፍላጎት እንዲያስተላልፍላቸው ካመቻቹ በኋላ ልክ እንደተናጋሪው ቃላት አስመስለው ለሰሚው ያቀርባሉ:: እነዚህ ሰዎች ሐሰተኞች ናቸው:: የዓባይን ወንዝ እንደ ምሳሌ እንውሰድ፤ መልኩ ቡናማ ቀለም ነው፤ ቡናማ የሆነበት ምክንያት ከመነሻው ጀምሮ በሰበሰበው የተሸረሸረ አፈር የተነሣ ነው:: ከዚያ በፊት በኢትዮጵያ ተራራዎች ላይ በዘነበው ንጹሕ ውኃ የተሞላ ነበር፤ በረዥሙ ጉዞው ግን ከአፈር ጋር ተደባልቆ ቡናማ መልክ ኖረው:: የመጀመሪያ መልኩም ለመለወጥ በቃ:: እንዲሁ ሁሉ ከመነሻቸው ንጹሐን የነበሩት ወሬዎች በመጨረሻ በሚሰማቸው ሰው ጆሮ ሲደርሱ ከብዙ ሃሳብ ጋር ተደባልቀውና ማንነታቸው ተለውጦ ነው:: ሐሰት የተጠደባለቀባቸውና የተበረዙ ሆነው ለጆሮ ይቀርባሉ:: ከንጹሕ ንግግር ጋር የተቀላቀለ ሐሰት በሰዎች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያሻክር ይሆናል:: በዚህ የተነሣም የተናፈሱትን የሐሰት ወሬዎች መሠረት በማድረግ ባልንጀራን ወይም ወዳጅን ወይም ማንኛውንም ሰው ቢሆን ከመቀየምና ስለጉዳዩም ከመናገር አስቀድሞ ስለሆነው ነገር ሁሉ እርግጠኛ መሆን ይገባል::

አንዳንድ ሰዎች በሐሰተኛ ወሬ የተነሣ ስማቸው ሲጎድፍና ሲታሙ እየሰሙ ራሳቸውን ከመከላከል ተቆጥበው ይኖራሉ:: እነዚህ ንጹሐን ቀጥብነትን በመምረጣቸው እንደ ጥፋተኛ መቆጠር የለባቸውም:: የአንድን ሰው ንጽሕና ለማረጋገጥ የሚደረገው ጥረት ስለሰውየው ሊታወቅ የማይገባውን የግል ምሥጢሩን የሚያጋልጥ፣ የሌላውን ሰው ወንጀለኛነት የሚያጋልጥ፣ ወይም የሰውየውን ስሕተቶች የሚያጋልጥ ሊሆን ስለሚችል ራሱን ለመከላከል ላይመርጥ ይችላል:: የአንድን ሰው ንጽሕና ማረጋገጥ በከሳሾቹና በስም አጥፊዎቹ ላይ ችግር የሚያስከትል ሲሆን ንጹሑ ሰው ነገሩን ሁሉ ለእግዚአብሔር በመስጠት መከላከሉን ሊተው ይችላል::

ይሁን እንጂ ሐሰተኛው ሰው ንጹሑን ጥፋተኛ፣ ጥፋተኛውን ደግሞ ንጹሕ አድርጎ የሰዎችን ኅሊናና አመ ለካከት ሊበርዝ ይችላል:: ይህን በተመለከተ በቅዱስ መጽሐፍ «ኃጥኡን የሚያጸድቅና በጻድቁ የሚፈርድ÷ ሁለቱ በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊዎች ናቸው::» የሚል ተጽፎ እናገኛለን:: ምሳ. 17÷15:: ንጹሑን ሰው የሚኮንን ኃጢአተኛውንም ጻድቅ እንደሆነ የሚመሰክር ሰው ሐሰተኛ ነው:: በሌላም በኩል በአንድ የሥራ መስክ በቂ ችሎታና ዕውቀት ሳይኖረው እንደ

አንድ ዐዋቂና ብቁ ባለሙያ ሆኖ ሥራ እንዲያገኝ ማድረግም ራሱ ሐሰት ነው፤ ይህን ያደረገውም ሐሰተኛ ነው። ይህ ውሸት /ሐሰት/ ችግረኛውን ወይም ድሀውን ለመርዳት ተብሎ የተደረገ ቢሆንም የዋሸውን ሰው በኃጢአቱ ከመጠየቅ ሊያድነው አይችልም።

## ውዳሴ ከንቱ

ከመጠን ያለፈ ምስጋናና የተጋነነ አድናቆት እውነተኛ መሠረት የሌለውና ሐሰት በመሆኑ ተወዳሹን ሰው ስለራሱ የተሳሳተ እምነት እንዲኖረው በማድረግ ይጎዳዋል። ብዙ ሰዎች ይህን ቀላል ዘዴ በመጠቀም ከሌሎች የሚፈልጉትን ያገኛሉ፤ ከሚሹት ሥፍራም ይደርሳሉ። ይህንን ኃጢአት አስጠያፊ የሚያደርገው ነገር አወዳሹ የሚያደንቀውን ሰው ሲያገኘው ማወደሱና በሌለበት ሥፍራ ደግሞ የሚተቸው በመሆኑ ነው። ስለዚህም ሰውን ባልዋለበት እንደዋለ፣ ያልሠራውን እንደሠራ፣ ያልሆነውን እንደሆነ አድርጎ ምስጋናና ውዳሴ እየሰጡ ማሞካሸት እውነተኛ መሠረት የሌለውና ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት የሚደረግ ስለሆነ ከሐሰት ተነጥሎ አይታይም።

ከዚህ ሌላ ደግሞ ስለ አንድ ሰው ጠንካራ ጎን ሲነገሩ የሚገባቸውን በመተው ድካሙን ብቻ አጉልቶ በማሳየት ሌሎች ስለእርሱ ያላቸውን አመለካከት ለመለወጥ መሞከር ግማሽ እውነት በመሆኑ እንደሐሰት የሚቆጠርና በኃጢአትነቱም የሚያስጠይቅ ነው። ሐሰት የተሰኘበት ምክንያትም ስለ ሰውየው የተሳሳተ መረጃ መስጠት ስለሆነ ነው።

ሐሰተኛ ሰው በሕብረተሰቡ መካከል ያለው ሥፍራ የተናገረው ነገር ተአማኒ እንዳይሆን ያደርገዋል። እንዲህ ያለው ሰው የሚናገረው ሐሰት አስጠያፊ ነው። ስለሆነም ሐሰትን የሚናገረው ሰው ደረጃው ከፍ ያለ መሆኑ የተናገረውን ሐሰት የበለጠ አስጠያፊ ያደርገዋል። በዚህ አንፃር ሐሰተኛውን ወሬ የተናገረው ሰው ሥልጣንና ደረጃ ሐሰትን አስጠያፊ ያደርገዋል። ለማንኛውም ተራ ሰው የተነገረና ለባለሥልጣን ወይም ለመንፈሳዊ አባት የተነገረ ሐሰት የሚመዘንበት ሚዛን እኩል አይደለም። ለምሳሌ ያህልም የዮሴፍ ወንድሞች ለአባታቸው እንደዋሹት፣ አንድ ሰውም ለንስሐ አባቱ እንደሚዋሽ፣ ሐናንያና ሰጲራ መንፈስ ቅዱስን እንደ ዋሹና እግዚአብሔር እንደቀጣቸው። የሐዋ.5÷3–4።

በሕዝቡ መካከል ከያዙት መንፈሳዊ ሥልጣንና ሥፍራ የተነሣ ሕዝቡን የሚያስቱትን ሐሰተኞች ነቢያት፣ ሐሰተኞች ክርስቶሶች፣ እግዚአብሔር ያልነገራቸውን ነገርን የሚሉ ሐሰተኞች መምህራንንና የመሳሰሉትን ሁሉ እግዚአብሔር «እኔም ሳልናገር፦ እግዚአብሔር እንዲህ ብሏል ስትሉ÷ ከንቱ ራእይን ያያችሁ፣ ውሸተኛንም ምዋርት የተናገራችሁ አይደላችሁምን? በማለት ስለጥፋታቸው ነቅፎአቸዋል። ሕዝ.13÷7። ስለሐሰተኞች ነቢያት ደግሞ «በስሜ ሐሰትን የሚናገሩትን የነቢያትን ነገር ሰምቻለሁ።» በማለት ቅሬታውን ገልጧል። ኤር.23÷25። ሕዝቡ

ለመንፈሳውያን መምህራን፣ በእነርሱ ለሚደረጉት ተአምራትና ድንቆችም የሚሰጠውን እውነታዊ ግምት ተገን አድርገው የተሳሳተ ትምህርት የሚያስተምሩት ሐሰተኞች ሐዋርያት እንዲሁም ለማሳሳት የሚጠቀሙባቸው «ሐሰተኛ ድንቆች» የእነርሱን ሐሰተኛነት አስከፊና ተጠያቂነታቸውንም ከፍተኛ ያደርጉታል:: ራእ.2÷2:: 2ተሰ.2÷9::

## የመዋሸት ምክንያትና መፍትሔው

አንዳንድ ሰዎች መዋሸት ከፈጸሙት ጥፋት የሚያድናቸው እየመሰላቸው የሠሩትን ኃጢአት ለመደበቅ ይዋሻሉ:: ይሁን እንጂ የሐሰት መንገድ አጭርና የትም የማያደርስ ብዙ ጊዜም መገለጡ የማይቀር በመሆኑ ሰዎች ከሐሰት ይልቅ የሚያድናቸውን እውነተኛና ተገቢ መንገድ መጠቀም ይኖርባቸዋል:: በተገለጠ ጊዜ የሚያሳፍርና ማኅበራዊ ክበሬታውና መንፈሳዊ ተአማኒነትን የሚያሳጣ ሐሰትን በመጠቀም ምንም ነገር መሥራት ተገቢ ካለመሆኑም በላይ ጉዳቱ ያመዝናል:: ለሁሉም የሚበጀው ደግሞ ልቡናን ከክፋት አእምሮን ከሐሰት ነፃ በማድረግ ማንኛውንም ኃጢአት ለማስወገድ የሚቻል መሆኑን ማመን ነው::

አንዳንድ ሰዎች ከመበሳጨት ወይም ከመፍራት ወይም ስለአንድ ነገር የሚጠይቃቸው ሰው ከሚያሳድርባቸው ጫና የተነሣ ሊዋሹ ይችላሉ:: ከመዋሸት ይልቅ ግን በእንደዚህ ያለ ጊዜ ዝምታ መልካም መሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው:: በሐሰት ራስን ለማዳን ከመሞከር ምንም ይሁን ምን የንግግርን አቅጣጫ በመቀየርም ቢሆን፣ መልስ ላለመስጠት ይቅርታ በመጠየቅም ቢሆን፣ በተቻለ መጠን በማስተዋልና እውነትን በመናገር ራስን መከላከልና ስለተሠራው ስሕተት ይቅርታ መጠየቅ መልካም ነው::

አንዳንድ ሰዎች ሳያውቁ እንደሚያውቁ፣ ሳይሆኑም እንደሆኑ በማስመሰል የሚኩራሩ በመሆኑና አለማወቃቸውንም እንዳይታወቅባቸው ስለሚዋሹ መዋሸትን እንደመሸፈኛ ሊጠቀሙበት ይችላሉ:: አንዱን ኃጢአት ለመሸፈን በመዋሸት ተጨማሪ ኃጢአት ከመሥራት አላውቅም በማለት እውነት መናገሩ የተመረጠና ተገቢም ነው::

ለማጠቃለልም ሐሰት በአንደበት በመናገር የሚፈጸም ኃጢአት ነው:: በሰው ዘንድ በምሥጢር መጠበቅ ያለባቸው ብዙ ጉዳዮች ስላሉ በዚህ ረገድ የማይናገረው ሰው ሐሰተኛ ሊባል አይችልም:: እንዲህም ስለሆነ ባለመናገር የሐሰትን ኃጢአት መዋጋትና መከላከል ይኖርብናል::

# ዘጠነኛው ትእዛዝ
# አትመኝ

"የባልንጀራህን ቤት አትመኝ የባልንጀራህን ሚስት ሎሌውንም ገረዱንም በሬውንም አህያውንም ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማንኛ ውንም አትመኝ"

ዘጸ 20:17

## ምኞት ምንድን ነው?

ምኞት የሰው ልጆች በዓይናቸው ያዩትን በእጃቸው የዳሰሱትን በጆሮአቸው የሰሙትን ልባቸው የወደደውንና የፈቀደውን ለማግኘት በኅሊናቸው ሰሌዳ ላይ የሚቀረጽ መሻት /ፍላጎት/ ነው:: ይህ ፍላጎት መንፈሳዊ ሥጋዊና ሰይጣናዊ ተብሎ ይከፈላል::

መንፈሳዊ:- ቀደምት ቅዱሳት አበው የተጋደሉትን መንፈሳዊ ተጋድሎ ከገድላቸው ተረድቶ የእነርሱን አሠረ ፍኖት ለመከተልና እነርሱ ያገኙትን ጸጋ ለማግኘት /እንደእርሱ ለመሃን/ በልብ ጽላት ላይ ተቀርጾ መከራውን ፈተናውን ሁሉ በትዕግሥት እንዲቀበሉ የሚገፋፉ ኃይሉ መንፈሳዊ ምኞት ይባላል:: የእግዚአብሔርን መንግሥት ካልተመኙ ለመንፈሳዊ ተጋድሎ መብቃት አይቻልምና::

ሥጋዊ የዓይን አምሮት የሥጋ ፍላጎትን ተከትሎ የሚመጣ ሲሆን ጉዳትም ጥቅምም አለው ለምሳሌ ሌሎች የደረሱበት ጥሩ ደረጃ ላይ ለመድረስ ዶክተር የሆኑትን አይቶ ዶክተር ለመሆኑ አስቀድሞ ወስጣዊ መሻት በልቦና መቀረጽ አለበት:: ይህም ተማሪውን ተግቶ እንዲጠና ሠራተኛውን ጠንክሮ እንዲሠራ ይገፋፋዋል:: ስለዚህ ለሥጋዊ ሕይወቱ ይህ ዓይነት ምኞት ያስፈልገዋልና በክርስትና ትምህርት አይወገዝም::

በአንጻሩ ግን ሌላው የደከመበትንና ላቡን ያንጠፈጠፈበትን ሀብት እጅና እግርን አጣምሮ የእኔ ባደረገው እያሉ መመኘት ሲብስም ያልደከሙበትን ሀብት ለራስ ለማድረግ ሰይጣናዊ መንገድ መጠቀም ከእግዚአብሔር አንድነት የሚለይ ነው::

ሰይጣናዊ የበጎ ነገር ሁሉ ተጻራሪ ርኩስ መንፈስ በረቂት መንገድ በኅሊናችን የሚያሳድረው መጥፎ ምኞት ሰይጣናዊ ምኞት ይባላል:: ሰይጣን አምላክ መሆንን እንደተመኘና ከክብሩ እንደተዋረደ ሁሉ አዳምና ሔዋንም አምላክነትን ሽተው እንዲዋረዱ ጸጋቸውን እንዲገፈፍ አድርጓል:: ዛሬም ሰው ያልተሰጠውን ክብር እንዲሻና ያንን ለማግኘትም እግዚአብሐርን በሚያሳዝን መልኩ እንዲሠማራ ያደርገዋል:: ይህንንም የሚያደርገው የምናየወና የምንሰማውን መነሻ በማድረግ ነው::

ምንም እንኳን ከላይ እንዳስቀመጥነው ምኞት መንፈሳዊ ሥጋዊና ሰይጣናዊ ተብሎ ቢከፈልም የዚህ ጽሑፍ ትኩረት ሰውን ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ውጭ በሚያደርገው የምኞት ዓይነት ነው:: ስለዚህ ከዚህ በኋላ ምኞት ስንል በሰዎች ዘንድ እንደ ኃጢአት የሚቆጠረውን ምኞት ማለታችን ነው::

"አትመኝ" የሚለው ይህ ዘጠነኛ ትእዛዝ በጥልቀት ሲተረጎ ምና ሲጤን ኃጢአቶችን ሁሉ የሚመለከት ሆኖ መገኘቱ የዚህን ትእዛዝ የበለጠ ጠቃሚ መሆን ለመረዳት ያስችላል:: በቀድሞ ጊዜ ከሰዎች ልቡና መደንደንና ከክፋታቸውም የተነሣ ይህ ትእዛዝ የታወቀና ትኩረትም የተሰጠው አልነበረም:: ትኩረት በተሰጠው ጊዜ ግን ጠቃሚነቱ ይታወቃል:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም "ሕግን ልሽር አልመጣሁም ልፈጽም ነው እንጂ" በማለት የተናገረው ቀድሞ ፍጹም ያልነበረውን የሰው ልጅ አእምሮ ወይም ዕውቀት ፍጹም ላደርገው መጥቻለሁ ማለቱ እንደነበር ማወቅ ተገቢ ነው:: ማቴ 5:17

በቅዱስ ወንጌልም "ወደሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርሷ ጋር አመነዘረ" የሚለው የጌታ ትምህርት በውስጡ የብሉይ ኪዳንን ሕግ የያዘ የብሉይ ኪዳንም ትርጉም ነው:: ማቴ 5:28:: እግዚአብሔር አስቀድሞ በኦሪት "የባልንጀራህን ሚስትም አትመኝ" ብሎ ሕግ ሠርቶ ነበርና:: ዘዳ 5:21:: እግዚአብሔር አምላካችን አትመኝ የሚለወን ትእዛዝ የሰጠው የኃጢአት ሁሉ መነሻ ምኞት ስለሆነ ነው:: ለምሳሌ ማመንዘር የሚጀመረው በሥጋዊ ምኞት ሌብነትም ሀብታም ለመሆን ከመመኘት ነው ሐሰትም አውነተኛ ለመምሰል ወይም አንዳችን ነገር ያለአግባብ ለማግኘት ከመመኘት የተነሣ የሚፈጸም መግደልም ከበቀል ምኞት ወይም ወደዚያ ከሚመራ ስሜት የሚመጣ ነው:: ሰው እንግዲህ ምኞትን ከተዋጋውና ድል ካደረገው ኃጢአትን ሁሉ በመቋቋም ድል ለማድረግ ይቻለዋል::

ሰው ከምኞት ጋር በተፋጠጠ ጊዜ ከምኞት ከመታገል ይልቅ የሚበጀው ከመመኘት መሸሽ ነው:: ምክንያቱም ምኞትን ከማሸነፋ አስቀድሞ ሊሸነፍና ልቡናውም በምኞት ጦር ተወግቶ በምኞት መርዝ የተነደፈ ሊሆን ይችላልና ነው:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ለጢሞቴዎስ "ከክፉ የጎልማሳነት ምኞት ግን ሽሽ" ሲል የመከረው ለዚህ ነው:: 2ኛ ጢሞ 2:22 ምኞት ከተመኙት እስኪፈጸም ድረስ ያለማቋረጥ የሚዋጋ ያር በመሆኑ መሸሽ አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው:: ምኞት በሰው ልቡና ውስጥ ሥፍራ በተሰጠው መጠን የሰውን ፈቃደኝነት ያገኛል ስለእርሱ በታሰበ መጠንም በልቡና ውስጥ ያድጋል ከዚያም ስለ እርሱ በማሰብ ወደ መደሰት ለመፈጸም ወደ ማስገምጀት ቀጥሎም በተግባር ወደ መፈጸም ያደርሳል:: ስለዚህ በመመኘትና የተመኙትን ፈጽሞ ከመውደቅ መጀመሪያውኑ ከመመኘት መሸሽ እጅግ ጠቃሚ ነው:: የሰው ባሕርይ ደካማ ነውና ከሥጋው የተነሣ ስለሚመኘው ኃጢአት ከማሰብ ጀምሮ በእርሱ ወደ መመራት ወደ መፈጸም ወደ መደጋገም በእርሱም ወደ መለከፍ ከዚያም አልፎ ለሚመኘው ነገር ወደ መገዛት ይደርሳልና ጠንቀኛ ከሆነው ምኞት አብዝቶ ራስን መቆጠብ አስፈላጊ ነው:: ምኞት የሚያስከትለው አደጋ አብዝቶ ራስን መቆጠብ አስላፈጊ ነው:: ምኞት የሚያስከትለው አደጋ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ብቻ የሚያበቃ አይደለም:: ሰወ ምኞቱን ለመፈጸም ሲል በሌላ ኃጢአት ሊወድቅም ይችላል:: ለምኞቱ መፈጸም ብሎ ሊዋሽ

ሊያታልል ሊሰርቅ ሊገድልና ሌላ ኃጢአትም ሊሠራ ይችላል:: ከዚህ ሁሉ ምኞትን ከሥሩ ነቅሎ ከልቡና ማውጣት ተገቢ ነው:: ስለዚህ መነሻውም መድረሻውም አደገኛ ከሆነ ከዚህ የመመኘት ኃጢአት መሸሽና ማምለጥ አስፈላጊ ነው::

## ለምኞት የሚዳርጉ ምክንያቶች

ሀ. *ያለኝ ይበቃኛል አለማለት:-* ሰው ውስጣዊ ፍላጎቱን ያለኝ ይበቃኛል በሚለው መንፈሳዊ መርሕ ካልለጎመው በስተቀር የሰው ፍላጎት የሚያየውን ሁሉ እንዲመኝ ያደርገዋል:: ስለዚህ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ያለኝ ይበቃኛል ማለትን ተምሬያለሁ በማለት ክርስቲያኖች ያለን ይበቃኛል በሚለው የወንጌል ትምህርት እንዲመሩ አስገንዝቧል::

ለ. ስንፍና:- ሰው ሆይ ለፍተህ ጥረህ ግረህ በላብህ ወዝ ብላ ለሚለው አምላካዊ ትእዛዝ ጀርባቸውን የሰጡ ሰነፎች ሌላው ወጥቶ ወርዶ ያፈራውን ንብረት እያዩ ምነው ይህን ለእኔ ባደረገው እንዲህ ዓይነት ቤት ቢኖረኝ አቤት የእገሌን ሀብት ለእኔ ቢያደርገው እያሉ የሌላውን ንብረት የእነርሱ እንዲያደርገው ሌት ተቀን ሲያልሙ ይኖራሉ:: የስንፍና ገመድ እጅና እግራቸውን ያሠራቸውን ሰዎች ለምኞት የተጋለጡ ብሉም በምኞት ፈረስ ተጭነው ወደ ኃጢአት ገደል የሚገቡ ናቸው::

ሐ. ራስን ከሌሎች ጋር ማነጻጸር:- ሰው እንደ ቤቱ እንጂ እንደ ጎረቤቱ አይኖርም ይባላል:: አንድ ሰው ሕይወቱን ሊመራ የሚገባው ከራሱ አቅም አንጻር መሆን ይኖርበታል:: ዳሩ ግን የእርሱን ሕይወት ከሌሎች ጋር ማወዳደር ከጀመረ በምኞት ባሕር ውስጥ ጠልቆ መዳከር ይመጣል::

መ. የሰይጣን ፆር:- ሰይጣን በእባብ ሥጋ ተሰውሮ በሔዋን ኅሊና ውስጥ ምኞትን እንደመረጸ ሁሉ ዛሬም በሰው የስሜት ሕዋሳት ተጠቅሞ የምኞት ጾር ሊቀሰቅስ ይችላል::

### ሃ. *ምኞት በእርካታ የሚገታ አይደለም*

የሰው ልጅ ምኞት በደከመውና ተገኘ ባደረገው ጊዜ ዳግመኛ እየኀኀሁ ከመቸገር ይህን ምኞትን ፈጽሜው ባርፍ ይሻለኛል በማለት ራሱን ያታልል ይሆናል:: ምኞት ግን በአንድ ጊዜ እርካታ ከልቡና የሚነቀል ከኅሊናም የሚጠፋ አይደለም:: የተጠማ ሁሉ አንድ ጊዜ ጠጥቶ ዳግመኛ እንደሚጠማ ምኞቱም በመፈጸም ደስታን የሚያገኝ የሚመስለውና ፈጽሞ እንደ ሚረካ በማሰብ የተመኘውን የፈጸመ ሰው እንደገና ደግሞ ይመኛል ምኞቱም ማብቂያ የለውም:: ምኞትን መፈጸም ሰውን ከመመኘት አያድነውም የበለጠ የምኞትን ፆር ይጨምርበታል እንጂ:: በዓለማችን እንደምናየው ገንዘብ ለማግኘት ተመኝቶ ገንዘብን ያገኘ ሰው ተጨማሪ ገንዘብ ለመሰብሰብ ይመኛል እንጂ የሰበሰብኩት ይበቃኛል አይልም::

አባታችን አዳም በገነት ያሉትን ዛፎች ሁሉ ከአንዲቱ በቀር እንዲያዝዝባቸው ሥልጣን ተሰጥቶት ነበር:: በዚህ ባለመርካቱም ያቺን አንዲቱን ደግሞ ተመኛት ከፍሬዋ ለመብላትም ጓጓ:: ሁሉ ያለው ንጉሡ አክዓብ የኢይዝራኤላዊውን የናቡቴን ትንሽ መሬት ተመኘ:: ሰባት ሚስቶች የነበረው ዳዊት የወታደሩን /የባለሚሉን/ የኦርዮን ሚስት ተመኘ:: ንጉሥ ሰሎሞንም ምኞቱን ለማርካት እስከ መጨረሻው ተጓዘ "ዓይኖቼንም ከፈለጉት ሁሉ አልከለከልኳቸውም በማለት መጨረሻ የሌለው ምኞቱን ገልጧል:: መክ 2:10:: በዚህ ወጤትም በመቶዎች የሚቆሩ ሚስቶች ለእርሱ አደረገ በማይሞተው ቃሉም "ዓይን ከማየት አይጠግብም ጆሮም ከመስማት አይሞላም:: ፈሳሾች ሁሉ ወደ ባሕር ይሄዳሉ:: ባሕሩ ግን አይሞላም" በማለት ሊረካ የማይችል የምኞቱን ነገር ተናግሯል:: መክ1:7ሀ8:: በዚህም ምኞት ፈጽሞ እርካታ ማግኘት ጊዜያዊ ብቻ እንጂ ዳግመኛ ከመመኘት የሚገላግል መፍትሔ አለመሆኑን አስተምሮናል:: ለዚህ መፍትሔ የሚመኝ ሥጋን ራስን በመግዛት ልጓም መቆጣጠር ነው የሚሻለው ግን ፈጽሞ ከምኞት መሸሽ ነው:: ያገባው ብዙም ሚስቶች የነበሩት ዳዊት እርካታን በፈለገና ራሱን መግዛት ባልተቻለው መጠን በምኞት ድል እንደተመታ ያላገባው ዮሴፍ በንጽሕና ሆኖ ራሱን በመግዛቱና ምኞትን ያሸነፋት የሸሹት ሰው እንጂ የተጋፈጡት አይደሉምና በጥበብ ሆኖ ከክፉ የሥጋ ምኞት መሸሽ መድኃኒት መሆኑን አውቀን ገንዘብ ልናደርገው ይገባናል::

### *የምኞት ዓይነቶች:-*

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም "ሥጋ በመንፈስ ላይ ይመኛል" በማለት ምኞት ከሥጋ ፈቃድ የሚመነጭ መሆኑን ተናግሯል:: ገላ 5:17:: ስለዚህ ምኞትን የሚያስከትል የሥጋ ፈቃድ ተዘርዝሮ የሚያበቃ አይደለም:: በዚህ የሥጋ ፈቃድ ላይ ተመሥርቶ በሰው ልቡና ስለሚያመላለሰው ምኞት ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ሲናገር "በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞት የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት "በማለት የተወሰኑትን ዘርዝሯል:: 1ኛ ዮሐ2:16:: በዚህ መሠረትም የዓይን አምሮት የሥጋ ፍላጎት የገንዘብ መሻት ሁሉ የምኞት ዓይነቶች ናቸው:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ "የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱ ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ" በማለት በክርስቲያኖች ዘንድ ምኞት በምን ዓይነት ሁኔታ እንደተረታ ገልጧል:: ገላ 5:24:: ሥጋን ከመሻቱና ከክፉ ምኞቱ ጋር በመስቀለ የማገኘው ደስታ መንፈሳዊ እርካታን የሚሰጥ ከፍተኛ ድል ነው::

የሥጋ ምኞትም ለዝሙት ለመብላት ለዓይን አምሮት ለመስማት ወይም ለመሻት የሚደረገውን ጉጉት ሁሉ ያጠቃልላል:: እግዚአብሔር የባልንጀራህን ሚስት አትመኝ ማለቱ አታመንዝር ሲል ነው:: ኤሳው ብኩርናወን ለምሥር ወጥ

እንዲሸጥ ያደረገው የመብል ምኞት ነው:: ዘፍ 25:29-34:: የእሥራኤላውያንም መጎምጀትና" የምንበላውን ሥጋ ማን ይሰጠናል በግብጽ ያለዋጋ እንበላው የነበረውን ዓሣ ዱባውንም በጢኹንም ኩራቱንም ሽንኩርቱንም እናስባለን " በማለት ማልቀስ ከዚህ የመመገብ ምኞት ጋር ተመሳሳይነት አለው:: ዘኁ11:4-5:1 እሥራኤል የተመኙትን ሥጋ እግዚአብሔር ሰጣቸው ነገር ግን በከባድ መቅሰፍት ደግሞ መታቸው ይህም ለክፋ ምኞታቸው መቀጣጫ ነው:: ያም ሥፍራ የምኞት መቃብር ተብሎ ተጠራ የጎመጁ ሕዝብ በዚያ ተቀብረዋልና ዘኁ 11:34::

ገንዘብ ምኞትም ንብረትን ለማደራጀት መመኘትም አለ:: ስለዚህም እግዚአብሔር የባልንጀራህን ቤት አትመኝ በማለት አዝዞአል:: የክብርና የታዋቂነት የሥልጣንና የማዕረግ የታላቅነት የውበትና የጌጠኛነት ወዘተ ምኞቶችም አሉ:: እነዚህ ሁሉ ወደውድቀት የሚያደርሱ የጥፋት መንገዶች ናቸው:: ዲያብሎስም የወደቀው ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ ከደመናዎች ከፍታ በላየ አርጋለሁ በልዑልም እመሰላለሁ በማለት የማይገባውን ለማግኘትና ለመሆን ካደረበት ምኞት የተነሣ ነው:: ኢሳ14:13-14:: እንዲሁም ዲያብሎስ እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ ባላቸው ጊዜ አዳምና ሔዋን ለመውደቅ የበቁት ባደረባቸው ከፍተኛ ምኞት የተነሣ ነበር::

ከሁሉም የበለጠ አደገኛው በሰይጣን ልቡና የነገሠው የሰውን ልጅ የማጥት ምኞት ነው:: ከመጀመሪያው አንሥቶ ዓላማው ሰውን በየምክንያቱ በማሰናከል ከእግዚአብሔር ለማጣላትና በነፍሱም እንዲሞት ለማድረግ ነበርና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ስለእርሱ እርሱ ከመጀመሪያው ነፍሰ ገዳይ ነበረ ብሎአል:: ዮሐ8:44:: የበቀል ስሜትም ከዚህ ምኞት ጋር የሚደመር ነው::

የሰው ልጅ ከዚህ ክዳት ከምኞት ኃጢአት ተለይቶ ለመኖር ውጊያውንም ሊቋቋም የሚችለው ለዚህ ዓለም እንግዳ መሆኑን በመገንዘብና ከንቱ የሆነውን የምኞት ምንጭ መናቅ መተው ሲቻለው ነው:: "ሁሉ ከንቱ ነፍስንም እንደመከተል ነውና እንዲሁም ደግሞ ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉና:: መክ 1:14:1 1ዮሐ 2:17:: የራስን ጥቅምና አርካታን ብቻ በማሰብ ላይ ተመሥርቶ በምኞት እሳት ከመቃጠል ይልቅ ሳያቋርጡ ስለ ሌሎች ሰዎች ማሰብን ሰውን ማፈቀርን እንዲሁም ሌሎችን በቸርነት የመርዳትን መንፈስ ገንዘብ ማድረግ ከምኞት የተነሣ የሚፈጸመውን ኃጢአት ለመቋቋም ያስችላል:: በዚህም ጸንተን ከምኞትም ተጠብቀን ለመኖር እንድንችል ቸሩ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ይርዳን::

# አሥረኛው ትእዛዝ

*«ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ»*

ዘሌ.19÷18

በዚህ መጽሐፍ በመጀመሪያው ክፍል እንደተገለጠው ሁሉ በዘሌዋውያን 19÷18 የተጻፈው «ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ» የሚለው ትእዛዝ በዘጸአት 20÷3-17 ከተዘረዘሩት ጋር ተዳምሮ ከአሠርቱ ትእዛዛት መካከል አንዱ ነው:: ይህን ትእዛዝ ከአሠርቱ ትእዛዛት ነጥለው የሚመለከቱ ቢኖሩም አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለትእዛዛት በተና ገረበት አንቀጽ ሕግ ሁሉ እግዚአብሔርን በፍጹም ልብ፣ በፍጹም ሃሳብ፣ በፍጹም ነፍስም በመውደድ በፍቅረ እግዚአብሔር እና ባልንጀራን እንደራስ አድርጎ በመውደድ /በፍቅረ ቢጽ/ የሚጠቃለል መሆኑን በሚገባ አስተምሯል::

ይህንን የጌታችንን ትምህርት መሠረት በማድረግም ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አሠርቱን ትእዛዛት በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች በመፈረጅ የመጀመሪያውን በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለውን ግንኙነት /ፍቅረ እግዚአብሔርን/ የሚመለከት፣ ሁለተኛውን ደግሞ በሰዎች መካከል ያለውን የእርስ በርስ ግንኙነት /ፍቅረ ቢጽን/ የሚመለከት ነው ብለውታል:: ይህም የሆነበት ምክንያት የትእዛዛት አሥረኛው «ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ» የሚለው በመሆኑ ነው:: ስለሆነም ከዚህ በመቀጠል የዚህን ትእዛዝ አተረጓጐምና ተግባራዊ አፈጻጸም እንመለከታለን::

## ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ

በብሉይ ኪዳን «ባልንጀራ» የሚለው ቃል በጉርብትና የሚኖር እሥራኤላዊን የሚመለከት ፍቺ የተሰጠው ነበር:: «ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ» በማለት የተሰጠው ትእዛዝም በመልክም ግንኙነት ላይ የተመሠረተ ጉርብትናን ብቻ የሚመለከትና በጎረቤታሞች መካከል ንጹሕ ፍቅር እንዲኖር የሚያስችል ዓላማ ያለው ነበር:: በዚሁ መሠረትም እያንዳንዱ ሰው ባለበት ደረጃና የኑሮ ሁኔታ ባልንጀራውን መውደድ እንደሚገባው ቅዱሳት መጻሕፍት ያስተምራሉ:: ለምሳሌ ጠቢቡ ሰሎሞን «ባልንጀራውን የሚንቅ ይበድላል» በማለት የተናገረው ሰውን መናቅ ኃጢአት ከመሆኑም በላይ በእግዚአብሔር ፊት የሚያስጠይቅ መሆኑን የሚያስረዳ ነው:: ምሳ 14÷21::

በቅዱስ ወንጌልም እንደተጻፈው የዘለዓለምን ሕይወት ለመውረስ ምን ማድረግ እንደሚገባ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ለጠየቀው ጎልማሳ የተሰጠው መልስ ትእዛዛትን እንዲፈጽም ነበር:: ትእዛዛቱ እንዲዘረዘሩለት በመጠየቅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «አትግደል፣ አታመንዝር፣ አትስረቅ፣ በሐሰት አትመስክር፣ እናትህንና አባትህን አክብር» በማለት ከዘረዘረለት በኋላ «ባልንጀራህን

እንደራስህ ውደድ» በማለቱ ባልንጀራን መውደድ እም ላካዊ ሕግና በተለይም ደግሞ የዘለዓለምን ሕይወት ለመውረስ መሠረታዊ መስፈርት መሆኑን የሚያመለክት ነው:: ማቴ.19÷19::

በብሉይ ኪዳን ከነበረው አንፃር ባልንጀራ የሚለው ቃል በሐዲስ ኪዳን ሰፋ ያለ ሆኖ እናገኘዋለን:: በዕለተ ዓ ርብ በመስቀል ያፈሰሰው የክርስቶስ ደም ለዓለም ሁሉ ማለትም ለደቂቀ አዳም ድኅነት በመሆኑና ይህ ቤዛነ ትም ሕዝብንና አሕዛብን አንድ ያደረገ ስለሆነ ባልንጀራ የሚለው ቃል ፍቺ በክርስቶስ አንድ አካል የሆኑትን ሁሉ የሚያጠቃልል ወደመሆን ሰፍቷል:: በዚህ ትርጉም መ ሠረትም ባልንጀራን መውደድ ማለት ሰውን ሁሉ መውደድ ሆኖ እናገኘዋለን::

በቅዱስ ወንጌል ታሪኩ የተጻፈለት ደጉ ሣምራዊ በመንገድ ላይ ወድቆ ያገኘውን ቁስለኛ አንሥቶ መልካም ነገር ስለአደረገለት፣ ከወንበዴዎችም እጅ ስለአዳነው፣ ምሕ ረትም ቸርነትም ስለአደረገለት ባልንጀራው እንደተባለ ተገልጧል:: ሉቃ.10÷25-37:: በደዌ ሥጋ ብቻ ሳይሆን በደዌ ነፍስም ተይዘው ለሚቃትቱና ዕርዳታን ለሚሹ ሁሉ ደርሶ ከቃለ እግዚአብሔር ተመግበው፣ በንስሐ ታክመው፣ ጸጋና ረድኤትን ተጎናጽፈው በመንፈሳዊ ሕይወት እንዲ ኖሩ ማድረግ ባልንጀራን መውደድ ነው:: ወንበዴ ዲ ያብሎስ በተለያዩ ሁኔታዎች የሚያንገላታቸውን ደቂቀ አዳም ለመንፈሳዊ የሕይወት ትንሣኤ ማብቃትና ነፍሳ ቸውን በኃጢአት ከመሞት መታደግም ባልንጀራን መውደድ ነው::

በጥቅሉ ስንመለከተው በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረ የሰውን ዘር ሁሉ ማንንም ከማን ሳያበላልጡ እኩል በሆነ ፍቅር መመልከትና ማክበር ባልንጀራን መውደድ መሆኑን ማጤን ያስፈልጋል:: ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብም «ነገር ግን መጽሐፍ፦ ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ እንደሚል የንጉሥን የእግዚአብሔርን ሕግ ብትፈጽሙ መልካም ታደርጋላችሁ፤ ለሰው ፊት ግን ብታደሉ ኃጢአትን ትሠራ ላችሁ÷ ሕግም እንደተላላፊዎች ይወቅሳችኋል::» በማለት የተናገረው ባልንጀራን መውደድ ማለት ሁሉን እኩል አድርጎ በአንድ የፍቅር ዓይን መመልከት እንደሆነ ለማ ስረዳት ነው:: ያዕ.2÷8-9::

ከዚህ በላይ የተመለከትናቸው የመጽሐፍ ክፍሎች ባልንጀራን መውደድ ማለት ሰውን ሁሉ መውደድ እን ደሆነ አረጋግጠውልናል:: አሥረኛው ትእዛዝ ደግሞ ባልንጀራን እንደራስ በመውደድ መፈጸም የሚገባው ትእዛዝ ነው:: «እንደራስ መውደድ» ሲባል ምን ማለት መሆኑን መመልከት አስፈላጊ ነው:: እንደራስ መውደድ ሰፊ ትርጉም ያለው ነው:: እንደሚከተለው እንመ ለከተዋለን::

እንደሚታወቀው ሁሉ ማንም ቢሆን በራሱ ላይ ክፉን የሚመኝ፣ የሚያደርግም የለም፣ ሞትን የሚወድ የሚሻውም የለም፤ ማንም መዋረድን፣ርኩሰትን፣ ውድቀትንም የሚፈልግ የለም:: ደግሞ ማንም ድኅነትን፣ ጸጋና በረከትን የማይሻ የለም:: ማንኛውም ሰው ዓይነቱ የተለያየ ይሁን እንጂ ለራሱ መልካም የሆነውን ሁሉ ይሻል:: መልካሙን ለማግኘት የተቻለውን ያህል የማይጥር የለም:: እንዲህ ከሆነ ባልንጀራን እንደራስ መውደድ ለራስ የሚሹትን መልካም ነገር ሁሉ ለባልንጀራ ማድረግ ማለት ነው:: በወንጌል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው፤ ሕግም ነቢያትም ይህ ነውና::» በማለት ያስተማረው ይህንኑ የሚያመለክት ነው:: ማቴ.7÷12:: በዚህ ትምህርት መሠረትም ሕግ በተባለች ኦሪት የታዘዘና በነቢያት ትንቢት የተሰበከው ፍቅር ይህ ነውና ባልንጀራን እንደራስ መውደድ ማለት ለራስ ቢያገኙት የሚወዱትን ለባልንጀራ ማድረግ ነው::

በሐዲስ ኪዳን ባልንጀራን እንደራስ መውደድ ማለት ከዚህም የበለጠ ትርጉም ተሰጥቶት እናገኛለን:: የዚህ ማረጋገጫ የሚሆነውም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «እያንዳንዱ የባልንጀራውን ጥቅም እንጂ አንድ ስንኳ የራሱን ጥቅም አይፈልግም:: ሲል» የተናገረው ነው:: 1ቆሮ.10÷24:: በዚህ ትምህርቱም የባልንጀራን ጥቅም ከራስ አስበልጦ መመልከት የሚገባ መሆኑን ገልጧል:: ይህንንም ለፊልጵስዩስ ሰዎች በላከው መልእክት «በአንድ ሃሳብ ተስማሙ፣ አንድ ፍቅር፣ አንድም ልብ፣ አንድም ሃሳብ ይሁንላችሁ፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትኅትና ይቁጠር፤ እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት÷ ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ::» በማለት አጠናክሮታል:: ፊልጵ.2÷2-4:: በዚህም ባልንጀራን እንደራስ መውደድ ማለት ፍቅርን በትሕትና መግለጥ መሆኑን እናስተውላለን::

ስለሆነም ሰው ባልንጀራውን እንደራሱ፣ ከራሱም አብልጦ የሚወደው ከሆነ የተቀደሰ የባልንጀራውን ሰውነትና መንፈሳዊ ሕይወቱን ያጠፋ ዘንድ አይገድለውም፤ አካሉን በዝሙት አያረክሰውም፤ ሀብቱንም ሆነ ንብረቱን አይሰርቅበትም፣ በሐሰት አይመሰክርበትም፣ ንብረቱንና ቤቱን በመመኘትና በመቅናት አይመቀኘውም:: ከአሥርቱ ትእዛዛት መካከል የሰዎችን የእርስ በርስ ግንኙነት የሚመለከቱትን ሁሉ የሚተላለፍ የፍቅርን ሕግ ይጥሳል:: ባልንጀራውንም የማይወድ ሰው ትእዛዛትን እንዳይጥስ፣ ሕግም እንዳያፈርስ የሚከለክለው ገደብ የለም::

ስለዚህ ለሰው ፍቅር የሌለው ማንም ቢሆን ጎሊናውን የሚከብደውና በወንድሙ ላይም ክፉን እንዳያደርግ የሚቃወመው ውስጣዊ ሃሳብና ስሜት ስለሌለ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በመተላለፍ ኃጢአትን እየፈጸመ የዲያብሎስ ባሪያ ሆኖ ይኖራል:: ይህ እንዳይሆን ነው አምላካችን እግዚአብሔር «ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ» በማለት ያዘዘው:: ነቢየ እግዚአብሔር ሳሙኤል «በውኑ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት ደስ እንደሚለው እግዚአብሔር በሚቃጠ

ልና በሚታረድ መሥዋዕት ደስ ይለዋልን? እነሆ መታዘዝ ከመሥዋዕት፥ ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል፡፡» ያለው የእግዚአብሔርን ሕግ መፈጸም የከበረ መንፈሳዊ ዋጋ ያለውና እግዚአብሔርንም የሚያስደስት መሆኑን ለማስረዳት ነው፡፡ 1ሳሙ.15፥22፡፡

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በመዋዕለ ትምህርቱ ባልንጀራን እንደመውደድ እግዚአብሔርን የሚያስደስተው ነገር የሌለ መሆኑን ሲገልጥ «በፍጹም ልብ በፍጹም አእምሮም በፍጹም ነፍስም በፍጹም ኃይልም እርሱን መውደድ እግዚአብሔርን፥ባልንጀራንም እንደራስ መውደድ በሙሉ ከሚቃጠል መሥዋዕትና ከሌላው መሥዋዕት ሁሉ የሚበልጥ ነው» በማለት አስተምሯል፡፡ ማር.12፥33፡፡

እግዚአብሔርን መውደድና ባልንጀራንም እንደራስ መውደድ የሕግጋት ማሠሪያ ነው፤ ሕግጋትና ትእዛዛት ሁሉ በእነዚህ በሁለቱ ይጠቃለላሉ፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍትም ይህንኑ ያረጋግጡልናል፡፡ ከነዚህም ማረጋገጫዎች መካከል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትእዛዛት ሁሉ እግዚአብሔርን በማፍቀርና ባልንጀራን እንደራስ በመውደድ የሚጠቃለሉ መሆኑን ከገለጸ በኋላ «ኦሪትና ነቢያት በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ጸኑ» በማለት የተናገረው አንዱ ነው፡፡ ማቴ.22፥37–40፡፡

ቅዱስ ጳውሎስም በዚህ ቃለ ወንጌል መሠረት ለሮሜ ክርስቲያኖች በጻፈው መልእክት «እርስ በርሳችሁ ከመዋደድ በቀር ለማንም ዕዳ አይኑርባችሁ፥ ሌላውን የሚወድ ሕግን ፈጽሞታልና፡፡ አታመንዝር፥ አትግደል፥ አትስረቅ፥ በውሸት አትመስክር፥ አትመኝ የሚለው ከሌላ ይቱ ትእዛዝ ሁሉ ጋር በዚህ ባልንጀራህን እንደነፍስህ ውደድ በሚለው ቃል ተጠቅልሎአል፡፡ ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም» በማለት ተናግሯል፡፡ ሮሜ.13፥8–10፡፡ ይህም ፍቅር የእግዚአብሔርን ሕግ በመፈጸም አማናዊውን የክርስትና ሕይወት በተግባር የመግለጥ የመጨረሻ የዕድገት ደረጃ መሆኑን የሚያስረዳ ትምህርት ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ፍቅር ትእዛዛትን በመፈጸም የሚገኘውን መንፈሳዊ ክብርና ሰማያዊ አክሊል ገንዘብ ለማድረግ መዘጋጀት ያስፈልጋልና፡፡

ፈጣሪአችን ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል ሲያስተምር «ከትእዛዛቱ ሁሉ ፊተኛይቱ፡– እሥራኤል ሆይ፥ ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፥ አንተም በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ፣ በፍጹምም ሃሳብህ፣ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትል ናት፡፡ ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት፡፡ ሁለተኛይቱም ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ የምትል እርሷን የምትመስል ይህች ናት» ብሏል፡፡ ማር.12፥29–31፡፡

ይህ ምንባብ ቀደም ብለን እንደተመለከትናቸው ትእዛ
ዛት በፍቅረ እግዚአብሔርና በፍቅረ ቢጽ መጠቃለላቸውን ከ
ማ ሳየቱም በላይ «ባልንጀራህን እንደራስ መውደድ» የሚለ
ውም ከእግዚአብሔር የተሰጠ ትእዛዝ መሆኑን የሚያረጋግጥ
ነው። እያንዳንዳችንንም በዕድሜ፣ በዕውቀት፣ በሥራ ቦታ፣ በማ
ኅበራዊ ኑሮ ይህን በመሳሰለው ሁሉ ባልንጀራ የሆነውን የሰው
ዘር በመውደድ ትእዛዛትን መፈጸምና ሰማያዊውን መንፈሳዊ
በረከት ለማግኘት እንድንዘጋጅ የሚመክር አምላካዊ ቃል
ነው።

በዚህ በአሥረኛው ትእዛዝ መሠረት ወንድምን መውደድ
ወይም ባልንጀራን እንደራስ የመውደድ ፍቅር የእግዚአብሔር
ስጦታ መሆኑን በሚገባ ዐውቀናል። ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም
«የእግዚአብሔር ልጆችና የዲያብሎስ ልጆች በዚህ የተገለጡ
ናቸው፤ ጽድቅን የማያደርግና ወንድሙን የማይወድ ሁሉ ከእግዚ
አብሔር አይደለም።» ሲል የተናገረው ወንድምን መውደድ
የእግዚአብሔር ልጅነት ማረጋገጫም ጭምር መሆኑን ሲገልጥ
ነው። የእግዚአብሔር ልጆች መንፈሳውያን ናቸውና በመንፈሳዊ
ምግባራቸው፤ ሰውንም በመውደዳቸው ይታወቃሉ።
1ዮሐ.3÷10። በመቀጠልም «እኛ ወንድሞችን የምንወድ ስለሆንን
ከሞት ወደ ሕይወት እንደተሻገርን እና ውቃለን፤ ወንድሙን የ
ማይወድ በሞት ይኖራል። ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ
ነው÷ ነፍሰ ገዳይም የሆነ ሁሉ የዘላለም ሕይወት በእርሱ
እንዳይኖር ታውቃላችሁ። ...ወንድሙም የሚያስፈልገውን ሲያጣ
አይቶ ያልራራለት ማንም ቢሆን ÷የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ
እንዴት ይኖራል? ልጆቼ ሆይ÷ በሥራና በእውነት እንጂ በቃ
ልና በአንደበት አንዋደድ።» በማለት ፍቅር በተግባር መገለጥ
የሚገባው መሆኑን አበክሮ አስገንዝቧል። 1ዮሐ.3÷14–18።

በሌላ ምንባብም ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ «በብርሃን
አለሁ የሚል ወንድሙን የሚጠላ እስከአሁን በጨለማ አለ።
ወንድሙን የሚወድ በብርሃን ይኖራል ማሰናከያም የለበትም፤
ወንድሙን የሚጠላ ግን በጨለማ አለ÷ በጨለማም ይመላለሳል÷
የሚሄድበትንም አያውቅም÷ ጨለማው ዓይኖቹን አሳውሮ
ታልና።» በማለት ያስተማረው ባልንጀራን መውደድ ብሩህ የሆነ
አምላካዊ ስጦታ መሆኑን የሚገልጥ ነው። 1ዮሐ.2÷9–11።

ባልንጀራን መውደድና እግዚአብሔርን መውደድ የማይ
ነጣጠሉ ናቸው። የአንዱ መኖር የሌላኛውን ሕልውና እየገለጠ
የሰውን ልጅ ከውድቀትና በኃጢአት የተነሣ ከሚመጣው ሞተ
ነፍስ የሚታደጉ ሰማያውያን ስጦታዎች ናቸው። ስለዚህም ነው
ቅዱስ ዮሐንስ «እግዚአብሔርን ስንወድ ትእዛዛቱንም ስናደርግ
የእግዚአብሔርን ልጆች እንድንወድ በዚህ እናውቃለን።» ያለው።
1ዮሐ.5÷2–3። በመሆኑም የእግዚአብሔር ልጆች የተባልን ሁሉ
ባልንጀሮቻችንን በመውደድና ትእዛዛቱንም በመፈጸም የፍቅር
ልጆች እውነተኛም አፍቃሪዎች ለመሆን እንችል ዘንድ
እንበርታ። በዚህ ሰማያዊ ሕግ በፍቅረ ቢጽ አንድ ሆነን የእግዚ
አብሔርን በረከት ለማግኘት እንችል ዘንድ እርሱ ልዑል
አምላካችን ቅዱስ ፈቃዱ ይሁን፤ አሜን።